«የድሮዋን ጠንካራዋን ኢትዮጵያ ስመመለስ 10 ዓመት እንኳን አይፈጅብንም»

- ዶክተር እመቤት ገዛኸኝ
የተወካዮች ምክር ቤት አባልና የጥርስ ሕክምና ክሊኒክ ባለቤት



ገጽ 6

ታካሚዎችን ከወጪና እንግልት የታደገ ማዕከል

ገጽ 8



ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

81ኛ ዓመት ቁጥር 351 ነሐሴ 21 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

DERBA CEMENT



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


# የትግራይ ሕዝብ መቸገርና መራብ ለአሸባሪው ሕወሓት ደስታ ነው



ጌትነት ምህረቴ

አዲስ አበባ፡- የትግራይ ሕዝብ ችግር፣ ርሃብ፣ ሞትና መከራ ለአሸባሪው ሕወሓት ደስታ ነው ሲሉ በአሜሪካ የሚኖሩ የትግራይ ተወላጅ ዲያስፖራ አቶ ነጋሲ በየነ ገለጹ፡፡

አቶ ነጋሲ በየነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የትግራይ ሕዝብ ሲቸገር፣ ሲራብ፣ ሲሞትና ሲሰቃይ አሸባሪው ሕወሓት በሕዝቡ ጉዳትና ደም እሱ ይፋፋል፡፡

በቀደመው ዘመን ወያኔ በረሃ እያለ የትግራይ ሕዝብ እየተራበ ለሰብዓዊ ዕርዳታ የመጣውን እህል እየሸጠ መሳሪያ ይገዛበት ነበር ያት አቶ ነጋሲ፤ አሸባሪው ቡድን ይህን የቆየና ስር የሰደደ እኩይ ባህሪውን በአሁኑ ጊዜም ደግሞታል፤ በትግራይ ህዝብ ስም የሚላከውን ሰብዓዊ እርዳታ ከሕዝቡ ጉሮሮ ነጥቆ ለጦርነት እያዋለው ይገኛል፡፡

አሸባሪው ሕወሓት በትግራይ ሕዝብ ርሃብና ስቃይ የሚነግድ ቡድን መሆኑን ያለፈ ታሪኩ ይመሰክራል ያሉት አቶ ነጋሲ፤ ከበረሃ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የትግራይን ሕዝብ በማይጠቅም የጦርነት አዙሪት ውስጥ አስገብቶ የወጣቶችን ነፍስ እየበላና ሕዝብ በርሃብ እንዲሰቃይ እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የትግራይ ሕዝብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

## ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሕወሓትን ወደ ሰላም መንገድ ሊመልሰው ይገባል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ሰላማዊ መንገድ እንዳይዘጋ፣ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ሕወሓትን ወደ ሰላም መንገድ እንዲያመጣው መንግስት ጥሪ አቀረበ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በወቅታዊ ጉዳይ ላይ ትናንት ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤

ዓለም አቀፉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## “ሕወሓት የትግራይ ሕዝብን መያዣ አድርጎ እየተጠቀመ ነው”

- ጋዜጠኛ ሔርሜላ አረጋዊ

አብዱረዛቅ መሐመድ

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ዳግም ወደስልጣን ለመመለስ የትግራይ ሕዝብን መያዣ አድርጎ እየተጠቀመ እንደሚገኝና ሕዝቡ ለደረሰበትና እየደረሰበት ላለው መከራ ተጠያቂ መሆኑን ኢትዮ-አሜሪካዊቷ ጋዜጠኛ ሔርሜላ አረጋዊ ተናገረች።

ጋዜጠኛ ሔርሜላ በአንድ የአሜሪካ የሚድያ ተቋም ላይ ቀርባ እንደተናገረችው፤ አሁን በትግራይ ክልል እየሆነ ያለው ነገር ባለፉት 27 ዓመታት ውስጥ ሀገሪቷን ጭካኔ በተሞላበት አካሄድ ሲመራ በነበረና አሁን ክልሉና ሕዝቧን መያዣ አድርጎ በሚጠቀም ጽንፈኛና ጨካኝ የሕወሓት የሽብር ቡድን አማካኝነት ነው።

ሕወሓት ለበርካታ ሕዝብ እልቂት ምክንያት የሆነውን የሰሜኑ ኢትዮጵያ ጦርነት በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት በቀረበው የሰላም ውይይት ላይ ለመሳተፍ ፍቃደኛ አለመሆኑን በግልጽ አሳይቷል ያለችው ጋዜጠኛ ሔርሜላ፤ ቡድኑ አሁንም ወደ ስልጣን ለመመለስ የትግራይ ሕዝብን መያዣ አድርጎ ይዟል፤ ሕዝቡ ላይ እየደረሰ ላለው



ስቃይም ተጠያቂው ሕወሓት ነው ብላለች፡፡

ለትግራይ ሕዝብ እቆረቆራለሁ የሚል ማንኛውም

“ሕወሓት የትግራይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል
















ገጽ 4

የሽብር ቡድኑ የፈጸመው የነዳጅ ዘረፋ የኖረበት የሌብነት ባህሪው ነው



ዜና

# በኦጋዴን ሰባት ትሪሊዮን ኪዩቢክ ጫማ የተፈጥሮ ጋዝ መኖሩ ተረጋገጠ

ጌትነት ምህረቴ




አዲስ አበባ፡- በኦጋዴን አካባቢ መውጣት የሚችል ሰባት ትሪሊዮን ኪዩቢክ ጫማ የተፈጥሮ ጋዝ መኖሩን የማዕድን ሚኒስቴር አዲስ ባስጠናው ጥናት ማረጋገጡን አስታወቀ።

የነዳጅና የተፈጥሮ ሀብት አቅምና አዋጭነት በተመለከተ የማዕድን ሚኒስቴር የአሜሪካ ኩባንያ ከሆነው ኤልሲኤአይ (LCAI) ጋር የጥናት እና ሰርተፍኬት ርክክብ በዛሬው እለት በአዲስ አበባ አካሂዷል።

ለአራት ወራት በተካሄደው ጥናት በኢትዮጵያ የሚገኙ የነዳጅ ሀብት መጠን ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ርክክብ ተካሂዷል። የአሜሪካ ኩባንያ በሆነው ኤልሲኤአይ (LCAI) አሸንፎ ወደ ሥራ መግባቱ ተገልጿል።

በርክክብ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ኡማን ጨምሮ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የአሜሪካ ኤምባሲ ተወካዮች ተገኝተዋል።

የማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ኡማ “እስከዛሬ አለ እየተባለ በአባቶቻችን ሲነገረን የቆየውን የተፈጥሮ ጋዝ ሀብታችንን እና የወደፊት እጣ ፋንታችንን የሚወስን አንዱ የሀገራችን የኢኮኖሚ ዋልታ እንዲሆን እንሠራለን” ብለዋል።

የተፈጥሮ ጋዝ ለሀገር ምርት እና ለውጭ ንግድ የምንጠቀምበት ይሆናል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ሰርተፍኬቱ ምን ያክል የተፈጥሮ ጋዝ እንዳለን የምናውቅበት ይሆናል ብለዋል።

የሰርተፍኬቱ ሚና ሀገራችን ያላትን የተፈጥሮ ሀብት፣ እውቀት፣ ልምድና ፍላጎት ሳይኖራቸው አንቀው ከቆዩ ችግሮች በመላቀቅ ሊሰሩና ሊያለሙ የሚችሉ ትላልቅ ኩባንያዎች ጋር ለመሥራት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

የተቀበልነው ሰነድ የተፈጥሮ ጋዝ እና ድፍድፍ ነዳጅ የማልማት ሀገራዊ እቅዳችንን አንድ እርምጃ ያራመደና በትልቁ የመንግስት ቁርጠኝነት የታየበት ስራ ነው ሲሉም ተናግረዋል፡፡

ይህ ሰነድ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ጋዝ መጠንና የኢኮኖሚ አዋጭነት የማረጋገጫ ሰርተፊኬት ነው፤ይህንን ሰርተፊኬት ይዘን በዓለም አቀፍ ደረጃ የቴክኖሎጂ፣የፋይናንስ እና በዚህ ኢንቨስትመንት አቅም ያላቸው ኩባንያዎች መጋበዝ ችለናል ብለዋል፡፡

የተዛባ መረጃ ይዘው ሀብታችንን እስረኛ እያደረጉ ላሉ ኩባያዎችም ጥሩ ማንቂያ ይሆናል ብዬ አምናለሁ ያሉት ሚኒስትሩ፤ በስራው ለተሳተፉ ሁሉ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

ሰነዱን ወደ ተግባር ለመቀየርም ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ጠቁመው፤ ወደ ተግባር የመቀየሩ ጉዳይም እንደ አሰራራችን ፍጥነት የሚወሰን ይሆናል ብለዋል፡፡



አምባሳደር ተሾመ ቶጋ

# መገናኛ ብዙኃኑ የሀገራቱ ግንኙነት እንዲጎለብት ሊሰሩ ይገባል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ እና የቻይና መገናኛ ብዙኃን ትብብራቸውን በማጠናከር የአፍሪካ-ቻይና ግንኙነት እንዲጎለብት ሊሰሩ እንደሚገባ በቻይና የኢትዮጵያ አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ተናገሩ።

አምስተኛው የቻይናና የአፍሪካ የመገናኛ ብዙኃን ትብብር ፎረም የቻይና የመስኩ ከፍተኛ ባለሥልጣናት፣ የአፍሪካ አገራት አምባሳደሮችና ከቻይናና ከተለያዩ የአፍሪካ አገራት የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት የተውጣጡ ጋዜጠኞች በተገኙበት ተካሂዷል።

በመርሀ ግብሩ ንግግር ያደረጉት በቻይና የኢትዮጵያ አምባሳደር ተሾመ ቶጋ፤ የአፍሪካና የቻይና ትብብርንና ግንኙነትን በተመለከተ የሚራገቡትን የተሳሳቱ መረጃዎች ለመመከት በጋራ መሥራት ይገባል።

የቻይናና የአፍሪካ የመገናኛ ብዙኃን የየራሳቸውን አገራት የተመለከቱ መረጃዎችን በራሳቸው እይታና እውነታውን በሚያሰርጽ መንገድ አሳሳች መረጃዎችን በሚከላከልና በሚመክት አግባብ መዘገብ ይገባቸዋል ብለዋል።

ይህም በተለይም የአፍሪካና ቻይና ትብብርን በተመለከተ የሚናፈሰውን የተሳሰተ መረጃ ለመቀልበስ እንደሚረዳ አስገንዝበው፤ ለዚህም በአፍሪካ በቻይና በመስኩ ያለው ትብብር መጠናከር እንዳለበት አሳስበዋል።

በአፍሪካና በቻይና በመገናኛ ብዙኃን በተለይም በዜና ሽፋን፣ በአመራር፣ በስርጭት ጣቢያ ልማት፣ በይዘት ሥራ፣ በእውቀት፣ በቴክኖሎጂና በሥልጠና የጋራ መርሀ ግብሮች በመቅረጽ ትብብሩ ሊጠናከር እንደሚገባው ነው አጽንኦት የሰጡት።

ይህም እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2018 ከተመሰረተው የአፍሪካና የቻይና የትብብር ማዕቀፍን ባገናዘበ መልኩ በጋራ ተጠቃሚነትና እኩልነት መርህ መፈጸም እንዳለበት ጠቁመዋል።

የአፍሪካና የቻይና የመገናኛ ብዙኃን ተቋማት ትብብር የጋራ ልማትና ብልጽግና ለማምጣት እንዲሁም በሁለቱ ወገን መካከል ያለውን የምጣኔ ሀብታዊ፣ ባህላዊ፣ ማኅበራዊ እንዲሁም ሌሎች የትብብር መስኮችን የተመለከቱ እውነታዎችን ለዓለም ለማሳየት ይጠቅማል ብለዋል።

የቻይናና የአፍሪካ የመገናኛ ብዙኃን ትብብር በአፍሪካ ቻይና የትብብር ማዕቀፍ ትልቅ ሥፍራ መያዙን የጠቀሱት አምባሳደር ተሾመ፤ ይህም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አሳስበዋል።

በመርሀ ግብሩ ላይ የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት ያስተላለፉት የቻይናው ፕሬዚዳንት ሺ ዢንፒንግ በበኩላቸው፤ የቻይናና የአፍሪካ የመገናኛ ብዙኃን በጋራ ሊሰሩ ይገባል ብለዋል።

በተለይም በሁለቱ ወገን ህዝቦች መካከል ያለውን የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት በማጠናከር፤ የእኩልነትና ፍትህ ጠበቃ በመሆን ለዓለም ልማት ሊተጉ እንደሚገባ ገልጸዋል።

ቻይና እና አፍሪካ ተመሳሳይ ራዕይ ያላቸው ሕዝቦች መሆናቸውን ጠቁመው፤ በሁለቱ ወገን ያሉት የመገናኛ ብዙኃን የጋራ ስምምነትና ትብብር እንዲኖር መሥራት ይኖርባቸዋል ነው ያሉት።

በተለይም የዓለምን ሰላምና መረጋጋት ለማስፈን እንዲሁም የጋራ ራዕይ ያላቸው ማኅበረሰቦች ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት የመገናኛ ብዙኃን ተቋማቱ በጋራ ሊሰሩ የሚገባቸው መስኮች መሆኑን አንስተዋል ሲል የዘገበው ኢ.ዜ.አ ነው።

የቻይና አፍሪካ የሚዲያ ፎረም ከተመሰረተ ዘንድሮ አስር ዓመት ሆኖታል። እስካሁን ሶስት ሺህ የሚጠጉ የአፍሪካ ጋዜጠኞች በቻይና የሙያ ሥልጠና መውሰዳቸውን መረጃዎች ያሳያሉ።

# አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት የሙከራ ትግበራ በቀጣይ ዓመት ይጀመራል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል አዲሱ ሥርዓተ-ትምህርት የሙከራ ትግበራ ከሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች በተመረጡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በቀጣይ ዓመት እንደሚጀመር የትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

ለዚህም ይረዳ ዘንድ የሙከራ ትግበራ ከሚካሄድባቸው ትምህርት ቤቶች ለተውጣጡ መምህራን ስርዓተ ትምህርቱን የማስተዋወቅ ስልጠና እየተሰጠ እንደሚገኝ ተገልጿል፡፡

አዲሱ የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት በርካታ ደረጃዎችን አልፎ ለሙከራ ትግበራ የደረሰ መሆኑን የስርዓተ ትምህርት ማበልፀጊያ መሪ ስራ አስፈፃሚ ዶ/ር ቴዎድሮስ ሸዋይርጋ ገልፀዋል።

በስርዓተ ትምህርት ዝግጅቱ ላይ የተመረጡ የመማር ማስተማር የልህቀት ማዕከላት ዩኒቨርሲቲዎች እና ካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ በአማካሪነት እንደተሳተፉበት ሥራ አስፈፃሚው ጠቅሰዋል።

የተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርቶች ስርዓተ ትምህርት ዴስክ ኃላፊ ወ/ሮ ዛፉ አብርሃ በበኩላቸው፣ ይህ ሥርዓተ ትምህርት ሀገር በቀል እውቀትን፣ ግብረ ገብነትን ፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን የተላበሰ እንዲሆን ተደርጎ የተዘጋጀ መሆኑን ገልፀዋል።

በሙከራ ትግበራው ወቅት የሚመጡ አስተያየቶች ተካተው በ2016 ወደ ሙሉ ትግበራ እንደሚገባም በመድረኩ ተገልጿል።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል አዲሱ ስርዓተ ትምህርት በ2014 የሙከራ ትግበራ ተካሂዶ በ2015 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንደሚደረግም የሚኒስቴሩ መረጃ ያመለክታል።

ዜና

# የዲጂታል ኢኮኖሚ መሰረተ ልማቶች እየተዘረጉ ነው

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በቴክኖሎጂ ለመገበያየት የሚያስችሉ የኢ-ኮሜርስ እና ተያያዥ ቴክኖሎጂዎችን ለማስፋፋት የሚያግዙ የዲጂታል ኢኮኖሚ መሰረተ ልማቾ እየተዘረጉ መሆኑን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ሁሪያ አሊ ገለጹ።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ሁሪያ አሊ በሎጂስቲክስ የሥራ ዘርፍ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለማቃለል የሚረዳ «ማስዴል» የተሰኘ መተግበሪያ ይፋ ሲደረግ እንደገለጹት፤ በዓለማችን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ቴክኖሎጂ ትልቅ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። በኢትዮጵያም በቴክኖሎጂ የሚሰጡ አገልግሎችን ለማስፋፋት መንግሥት የኢ-ኮሜርስ እና ተያያዥ ቴክኖሎጂዎችን ለማስፋፋት የሚያግዙ የሕግ ማዕቀፎች እና የአሠራር ስርዓቶችን እየዘረጋ መሆኑን ጠቁመዋል።

አገራችን የቴክኖሎጂ ቱርፋቶች ተጠቃሚ እንድትሆን መንግሥት የግል ባለሀብቶችንና የልማት አጋሮችን በማስተባበር እየሠራ ይገኛል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ የአገራችንን ዲጂታል ኢኮኖሚ ለማሳለጥ ስትራቴጂ ተነድፎ እየተሠራ ነው። በስትራቴጂው ውስጥ ካሉ ቁልፍ ተግባራት መካከል የዲጂታል ኢኮኖሚ መሠረተ ልማቶችን መገንባት ይገኝበታል ብለዋል።

መንግሥት ኢ-ኮሜርስ እና ተያያዥ ቴክኖሎጂዎች እንዲስፋፉ አስፈላጊ የሆኑ የህግ ማእቀፎች እና የአሠራር ስርዓቶችን እየዘረጋ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለኢ-ኮሜርስና ተዛማጅ ሥራዎች እውቅና የሚሰጠውን የኢትራንዛክሽን አዋጅ፣ ከዲጂታል ክፍያና ከሎጂስቲክ አሰራሮች አንጻር የተዘጋጁ መመሪያዎች እና በሂደት ላይ ያሉ የግል ዳታ ጥበቃ አዋጅና የኢትራንዛክሽን ደንብን ለአብነት አንስተዋል።

‹ማስዴል› የተሰኘው መተግበሪያ ወደ ሥራ መግባቱም በሎጂስቲክ የሥራ ዘርፍ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለማቃለል ትልቅ ሚና ይጫወታል የሚል እምነት እንዳላቸው ጨምረው ገልጸዋል።

የማስዴል ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ተዋበ ይላክ በበኩላቸው፤ መተግበሪያውን ለማልማት እና አገልግሎት ለማስጀመር ከ30 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጎበታል። ይህም በሎጂስቲክስ የሥራ ዘርፍ የሚስተዋለውን ውጣ ውረድ ያቃልላል ብለዋል።

አሽከርካሪዎች ጭነቱ እስኪሰናዳ እና እስኪጫን የሚወስደው የቆይታ ጊዜ ተሰልቶ እንደሚከፈላቸው የገለጹት ዋና ስራ አስኪያጁ፤ የጭነት ጉዞ ታሪፍ በመተግበሪያው ላይ በሚሞላው መረጃ መሰረት የሚተመን መሆኑንም አመልክተዋል።

መተግበሪያው በአዲስ አበባ እና ዙሪያው አካባቢዎች ወደ ሥራ የገባ ወደ ሌሎች አካባቢዎች ብሎም ወደ ጎረቤት አገራት የማስፋት እቅድ እንዳላቸው አብራርተዋል።

ከሞተር ሳይክል ጀምሮ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው የጭነት አገልግሎት ሰጪ ተሽከርካሪዎች በመተግበሪያው መጠቀም እንደሚችሉ ጠቅሰው፤ መተግበሪያ በደንበኞች ፍላጎት መሰረት ከጥቃቅን እስከ ጅምላ ጭነት አገልግሎት ይሰጣል።

የማስዴል መተግበሪያ ለጊዜው በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሚሰራ ሲሆን፤ በቀጣይነት ከሌሎች ቋንቋዎች ጋር የማስተዋወቅ ሥራ እንደሚሠራ ጠቅሰው፤ አገልግሎቱን በስልክ ጥሪ ማዕከል፣ በመተግበሪያ እና በዌብሳይት አማካኝነት አገልግሎት ሰጪና አገልግሎት ፈላጊውን በፍጥነት የሚያገናኝ ስርዓት ነው ብለዋል።

# የንግድ ፈቃድና ኢንስፔክሽን አሰራርን ለማሻሻል የሕግ ማዕቀፍ እየተዘጋጀ ነው

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚስተዋለውን የተዘበራረቀ የንግድ ፈቃድ አሰጣጥና ኢንስፔክሽን አሰራር ወጥነት እንዲኖረው የሚያግዝ የሕግ ማዕቀፍ እየተዘጋጀ መሆኑ ተገለጸ።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከንግድና ቀጣናዊ ሚኒስቴር ጋር ያዘጋጀው የንግድ ምዝገባ ፣ ፈቃድና ድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ረቂቅ መመሪያ ላይ ያተኮረ ውይይት ትናንትና ተካሂዷል።

በወቅቱ የንግድና ቀጣናዊ ሚኒስቴር ዴኤታ አቶ ሃሰን ሞሐመድ እንደገለጹት፤ በተለያዩ አካባቢዎች ያለው የንግድ ፈቃድ አሰጣጥና የቁጥጥር ስራ ወጥነት ያለው ባለመሆኑ የተቀናጀ አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዳ ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቷል።

ከዚህ ባለፈ አሳሪ አሰራሮችን ከማስተካከል ባለፈ ለህገወጥነት በር የሚከፍቱ ህጎችን ለማስተካከል የሚረዳ የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል።

በተለይም እስካሁን ባለው አሰራር በንግድ ፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት መሰረት በአንድ ግለሰብ የስራ ቦታ አድራሻ ሳይኖረው የንግድ ፈቃድ ማውጣት ይችላል የሚል አሰራር እንደነበር አስታውሰው፤ አሰራሩ ከሚኒስቴሩ የቁጥጥር ስራዎች ጋር ሊጣጣም አለመቻሉን ገልጸዋል።

በተለይ የንግድ አድራሻዎችን ለማግኘት አስቸጋሪ ስለሚሆንና ለህገወጥ አሰራር ክፍተት ስለሚፈጥር ችግሩን የሚቀርፍ መመሪያ ማስፈለጉን ተናግረዋል።

ከዚህ ባለፈ መመሪያው በአንድ አድራሻ ሶስትና አራት የንግድ ፈቃድ በማውጣት አላግባብ የንግድ ዘርፉን ለመጉዳት የሚሞክሩትን አካላት ለመቆጣጠር እንደሚረዳም ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ሃሰን ገለጻ፤ በ1952 ዓ.ም ወጥቶ የነበረው



**አቶ ሃሰን ሞሐመድ**

የንግድ ሕግ ባለፈው ዓመት በአዲስ መልክ ተሻሽሎ ከወጣ በኋላ ሕጉ ያመጣቸውን አዳዲስ ለውጦች ታሳቢ በማድረግ የተሻሻለ የንግድ ምዝገባ፤ ፈቃድና ድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን መመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቷል።

ረቂቅ መመሪያው በከተማ አስተዳደሮችም ሆነ በክልል የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ቢሮዎች ዘንድ ግልጽና ተመሳሳይ አሰራር እንዲኖር የሚያግዝ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው ፤በቀጣይ ግብዓቶች ተካተውበት ረቂቅ መመሪያው እንዲጸድቅ ጥረት ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ኢንጂነር መላኩ አዘዘው በበኩላቸው፤ ከንግዱ ማህበረሰብ የሚነሱ ችግሮችን በመረዳት ረቂቅ መመሪያው መዘጋጀቱን አድንቀው፤ ለንግድ ሥርዓቱ አሳሪ የሆኑና ጊዜው የደረሰበትን የቴክኖሎጂ የዕድገት ደረጃ ታሳቢ ያደረጉ አሰራሮች እንደሚያስፈልጉ ተናግረዋል።

በተለይ የንግድ ፈቃድ ለማውጣት፤ ፈቃድ ለማሰረዝና ተመሳሳይ አገልግሎቶችን ለማግኘት ወደቢሮዎች ሲኬድ ከባለሙያ ባለሙያ የተለያየ አሰራርና መልስ እንደሚሰጥ ፕሬዚዳንቱ ጠቁመዋል።

እንደየሰው አረዳድና ፍላጎት የተለያዩ መስፈርቶች ስለሚጠየቁ በርካታ የንግዱ ማህበረሰብ በአገልግሎቶቹ ደስተኛ እንደማይሆኑ ገልጸዋል።

አሁን ላይ የተዘጋጀው ረቂቅ መመሪያ በአስር ክፍሎት ተዋቅሮ ለእያንዳንዱ አገልግሎት ምን አይነት መስፈርት እንደሚያስፈልግ በግልጽ የሚያስቀምጥ በመሆኑ አገልግሎት ለሚያገኘውም ሆነ አገልግሎት ለሚያቀርበው አካል ወጥነት ያለው አሰራርን የሚያስተዋውቅ እንደሚሆን ጠቁመዋል።

በምክክር መድርኩ የተካፈሉ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት የንግድ ፈቃድ ለማውጣት፣ ፍቃድ ለማደስ፣ ንግድ ዘርፍ ለመቀየርና ፍቃዳቸውን ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማሳደግ ሲፈልጉ በአንዱ ክፍለ ከተማ ቢሮ የሚጠየቁትና በሌላኛው ክፍለከተማ አሊያም በሌላ ከተማ የሚጠየቁት መስፈርት ሰፊ ልዩነት እንደሚስተዋልበት አንስተዋል።

ችግሩን በመቅረፍ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥነት ያለው አሰራር ለመተግበር የሚያግዝ መመሪያ መዘጋጀቱም ለስራቸው መሻሻል አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ተናግረዋል።

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥና የድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ረቂቅ መመሪያው ጸድቆ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ተከታይ የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች እንደሚዘጋጁ የንግድና ቀጣናዊ ሚኒስቴር አስታውቋል።

# በከተማዋ የውሃ ብክነት ለመቀነስ የ696 ሚሊዮን ብር ፕሮጀክት ይፋ ተደረገ

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የሚስተዋለውን ከፍተኛ የውሃ ብክነት ለመቀነስ የሚያስችልና በዓለም ባንክ የሚደገፍ የ696 ሚሊዮን ብር ፕሮጀክት ትግበራ መጀመሩን ባለስልጣኑ አስታወቀ። የከተማዋ ውሃ ብክነት ከ37 እስከ 41 ከመቶ ይደርሳል ተብሏል።

የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ውጤትን መሠረት ያደረገ የውሃ ብክነትና ቁጥጥር ፕሮጀክት አስተባባሪ አቶ አልታሰብ አዘዘው በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በመደበኛው የባለስልጣኑ ሥራ የውሃ ብክነት ለመቀነስ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ሲሆን በዓለም ባንክ የሚደገፍ አዲስ ፕሮጀክት ትግበራ መጀመሩን አስገንዝበዋል።

የከተማዋ አጠቃላይ የውሃ ብክነት ከ37 እስከ 41 ከመቶ እንደሚደርስ ጥናቶች የሚያመለክቱ መሆኑን ያወሱት አቶ አልታሰብ፤ ይህን ብክነት በመቀነስ በመደበኛ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ እየሰራ ነው።

የውሃ ብክነት በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከሰቱ ሲሆን የመጀመሪያው ፊዚካል ብክነት የሚሰኘው፤ የተለያዩ መሠረተ ልማቶች ግንባታዎች ሲከናወኑ በሚሰበር መስመርና እንዲሁም ሌሎች የውሃ መሰረተ ልማቶችና ቧንቧዎችና መስመሮች እያረጁ ውሃ ሲያፈሱ ውሃ ይባክናል። በተጨማሪም ከተማውም ሰፊ በመሆኑም የውሃ መስመር ሲስተም ማስተካከያ አለመደረጉም ውሃ ይባክናል ብለዋል።

ሌላኛው ኮምርሻል ብክነት የሚሰኘው ደግሞ ውሃው ጥቅም ላይ እየዋለ ገቢ ባለመሰብሰብ የሚከሰት ብክነት መሆኑን የጠቀሱት አስተባባሪው፤ ይህም ሕግ-ወጥ የውሃ መስመር ቅጥያ፣ ዘመናዊ የውሃ ቆጣሪዎችን ሥራ ላይ አለማዋል፤ ተቋማት በወቅቱ የውሃ ቆጣሪ አለመክፈል፣ በውሃ ቆጣሪ ባለሙያ ንባብ እና ዳታ ኢንኮዲንግ አለመናበብ፣ ሕብረተሰብ የውሃ ቆጣቢ ቴክኖሎጂ አለመጠቀምን ያካትታል ብለዋል።

በዚህ የተነሳ ከፍተኛ የውሃ ብክነት እየተስተዋለ በመሆኑ ተቋሙ አዲስ ፕሮጀክት ለመተግበር መገደዱን አቶ አልታሰብ አስረድተዋል።



**የለገዳዲ ውሃ ፕሮጀክት**

እንደ አስተባባሪው ገለፃ፤ ይህ ፕሮጀክት በለሚ ኩራ እና ጉርድ ሾላ ቅርንጫፎች ለናሙና የሚተገበር ሲሆን 100ሺ ደንበኞችን ተጠቃሚ ያደርጋል። በዚህ ፕሮጀክትም በቀን 18ሺ ሜትር ኪዩብ ውሃን ከብክነት ማዳን ይቻላል። ይህን ፕሮጀክት በሂደት በሌሎች የከተማዋ ክፍሎች ተግባራዊ ይደረጋል።

የፕሮጀክቱ ትግበራ በአሁኑ ወቅት የተጀመረ ሲሆን አራት ዓመት ከሁለት ወር ውስጥ የሚጠናቀቅ ሲሆን፤ ለዚህም 696 ሚሊዮን ብር የወጪ ይደረጋል። የፕሮጀክቱ ዋነኛ ዓላማው ከ37 እስከ 41 ከመቶ የሚባክነውን ውሃ መቀነስ ነው። ይህ ለማድረግ ደግሞ አዳዲስ መስመሮችንና ቆጣሪዎችን መቀየር፣ ሲስተም ማስተካከል፣ የውሃ ግፊት ማመጣጠንና ተያያዥ ሥራዎች ይከናወናሉ። ይህም እንደሞዴል ተወስዶ የእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ በሌሎችም ቅርንጫፎች የሚተገበር ይሆናል።

ፕሮጀክቱን የዓለም ባንክ በገንዘብ የሚደግፈው ሲሆን፤ በአፍሪካ እና ሌሎች የዓለማችን ሀገራት ረጅም ልምድ ያዳበረው ‹‹ሚያ›› የተባለው የአውሮፓ ኮንትራክተር ሥራውን የሚያከናውን ይሆናል። ባለስልጣኑ ደግሞ ፕሮጀክቱን በዋናነት የሚያስተዳድር ሲሆን፤ አስፈላጊ መረጃዎችንም በወቅቱ ይሰጣል።

ከአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የተገኘው አሃዛዊ መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ባለስልጣኑ በአሁኑ ወቅት በቀን 700ሺ ሜትር ኪዩብ ውሃ እያመረተ ለደንበኞች የሚያቀርብ ሲሆን፤ ዕለታዊ የከተማዋ ፍጆታ ግን 1ነጥብ2 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ የከተማዋ ውሃ ብክነት ከ37 እስከ 41 ከመቶ ደርሷል። በተጨማሪም ከሚመረተው ውሃ 25 ከመቶ የሚሆነው በመብራት መቆራረጥ የተነሳ ይባክናል።

ዜና

# የሸብር ቡድኑ የፈጸመው የነዳጅ ዘረፋ የኖረበት የሌብነት ባህሪው ነው

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት የፈጸመው የነዳጅ ስርቆት ከምስረታው ጀምሮ የመጣበትን የሌብነት ባህሪ በግልጽ ያሳየ መሆኑን የሠላም አምባሳደር፣ የሰብዓዊ መብትና የመልካም አስተዳደር ተሟጋች የሆኑት አቶ ምዑዝ ገብረህይወት ገለጹ። የሕወሓት ፍላጎት በግጭት ውስጥ በመኖር የትግራይ ህዝብ እንዲያልቅ ነው ብለዋል።

አቶ ምዑዝ ገብረህይወት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሕወሓት በትግራይ ከባንክ ጀምሮ እስከ ምስኪኑ ህብረተሰብ ድረስ ሲዘርፍ የመጣ በመሆኑ ነዳጅ መዝረፉ አዲስ ባህሪ አይደለም። በቅርቡም በአፋርና በአማራ ክልል ወረራ በፈጸሙበት ወቅት የተቦካ ሊጥ ሳይቀር ዘረፋ የፈጸመ ነው።

አቶ ምዑዝ እንደሚሉት፤ ቡድኑ ከምስረታቸው ጀምሮ በትግራይ ከባንክ እስከ ምስኪኑ ህብረተሰብ ድረስ የቤት ቁሳቁስ ሳይቀር ሲዘርፍ የመጣ ነው። ስለዚህ የነዳጅ ስርቆቱ አዲስ ባህሪ አይደለም። የፌደራል መንግሥት የሰላም ኮሚቴ አቋቁሞ ለሰላማዊ ድርድር በሩን ቢከፍትም ሕወሓት ግን ለሰላማዊ ውይይቱ ዝግጁ አለመሆኑን ኮሚቴ እንኳን ሳያቋቁም በሩን ዝግ አድርጓል። ከዚያም አልፎ ወደጦርነት ገብቷል። ስለዚህ ሰላም የማይፈልግ ከልጅነቱ እስከ እርጅና ዘመኑ በደም የተጨማለቀ ተራ የሽብር ቡድን ስብስብ ነው።

ከተለያዩ ድርጅቶች ሰላም ፈጥረው አብረው ኑረው አያውቁም ያሉት አቶ ምዑዝ፤ የሕወሓት ፍላጎት ዕድሜ ልኩን በጦርነት በመቆየት የትግራይ ህዝብ እንዲያልቅ ነው። ጦርነት አቁመው ሰላም ከፈጠሩ የትግራይ ህዝብ ልጆቻችን የት ናቸው ብሎ ይጠይቃቸዋል። ሕወሓት ነዳጅ ብቻ ሳይሆን ለትግራይ ህዝብ የሚገባውን ምግብና ምግብ ነክ ድጋፍ ለታጣቂው እየመገበ ንጹሃን ትግራውያን በርሃብ እንዲያልቁ እያደረገ ነው። ዘረፋና ሌብነታቸው ገና ከጫካ ጀምሮ ሲዘርፉ የመጡበትን ባህሪ ያሳየ ነው።

ለኢትዮጵያ የሚታገል ሰው ጠላት አድርገው የሚፈርጁ መሆናቸውን የገለጹት አቶ ምዑዝ፤ እሳቸውን ጨምሮ ትግራይ አትገነጠልም ብሎ ሲታገሉ የነበሩትን ሙትና ቁስለኛ አድርገዋል። ስለሆነም የሽብር ቡድኑ በምንም አይነት ሁኔታ ለትግራይ ሕዝብ የማያስቡ ለራሳቸው ብቻ የቆሙ ናቸው። አሁንም ለአንድ አሸባሪ የትግራይ ህዝብ እየተራበ ለራሳቸው ጀኔራሎች በቀን አንድ ፍየል እየተገዛ ይሰጣቸዋል ሲሉም ተናግረዋል።

እንደ አቶ ምዑዝ ገለጻ፤ የትግራይ ህዝብ በርሀብ እያለቀ እነሱ የተቀናጣ ኑሮ እየኖሩ ነው። 27 ዓመት በስልጣን ሲቆይ ለህዝቡ ምንም ያደረጉለት ነገር የለም። በምንም አይነት ባህሪያቸው ለሰላም አስበው የማያውቁ ፍላጎታቸው የትግራይ ህዝብ እንዲያልቅ ነው።

ምዕራባውያን እነዚህ ተራ ሽፍቶች ለሰላማዊ ውይይት የማይመቹ መሆናቸውን መገንዘብ እንዳለባቸው የጠቆሙት አቶ ምዑዝ፤ የሰላም ውይይቱን ከማደናቀፍ አልፈው ጦርነት እስከመክፈት ድረስ የሄዱበት መንገድ የቡድኑን ባህርይ የሚያሳይ ነው ብለዋል። የትግራይ ህዝብም ሆነ ታጣቂው ሃይል ሰላም ማግኘት ከፈለገ እነዚህን አውሬዎች አንቆ ለህግ ማቅረብ እንዳለበትም ተናግረዋል።



# “ሕወሓት የትግራይ ሕዝብን መያዛ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ግለሰብና ተቋም የሕወሓትን ተግባር ሊያወግዝ እንደሚገባም አጽንዖት ሰጥታለች።

“የትግራይ ሕዝብ ስቃይ እየደረሰበት እንደሆነና በቆዳው ምክንያት የዓለም ሕዝብ ተገቢውን ትኩረት አልሰጠውም” በሚል በዓለም የጤና ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ቴድሮስ አድኃኖም የሚቀርበውን ክስ በተመለከተም ሔርሜላ ስትናገር፤ የዓለም ሕዝብ የዶክተር ቴድሮስን ድርጊት ከማውገዝ ይልቅ ዓለም አቀፍ ኃላፊነቱን የሕወሓት ፕሮፖጋንዳ ማሰራጫና ድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ እንዲጠቀም ፈቅዶለታል ብላለች።

የትግራይ ሕዝብ እስካሁን ለደረሰበትና አሁንም እየደረሰበት ላለው ስቃይና መከራ ተጠያቂው ዶክተር ቴድሮስና ፓርቲያቸው ሕወሓት መሆኑንም አብራርታለች።

ዶክተር ቴድሮስ በዓለም ሕዝብ የጤና ጉዳዮች ላይ ከማተኮር ይልቅ ቦታቸውን ለአሸባሪው ሕወሓት ዓለም አቀፍ ድጋፍ ለማሰባሰብ እየተጠቀሙበት መሆኑን አስረድታለች።

እንደ ጋዜጠኛ ሔርሜላ ገለጻ፣ ዶክተር ቴድሮስ ሐኪም ሳይሆኑ የዓለም ጤና ድርጅትን የመሩ ብቸኛው ሰው ናቸው።

ዶክተሩ የዓለም የጤና ድርጅት ኃላፊ ከመሆናቸው በፊት በሀገሪቱ በርካታ ዘግናኝ ግፎችን በመፈጸምና በማስፈጸም ክስ እንደሚቀርብባቸው የተናገረችው ጋዜጠኛ ሔርሜላ፤ ከእነዚህም መካከል ዶክተር ቴድሮስ የጤና ሚኒስትር በነበሩበት ወቅት ሦስት የተለያዩ የኮሌራ ወረርሽኞችን መሸፋፈናቸውና በአማራ ክልል ሴቶችን መካን ያደረጉ ፕሮግራሞች ማስፈጸማቸውን ጠቅሳለች።

በተለያዩ ጊዜ ዜጎች ምርጫና ሌሎችም የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን በተመለከተ ጥያቄዎችን በማንሳታቸው ምክንያት በሕወሓት ሲጨፈጨፉ ዶክተር ቴድሮስ ከፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች አንዱ ነበሩ ያለችው ጋዜጠኛ ሄርሜላ፤ ፓርቲያቸው ለ27 ዓመታት ሀገሪቷን ሲመራ በነበረበት ወቅት ንጹሃን ዜጎች ላይ በርካታ ዘግናኝ ግፎችን መፈጸሙንም ገልጻለች።



# ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያለ ጦርነት መኖር የማይችለው ሕወሓት ለሰላም የተከፈቱትን በሮች ሁሉ እየዘጋቸው እንደሆነና የመከላከያ ኃይላችን ይዞ በቆየባቸው ቦታዎች ላይ አሁንም ጥቃት እየፈጸመ መሆኑን አስታውቋል፡፡ በመሆኑም ሰላማዊ መንገድ እንዳይዘጋ፣ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ሕወሓትን ወደ ሰላም መንገድ ሊያመጣው ይገባል፡፡

የመከላከያ ኃይል የመንግሥትን የሰላም አማራጭ በመያዝ በጥንቃቄ በመከላከል ላይ መሆኑንም መግለጫው አመልክቶ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሰላም ያደረገው ጥረትና የከፈለው ዋጋ ቢኖርም አሁንም መንግሥት በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል የተፈጠረውን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ውሳኔ ማሳለፉን አውስቷል፡፡

በውሳኔው መሠረት የተናጠል ተኩስ አቁም ማድረጉን፣ ለእርዳታ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች እና ቁሳቁሶች ላልተገባ ተግባር መዋላቸውን እያወቀ እንኳን፣ ለሕዝብ ሲባል ወደ ትግራይ ክልል ሰብዓዊ እርዳታ እንዲገባ ሁኔታዎችን አመቻችቷል ነው ያለው በመግለጫው፡፡

የድርድር ዕቅዱን እና ተደራዳሪዎቹን ይፋ በማድረግ፣ በየትኛውም ጊዜ፣ ቦታ እና ጉዳይ ለመነጋገር ዝግጁ መሆኑንም መንግሥት ማስታወቁንም አስገንዝቧል፡፡

ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አሁን በግልጽ እንደታየው ሕወሓት ነዳጅ ዘራፊ ብቻ ሳይሆን ጠብ ጫሪ መሆኑንም

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

አውቆ ማውገዝ እንዳለበት ነው የገለፀው፡፡

ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ “ሁለቱ ወገኖች” ከሚል ፍርደ ገምድል አካሄድ ተላቆ ሕወሓት መንግሥት ወደ ያዘው የሰላም አማራጭ እንዲመጣ ግፊት እንዲያደርግ ጥሪ አቅርቧል፡፡

ይህ ካልሆነ እና ሕወሓት ጥቃቱን የሚቀጥል ከሆነ መንግሥት በሕግ የተጣለበትን ግዴታ ለመወጣት ሲል ማንኛውንም እርምጃ ለመውሰድ የሚገደድ መሆኑን አስታውቋል፡፡

# የትግራይ ሕዝብ መቸገርና መራብ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደ አቶ ነጋሲ ገለጻ፤ቡድኑ በአንድ ጎን ለትግራይ ህዝብ ቆሜያለሁ ቢልም በሌላ ጎን ደግሞ ለትግራይ ህዝብ የተላከውን ሰብዓዊ ዕርዳታና ነዳጅ ይዘርፋል፡፡ ይህ የሚያሳየው አሸባሪው ቡድን ከበረሃ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በትግራይ ህዝብ ችግርና ርሃብ ይነግዳል እንጂ ለህዝቡ አስቦለትና ተቆርቁሮለት እንደማያውቅ ነው፡፡ ሁልጊዜ ለህዝብ ጥቅምና መብት እንደቆመ ያስመስላል እንጂ በተቀራኒው ከትግራይ ህዝብ ጥቅም በሚጻረር መልኩ የቆመ ነው፡፡

አሸባሪው ሕወሓት እራሱ ሲነካ የትግራይ ህዝብ ተነካ እያለ ይጮሃል እንጂ የትግራይ ህዝብ ችግርና ርሃብ ለአሸባሪው ሕወሓት ደስታ መሆኑን ገልጸው፤ቡድኑ ከትግራይ ህዝብ እንደ መዥገር ተጣብቆ ለፖለቲካ ፍላጎቱና ለስልጣኑ ማስጠበቂያ ይጠቀምበታል እንጂ ለህዝቡ ደንታ ኖሮት አያውቅም፤ ቢኖረው ኑሮ ለተቸገረው የትግራይ ህዝብ የተላከውን ሰብዓዊ ዕርዳታ አይዘርፍም ነበር ብለዋል፡፡

መንግስት ችግሩ በሰላም እንዲፈታ ብዙ ተጨባጭ ጥረቶችን ማድረጉን አመልክተው፤በአንድ እጅ ብቻ ማጨብጨብ አይቻልም እንደሚባለው መንግስት የሰላም እጁን ሳያጥፍ አሸባሪው ሕወሓት ጦርነት መክፈቱ እውነትና ሰላም ለአሸባሪው ሕወሓት እንደማይመቸው ያሳያል ብለዋል፡፡

የትግራይ ህዝብ ሰላም ነው የሚያስፈልገው፤ በአንጻሩ አሸባሪው ሕወሓት ለሁሉም ነገር መፍትሄው ጦርነት ነው ብሎ የሚያምን ቡድን ነው፡፡ ለዚህም ነው ከጦርነት ውጪ ሌላ አማራጭ ያለ አይመስለውም ያሉት አቶ ነጋሲ፤ የተዘረጋለትን የሰላም አማራጭ አልፈልግም ብሎ ጦርነት ላይ የሙጥኝ በማለቱም በትግራይ ህዝብ ሞትና ችግር እየቀለደ ያለ ፌዘኛ ቡድን ነው ብለዋል፡፡

ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለአሸበሪው ሕወሓት ሲያደላ የቆየ ቢሆንም አሁን አሁን እውነታውን የተገነዘበው ይመስላል ያሉት አቶ ነጋሲ፤በአሁኑ ጊዜ መንግስት ያደረገውን ጥረት በትንሹም የመጥቀስና አሸባሪው ሕወሓት የፈጸመውን ዘረፋ የማውገዝ ሁኔታ እየታየ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በተለይ በውጭ አገር የሚገኘው የትግራይ ተወላጅ ዲያስፖራ ለትግራይ ህዝብ እውነት የሚያስብ ከሆነ አሸባሪው ሕወሓት በመንግስት የቀረበለትን አማራጭ እንዲቀበል ሊያስገድደው ይገባል ብለዋል።

አሸባሪው ቡድን የትግራይ ህዝብ አንድ ለአምስት በሚለው ሰንሰለት ቢጠረንፈውም፤ የትግራይ ህዝብ በርሃብና በጦርነት ከሚሞት በአሸባሪው ላይ ማመጽ እንደሚኖርበት ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የሽብር ቡድኑ ለጦርነትና ግጭት ካለው ናፋቂነት የተነሳ ጥቅምት 24 ቀን 2012 ዓ.ም የሰሜን እዝ ላይ አሳፋሪ ጥቃት መፈጸሙ ይታወሳል።

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሄት



የሲዳማ ባህላዊ ምግብን ከቤት ወደ አደባባይ ያወጡት የባህል ምግብ ቤት ባለቤት

ገጽ 17



## «የድሮዋን ጠንካራዋን ኢትዮጵያ ለመመለስ 10 ዓመት እንኳን አይፈጅብንም»

- ዶክተር እመቤት ገዛኸኝ

የተወካዮች ምክር ቤት አባልና የጥርስ ሕክምና ክሊኒክ ባለቤት

ገጽ 6



አጂማ ጫጫ የመስኖ ግድብ ፕሮጀክት፤ በውሃ ሃብት የመጠቀም መብት ሌላኛው ማሳያ

ገጽ 14



ካልሻረው ጦርነት ጠባሳ ስር ...

ገጽ 16

## በውስጥ ገጾች

ትዕቢት ውድቀትን ይቀድማል! ገጽ 9

ስማችንን እንኑር ገጽ 11

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# «የድሮዋን ጠንካራዋን ኢትዮጵያ ለመመለስ 10 ዓመት እንኳን አይፈጅብንም»

ዶክተር እመቤት ገዛኸኝ
የተወካዮች ምክር ቤት አባልና የጥርስ ሕክምና ክሊኒክ ባለቤት

አስቴር ኤልያስ

ከአገር የወጡት ገና በለጋ እድሜያቸው ለትምህርት ነው። መዳረሻቸውን ያደረጉትም ኩባ ሳንዲያጎ ከተማ ነው::ወደኩባ የመሄድ አጋጣሚውን ያገኙት ደግሞ የቀድሞ የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት በሆኑት በመንግስቱ ኃይለማሪያም የአገዛዝ ዘመን ነው::ከስድስተኛ ክፍል ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ድረስ በኩባ ቢማሩና እዛው ቢቆዩም  አገራቸው ኢትዮጵያ ለአፍታም ቢሆን ከልባቸው ወጥታ አታውቅም፡፡

እኚህ ሰው፣ ተወልደው ያደጉት ሐረር ነው::በወቅቱ አፋቸውን የፈቱበት ቋንቋ  አደሬኛ ሲሆን፣ ሐረር መድረሳ የሚባል የሙስሊም ትምህርት ቤት ገብተው ቁራን መቅራት ጀምረውም ነበር::የደርግ ዘመን መኮንን የነበሩ አባታቸው የሶስተኛው ክፍለ ጦር አዛዥ በመሆናቸው ከሐረር ወደጭናክሰንና ጅግጅጋ በሚመላለሱበት ወቅት ይዘዋቸው ስለሚሄዱ እንደገና ቄስ ትምህርት ቤት ገብተው የመማር እድል አግኝተዋል::በሀረር ከተማም  የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጀመረዋል::

የዛሬው ‹‹የዘመን እንግዳችን›› ዶክተር እመቤት ገዛኸኝ ይባላሉ። የዶክተር እመቤት የጥርስ ሕክምና ክሊኒክ ባለቤትና የሚናሮል ባለድርሻ እንዲሁም መስራች ናቸው::ብቸኝነትን አጥብቀው ይጠላሉ። ከዚህም የተነሳ በርከት  ያሉ ሰዎች በዙሪያቸው አይታጡም::በተለይ በቤተሰባቸውና በዙሪያቸው ላሉ የቅርብ ወዳጃቸው ሁሉ  ብልሃተኛ፣ አማካሪ እንዲሁም ገበና ሸፋኝም ናቸው::በልጅነት እድሜያቸው አግብተው አራት ልጆች ወልደዋል። በአራስነት ጊዜያቸውን ከስራ ገበታ መራቅ አይሆንላቸውም::የእረፍት ጊዜያቸውን አሳጥረው ወደ ስራቸው ይመለሳሉ። በዚህም አብረዋቸው ለሚሰሩት አርአያ መሆንን ይሻሉ::ዛሬም የስራ ሀላፊነታቸውን የሚወጡት እንደልጅነታቸው ነው::ይህ ንቃት የመልካምነት ስጦታ ነው ብለውም ያስባሉ::

እንግዳችን የአራት ልጆች እናት ሲሆኑ፣ ሁለቱ ልጆቻቸው ዶክተሮች ናቸው::አንደኛዋ ደግሞ በሳይኮሎጂ ሁለተኛ ዲግሪ ያላት ስትሆን፣ አንደኛዋ ደግሞ አርክቴክት ናት:: አዲስ አበባን በቅጡ ያወቋት ከውጭ አገር ተመልሰው ከመጡ በኋላ ሲሆን፣ በአዲስ አበባ  ከተማ ለ30 ዓመት ኖረዋል፡፡

ዶክተር እመቤት፣ በተለይ በ1983 እና 1984 ዓ.ም አካባቢ ጃንሜዳ በሚኖሩበት ሰዓት በኤች. አይ.ቪ ምክንያት ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ ከ12 በላይ ልጆችን ሰብስበው ከልጆቻቸው ጋር አብረው አሳድገዋል::ያሳደጓቸው ልጆችም በአሁኑ ሰዓት ጥሩ ቦታ ደርሰውላቸዋል::በዚህም ደስተኛ ናቸው::ምንም እንኳን ሁሉንም ልጆቻቸውን ያስተማሩዋቸው ውጭ አገር ቢሆንም ሁሉም ተመልሰው አገራቸውን በማገልገል ላይ ይገኛሉ::የዛሬ እንግዳችን እንዲሆኑ የመፈለጋችን ምክንያትም በበጎ ፈቃደኛ ስራ ግንባር ቀደም ተሳታፊ በመሆናቸው ሲሆን፣ በተለይ ወጣቶችን ትኩረት አድርገው በሚሰሩት ስራ ለሌሎች አርአያ እንዲሆኑልን በመፈለግ ነው።  ከእርሳቸው ጋር ያደረግነውን ጭውውት እነሆ  ለንባብ ብለናል::


ፎቶ፡ በገባቦ ገብሬ

**አዲስ ዘመን፡- ዶክተር እመቤት  ብዙ ጊዜ ኢትዮጵያዊነት ደሜ  ነው ሲሉ ይደመጣሉ፤ ምን ለማለት ነው  ከሚለው ጭውውታችን እንጀምር?**

**ዶክተር እመቤት፡-** ኢትዮጵያዊነት ደግነት ነው:: ኢትዮጵያዊነት መራራት ነው::ብዙዎች  የቅርቡን ክስተት በማየት ኢትዮጵያዊነት ደግነት ሊሆን እንዴት ይቻላል ሊሉ ይችላሉ:: ኢትዮጵያዊነት ግን ደግነት ነው፤ ያለውን መቋደስ ነው:: አንድ የቤተሰብ ኃላፊ የሆነ ሰው በአማካይ 13 ሰዎችን ሊቀልብ ይችላል:: ይህ ቁጥር የልጆቹ ብቻ ላይሆን ይችላል::የእህትና የወንድም ልጅ አሊያም የአክስትና የአጎት ሌላም ሊሆኑ ይችላሉ:: እነዚህን ሁሉ አንድ ሰው ቢኖረውም ባይኖረውም፣ ተበድሮም ይሁን ተለክቶ ያስተዳድራል::ይህ አይነቱ አኗኗር የት አገር ይገኛል ቢባል ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ነው ብዬ በድፍረት ልናገር እችላለሁ::በሌላው አገር ስትኖሪ በመኖሪያ አፓርትመንት ውስጥ ያለው ጎረቤትሽ ምን እያደረገ ስለመሆኑ የምታውቂው ነገር የለም::አንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሰብስቦ ሲቀልብና አስጠግቶ ሲያኖር ኖሮት አይደለም፤ የኢትዮጵያዊነት ደም በውስጡ ስላለና እሱ ነገሩ ስለሚያስገድደው  ነው::እኔም ይህ አብሮነትና መረዳዳት በደሜ ውስጥ አለ ብዬ አምናለሁ::

**አዲስ ዘመን፡- ሕጻናትን እንዲሚረዱና እንደሚያሳድጉ ሰምቻለሁ፤ ህጻናቱንስ ከየት አምጥተው ነው የሚረዷቸው?**

**ዶክተር እመቤት፡-** ሕጻናትን ከማሳደግ አኳያ ድጋፍ ማድረግ ወሳኝ ነው:: ድጋፉንም በሁለት አይነት መንገድ ማድረግ ይቻላል:: አንደኛው ለሕጻናቱ ባለቡት ቦታ ድጋፍ ማድረግ ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ በጉዲፈቻ በመውሰድ ማሳደግ ነው:: ሁለቱም መልካም የሆኑ ስራዎች ናቸው::

ነገር ግን በጉዲፈቻ መልኩ ከሚወሰዱ ሕጻናት መካከል ጤነኛውም እንዳለ ሁሉ ጤናው የተጓደለ ሕጻን አለና እነርሱንም ልክ እንደጤነኞቹ ሁሉ የሚወስዳቸው ሰው እምብዛም አይታይም::ከዚህ አኳያ እኔም ሆንኩ ሌሎቹ ከሜሪጆይ ሕጻናትን ለማሳደግና ለመደገፍም በምንፈልግበት ጊዜ ጤነኛውንም ጤናው የተጓደለውንም ብንወስድ መልካም ነው:: እኔ ያደረኩት ነገር ቢኖር ከማሳድጋቸው 21 ሕጻናት በተጨማሪ የጤና እክል ያለባቸውን አምስት ሕጻናትን መውሰድ ነው::ይህ የራሱ የሆነ መልዕክት ይኖረዋል ብዬ አስባለሁ::ጤነኛ እና ቆንጆ ልጅ ነው ያልነውን መርጠን መውሰዱ ብዙዎች ሊያደርጉት የሚፈልጉት ይሆናል::የጤና እክልም ያለበት ሕጻን የእግዚአብሔር ፍጡር እንደመሆኑ እርዳታችን ሁሉ ከፈጣሪያችን ጋር ሊያቀራርብ የሚችል መሆን አለበት ብዬ አምናለሁ::

**አዲስ ዘመን፡- የሚያሳድጓቸው አምስቱ ሕጻናት ምን አይነት የጤና እክል ያለባቸው ናቸው?**

**ዶክተር እመቤት፡-** ሕጻናቱ በተለምዶ የሚጥል በሽታ፣ የአዕምሮ ዝግመት ያለባቸው የአዕምሮ ሕሙማን ናቸው:: በእርግጥ እነዚህ ወላጅ ያላቸው ቢሆኑም ወላጅ ከአቅሙ በላይ በመሆኑ በሜሪጆይ እንዲረዱ የተሰጡ ሕጻናት ናቸው:: እነዚህን አምስቱን ከ21 ጋር የቀላቀልኳቸው ለትውልድ ትምህርት ይሆናል በሚል ጭምር ነው::የምንረዳው የጤና እክል ያለበትንም ጭምር እንጂ ጤነኛ የሆነውን ብቻ መርጠን መሆን የለበትም::እነዚያንም ማስታወሱ መልካምነትን ያገዝፋልና ይህ ለሌሎች ትልቅ ትምህርት መሆን የሚችል ነው::

ሰዎችን የምትረጂው፣ የምትወስጂውና የምትደግፊው በማንነታቸው ላይ ተመስርተሽ መሆን የለበትም:: መረዳት ያለባቸው ሰው በመሆናቸው ነው:: በሚጥል በሽታ የሚታመምን  ሕጻን ወስዶ ማሳደጉ ዋጋ ያስከፍላል::በዚህ አይነት ሁኔታ ግን ብዙዎች መቸገርን አይመርጡም:: ጤነኛውን ልጅ ወስዶ ማሳደጉ ለታይታ ‹እየረዳሁ ነው› የሚል ስሜት እንዲኖረን ያደርገን ይሆናል::ያንንስ የጤና እክል ያለበትን ማን ያሳድገው? ራስን ከሕሊና ተጠያቂነት ለማሸሽ መሞከሩ መልካም አይሆንም:: እኔ ከሜሪጆይ የጤና እክል ያለባቸውን  ሕጻናት ጠይቄ  ስወስድ የመጀመሪያዋ ልሆን እችላለሁ::ስለሆነም በተለይ ባለሀብቶች ገንዘብ ኖሮን ለቅንጦት ከምናውለው ይልቅ በእንዲህ አይነት ችግር ውስጥ ላሉ ድጋፍ ማድረጉ ደስተኞች እንድንሆን  ያደርጋል::

**አዲስ ዘመን፡- እንደማንኛውም በጎ ፈቃደኛ ሰው የመርዳቱ ፍላጎት  ኖሮት  የጤና እክል ያለባቸውን መርጠው ለመውሰድ ሲነሳሱ የገጠመዎት ፈተና ይኖር ይሆን?**

**ዶክተር እመቤት፡-** ‹በጎ› የሚለው ቃል በራሱ የቅዱስ መጽሐፍም የቁራንም አካል ነው::ያንን በጎነት ለማድረግ ስትሄጂ ከውስጥ  በመነሳሳትና በእምነት ነው ማድረግ ያለብሽ::ስታገኚም ለይስሙላ መሆን የለበትም::ለመደገፍ ስናስብ የጤና እክል ካለበት ይልቅ ጤነኛ ወደ ሆነው ነው መሄድ የምንፈልገው::ወይም ደግሞ በሌላ ቋንቋ እነዚህን እናገልላለን::የጤና እክል ያለባቸውን ሕጻናት መውሰድ ምቾት ይነሳናል፤ አሊያም ተጨማሪ ወጪን ይጠይቃል ስለሚባሉ ልጆቹ የማንም ምርጫ ሳይሆኑ ይታለፋሉ::

> **ፈተናን ለመጋፈጥ መዘጋጀት መልካም ነው፡፡ ድህነትን ለመዋጋት ብርቱዎች መሆን አለብን፡፡ በሰው አገር መኖር  ምንም አይነት ነጻነት አይሰጥም፡፡ በአገራችን እርስ በእርስ ተረዳድተን ፈተናን መሻገር እንችላለን፡፡ በጎነት የሁላችንም ድርሻ ነው እንጂ የአንድ ሰው አይደለም**

ለምሳሌ እኔ  በጀት የማደርገው ዓመታዊ ወጪያቸው ላይ ነው::በተለይ የሕክምና ወጪያቸውን እሸፍናለሁ::ምክንያቱም ትልልቅ የጤና ችግር ያለባቸው ናቸው ::ከዚህ ባለፈ ደግሞ የእነርሱን ችግር ለማጣጣም ስል ነው::ምናልባትም የጤና እክል ያለበትን ልጅ የወለደች እናት ልጇን  አሳልፋ ለመስጠት የተገደደችው የበኩሏንና የምትችለውን ሁሉ አድርጋ ሊሆን ይችላል::ደግሞም የሚሆነው ይኸው ነው::ይህ ደግሞ የሁሉም ሕመም ሊሆን ይገባልና የየበኩላችንን ማድረግ አለብን እላለሁ::

እኔ በበኩሌ ልጆቹን ከመርዳት ባለፈ አንድ የገባሁት ቃል አለ::ይኸውም እድሜዬ ገፍቶ ምናልባት በሕይወት ካልኖርኩ በሚል በዚህ ጉዳይ ልጆቼን በተለይም ትልቁ ልጄን የጤና እክሉ ያለባቸውን ልጆች ልክ እንደ እኔ ሆኖ የመደገፉን ጉዳይ እንዲያስቀጥል በሚል አስፈርሜዋለሁ:: ይህን ያደረኩት የግድ ልጄ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን ትውልድ እንዲቀባበለውም ስላሰብኩ ጭምር ነው:: ልጆቹን ለልጄ አደራ ስል ቀጣይ ትውልድ ውስጥ የምታስቀምጪው አንድ አይነት የመተጋገዝና የመደጋገፍ ባህል እንዲኖርም በማሰብ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- አንዳንድ እናቶች የጤና እክል ያለበትን ልጃቸውን ከአቅም በላይ ሲሆንባቸው አሳልፈው ለድርጅት ይሰጣሉ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ሲሸሽጓቸው ይስተዋላሉ፤ እርስዎ 26 ልጆችን ይረዳሉ፤ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ አምስቱ የጤና እክል ያለባቸው ናቸውና ለሌሎች ትምህርት ይሆን ዘንድ በዚህ ጉዳይ ምን ማስተላለፍ ይሻሉ?**

**ዶክተር እመቤት፡-** የእኛ የኢትዮጵያውያን ደም እንዳልኩሽ መሰረቱ ደግነት ነው የሚል ጽኑ አቋም አለኝ::አሁን በአጭር ጊዜ የተረሳን የማንነት ጥያቄን ትተን ያለፈ ነገራችንን ስናይ እንደ አገር ኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይነቷ የሚዘነጋ አይደለም::

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ



ኢትዮጵያዊነት ማለት የእምነት ቤት ማለት ነው::ኢትዮጵያ ማለት በየትኛውም ኃይማኖት ውስጥ ፈጣሪ የሚመሰገንባትና የማይረሳባት አገር እንደማለት ነው::በኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉም እምነቶች ተከባብረው ይኖሩባታል::የኢትዮጵያውያን ደም ደግና በጎ አድራጊ ነው፤ ኢትዮጵያዊነት የሚለካው አሁን ጊዜ ባመጣው ከስተት አይደለም::የጥንት አባቶቻችን ወግ አብሮነትንና መተሳሰብን ነው የሚያስተምረን::እኔ በግሌ የእዛ የኢትዮጵያ ደም አካል ነኝ ብዬ አምናለሁ::

እኔን ብትወስጂኝ እናቴ ሙስሊም ናት፤ አባቴ ደግሞ ክርስቲያን ነው::የዚህ ድምር ውጤት ነኝ::በመሆኑም ኢትዮጵያ የመልካምነትን ሕይወት የዘራችልኝ አገር ናት::ኢትዮጵያ ማንነቴን ያደመቀችልኝ አገር ስለሆነች የምኖርባት ደስ ብሎኝ ነው::በጎነት ደግሞ የኢትዮጵያውያን መገለጫ በመሆኑ ለማንም አሳልፈን የማንሰጠው መልካሙ እሴታችን ነው::ይህንንም አጠንክረን ልንይዘው ይገባል::እርግጥ ነው በአሁኑ ወቅት ብዙ ፈተና እና ተግዳሮት የተፈራረቀብን ጊዜ ነው::ብዙም የጎደለብን ነገር አለ::በጉድለታችን ምክንያት የምናጠፋው ጥፋት ኢትዮጵያዊነታችንን አያበላሸውም::እናም እርስ በእርስ እንደጋገፍ ባይ ነኝ::

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያውያን አንዱ ሌላውን እየረዳና እየደገፈ ነው የመጣው፤ ይህ ግን አሁን ላይ ውልክፍክፍ ያለ አይመስልዎትም? እንዴትስ ልናቃናው እንችላለን?**

**ዶክተር እመቤት፡-** አዎ! ኢትዮጵያዊነት በብዙ መልኩ ተዛንፏል::ይሁንና አይታወቃችሁ እንደሆነ እንጂ አሁን አሁን ለውጦች አሉ::ቀላል ምሳሌ ብጠቅስልሽ ‹‹ድንቅ ልጆች›› በሚለው መርሃግብር ላይ አዘጋጁ እሸቱ በሚያቀርባቸው ልጆች እጅግ በጣም ነው የምደነቀው::በተለይ ደግሞ አዕምሯቸው በምን ያህል መጠን እየተቀየረ ያሉ ልጆች እንዳሉ ሳይ በተስፋ እሞላለሁ::ትውልድም እየተቃና ነው ብዬ አስባለሁ::

ድሮ ግብረገብ እንማራለን::በየትኛውም ትምህርት ቤት ቅዱስ መጽሐፍንና ቁራንን የሚከለክል መንግስት የለም::ስለዚህ በትውልድ መካከል ቢያንስ ፈሪሃ እግዚአብሔር አለ::በዚህ እሸቱ በሚያዘጋጀው መርሃግብር ያስተዋልኩት ነገር ቢኖር ማንነታቸውን አሳምረው የሚያውቁ ሕጻናት እንደሆኑ ነው::እሸቱ በልጆች ላይ እየሰራ ያለው ስራ ድንቅ ስራ የሚያስብለው ነው::ትልቅ ውለታም እየዋለልን ነው::አሁን ባለው ሁኔታ ያሉ ልጆች አገራቸውን የሚያደንቁ ሆነው አግኝቼያቸኋለሁ::ልጆች ከጥቂት ዓመት በፊት ሲታዩ የነበረው ከአገራቸው ይልቅ የሌላ አገር አድናቂ ሆነው ነው::ስለዚህ አሁን ትውልድ እየተቃና ነው ብለን ብናስብ መልካም ነው እላለሁ::

በአሁኑ ወቅት እንደ አገር ዓባይን የመሰለ ግድብ ተገድቧል::በዚህ ታላቅ ፕሮጀክት ልጆቹ ትልቅ ትምህርት ይማራሉ::በፊትም በሌሎች አገሮች በአይነቁራኛ የምንታየው በጥንካሬያችን ነው::እኔ በግሌ በጣም እሰጋ የነበረው የዓባይ ግድብ ይቀጥላል ወይስ አይቀጥልም በሚለው ላይ ነበር::ያ ሁሉ ተግዳሮት ታልፎ እዚህ መድረስ ተችሏል::ይህ ደግሞ ትውልዱን ቆራጥነትን እና ብርታትን የሚያስተምር ነው::

እኛ አሁን የድሮዋን ጠንካራዋን ኢትዮጵያ ለመመለስ 10 ዓመት እንኳ አይፈጅብንም::ምክንያቱም እየተሰራ ያለው ነገርና እየተሰራበት ያለው ነገር ቀላል አይደለም::የተወላገደውን ማቃናት ደግሞ የሁሉም ኃላፊነት መሆን አለበት::

በእኛ አገር ያሉ ወጣቶች አንገታቸውን ደፍተው ሲሄዱ ሳይ በብዙ ያመኛል፤ እንደሌላው አገር ወጣቶች አይደሉም::እጅግ መልካም ስነ ምግባር ያላቸው ናቸው::እንዲያውም ወጣቶች በተቸገሩበት ያህል ልክ አልጎዱንም ብዬ አስባለሁ::አሁን መመለስ የምንችለበት ሰዓት ላይ እንገኛለን::

**አዲስ ዘመን፡- ወጣቱ የተቃና ይሆን ዘንድ ሕጻናቱ ላይ መስራት ይጠበቃልና እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**ዶክተር እመቤት፡-** ዋናው ነገር ከቤት ይጀምራል::አንዳንዴ ወላጆች ልጆቻቸውን ‹ውጭ አገር ነው እንጂ ኢትዮጵያማ አትማርም› ሲሉ ይደመጣሉ::‹ቆይ ውጭ አገር እልክሃለሁ› ይሏቸዋል::ቢያንስ እንኳ እዚህ የሌለ ትምህርት ቢሆን ግድ የለም::እንደዚያ ሆኖ እንኳ ‹ልጄ ተምረህ መመለስ አለብህ› ብለው ቢልኳቸው እሰይ የሚያስብል ነበር::ልጆቻቸውን ወደ ውጭ አገር ሲልኳቸው ‹ተምረህ ትመለሳለህ›› ብለው ቢልኳቸው ተምረው ይመለሱ ነበር::

የእኔን ተሞክሮ ብነግርሽ ከኢትዮጵያ የወጣሁት በበቀድሞ የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት መንግስቱ ኃይለማርም ጊዜ ነበር::በወቅቱ ፕሬዚዳንት መንግስቱ ‹‹ተምራችሁ ወደአገራችሁ ትመጣላችሁ›› ብለውን ነው ወደኩባ የላኩን::በውጭ አገር ቆይታችን መቼም ቀን ቢሆን ከአገራችን ውጭ ተመኝተን አናውቅም::ከእኔ ጋር የነበሩ ልጆች ተምረው ወደአገራቸው በመመለሳቸው በአሁኑ ወቅት በጳውሎስ፣ በምኒልክም ሆነ በሁሉም ስፍራ ያሉ በሙያቸው ‹አንቱ› የተባሉ ናቸው::

ምንም እንኳ በውጭ አገር ኩባ የተማርን ብንሆንም በትምህርት ቤታችን ውስጥ የተማርነው ስለኢትዮጵያ መዝሙር እንድንዘምር ተደርገን ነው::የመዝሙሮቹ ግጥሞች ዛሬም ድረስ የማይረሱኝ ናቸው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ዶክተር ከመዝሙሩ ግጥም በጥቂቱ ያስታውሱናል?**

**ዶክተር እመቤት፡-** ያውም ከነዜማው ነዋ!

‹‹ጊዜ ቢለያየን ባልኖር አጠገብሽ፣

ቃል ኪዳን አለብኝ ፈጽሞ ላልረሳሽ...››

እያለ የሚቀጥል መዝሙር ነው::ውጭ አገር ሆነን የተማርነው የኩባን አገርና የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሰቅለን ነው::መንጌ በወቅቱ ሲልከን ‹አማርኛ እንዳትረሱ›› ብሎናል::የሄድነው የተለያየ ባህሪ ያለን ልጆች ነን::የተወሰንን ደግሞ የሙት ልጆች ነን::በወቅቱ እንዘምር የነበረው መዝሙር በውስጣችን የታተመ በመሆኑ ከአገራችን ውጭ ምንም አያስመኘንም ነበር::እኛ በወቅቱ ትምህርት የጨረስን ሰሞን ወደአገራችሁ እንዳትገቡ የሚሉ ነበሩ፤ ነገር ግን ከአገርሽ ውጭ ወዴት ትሄጃለሽ? የተረዳሽው እውነት ቢኖር ተምሮ መመለስን ነው::በሰልፍ ላይ ሁሌም የሚዘመረው መዝሙር በራሱ አገርሽን እንድትናፍቂ የሚያደርግሽ ነው፡፡

እኔ በወቅቱ በጣም ልጅ ነበርኩ::ከአገር የወጣሁት ገና ከአምስተኛ ክፍል ወደ ስድስተኛ ክፍል ተዛውሬ ባለሁበት ጊዜ ነው::ከስድሰተኛ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ትምህርቴን የተማርኩት እዚያው ኩባ ነው::ኩባ ደግሞ የትምህርት አሰጣጡ በጣም ግሩም ነው::አንድ አስተማሪ በትክክል ባያስተምረን አምስት ዓመት ሙሉ ከስራው ሊታገድ ይችላል::ከኩባ በኋላ ለአጫጭር ኮርሶችና ለትምህርትም ጭምር ወደተለያዩ አገሮች የመሄድ እድሉ ነበረኝ::በዚህ ሁሉ አገሮች መካከል ግን መቼም መልሼ የማላገኛት አገር ብትኖር ኢትዮጵያ ብቻ መሆኗን አስተውያለሁ::ኢትዮጵያ በእኔ አስተሳሰብ አቻ ያላገኘኋት አገር ናት::ከአገር ወጥተሽ ልትማሪ ትችያለሽ፤ ነገር ግን ጥለሻት መሄድ አይገባም::አሁን ባለው ትውልድ ላይ ካልተሰራ ችግር ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ቀደም ሲል በአጼ ኃይለስላሴ የነበረው ትውልድ ለትምህርት ወደ ውጭ አገር ሲላክ ተመልሶ መጥቶ አገሩን የሚያገለግል እንዲሆን ተመክሮና ተዘክሮ ነው፤ ከዚህ አንጻር የአሁኑ ትውልድ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**ዶክተር እመቤት፡-** አዎ! ይህን ነው የምለው:: ለአሁኑ ትውልድ ታላቅነታችንን ካላስተማርንና አደራ ካልሰጠን ትውልዱ አደራውን ለመወጣት አይችልም:: በወላጆችሽና በቅርብ ዘመዶችሽ እንድትሸሺ ከተመከርሽ ትሸሺያለሽ::በጃንሆይ ጊዜ ከአገር ወጥቶ እንዲማር የተደረገ ሁሉ ተምሮ መጣ እንጂ የቀረ የለም ማለት ይቻላል::በደርግ ጊዜ ወጣቱ ላይ ትንሽ አደጋ ደረሰ::በመሆኑም ለሽሽት ምክንያት ሆነ::ኢህአፓን ጨምሮ በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች ሲፈጠሩ በፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ብዙ ጊዜ የሚሳቡት ወጣቶች ናቸውና በነበረው ሁኔታ ለሽሽት ምክንያት ሆኗል::እስካሁንም እሱ አይነት ፍርሃት ያለቀቀው አለ፡፡

በዚህ ምድር ላይ የምንፈጠረው አንዴ ነው::ሞትን ፈርተሽ አገር አትለቂም::በአገር መሞት ደግሞ ክብር ነው::ስለዚህ የሚደርሰው የፖለቲካ ተጽዕኖ ጊዜያዊ ነውና አገር ትበልጣለች ባይ ነኝ::ትልቁ ግን የትምህርት ስርዓቱ ነው የተበላሸው ባይ ነኝ፤ ቻይ እንድንሆን አላደረገንም:: ሕይወት የምትደበድብሽ በቦክስ ነው፤ ያንን ጡጫ እንዴት መከላከል እንዳለብን መማር አለብን::ያንን ግን አላስተማሩንም::ከዚህ ውጭ ኢትዮጵያውያን በማንነታችን የምናፍር አይደለንም፤ ምክንያቱም በማንም አገር ቅኝ አልተገዛንም::ከፖለቲካ ረብሻ ሌላ ያባረረን ድህነት ነውና ጠንክረን ልንሰራ ይገባል::ደግሞም በሰው አገር ኢትዮጵያውያን በዝተናልና በቃን::ፈተናን ለመጋፈጥ መዘጋጀት መልካም ነው::ድህነትን ለመዋጋት ብርቱዎች መሆን አለብን::በሰው አገር መኖር ምንም አይነት ነጻነት አይሰጥም::በአገራችን እርስ በእርስ ተረዳድተን ፈተናን መሻገር እንችላለን::በጎነት የሁላችንም ድርሻ ነው እንጂ የአንድ ሰው አይደለም::እኔም እያደረኩ ያለሁት ኃላፊነቴን መወጣት አለብኝ ብዬ ስለማምን ነው::ለዚህም ነው አንቺ በጎ አድርገሻል ስባል ሁሉም ሰው በጎ ነው የሚል መልስ የምስጠው::

**አዲስ ዘመን፡- እርሶ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ እየተሳተፉ ስለመሆንዎ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን አማካይነት ሰምተናል ። የሰሩት በጎ ስራ ለሌላውም አርዓያ ይሆናሉና እስኪ ከአንደበትዎ እንስማው?**

**ዶክተር እመቤት፡-** አሁንም ደግሜ የምነግርሽ ነገር ቢኖር በጎነት የዶክተር እመቤት ስራ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያውያን ሁሉ ስራ ነው::ኢትዮጵያዊነት የሚገለጸው በዚህ ነው::እኔ ሳድግ አዳሪ ቤት በመሆኑ አብሮ መኖርን ተምሬያለሁ::የእኔን ወላጆች ጨምሮ በሁሉም ወላጆች ዘንድ ደግነት ነበር::ስለዚህም ነው ጉዳዩ የእኔ ብቻ ሊሆን የማይችለው፡፡

ቀን በቀን በማያቸው ክስተቶች ውስጥ ልቤን የሚሰብሩ ነገሮች ያጋጥሙኛል::ከታካሚዎች ብጀምርልሽ እንደ ሀኪም ሙብት ስላለኝ ስለራሳቸው የምጠይቃቸው በጥልቀት ነው::በዚህ ውስጥ ግን ግላዊ የሆኑ ችግሮቻቸውን በድንገት እስማለሁ::ሰምቼም የሁሉም መፍትሔ መሆን ባለመቻሌ በጣም እጨነቃለሁ::ይህ አይነቱ ጉዳይ ግን የእኔ ባህሪ ብቻ ነው ማለት አልችልም፤ ምክንያቱም ብዙ ኢትዮጵያውያን ውስጥ ያለ ነው::

ለምሳሌ እኔ በምሰራበት የጥርስ ሕክምና የጽዳት ሰራተኛ የሆኑት ሁሉ ጤና መኮንን፣ ነርስ ብሎም ሐኪም ሆነዋል:: እንዳጋጣሚ ሆኖ አንዳቸውም ጥለውኝ አልሄዱም፤ ነገር ግን ወደየትኛም ቦታ ቢሄዱም ቅር አልሰኝም፤ ምክንያቱም እዛም ሄደው የሚያገለግሉት ኢትዮጵያውያኑን ነው።

በሌላ በኩል ወጣቶችን በብዙ መልኩ ማገዝ ያስደስተኛል:: በተወሰነ መልኩም ለመርዳት እሞክራለሁ:: ብቻዬን ሆኜ የኢትዮጵያ ወጣት ወደአንድ ቦታ ማድረስ ባልችልም ተደራሽ መሆን ለሚችለው የበኩሌን እሞክራለሁ::እሱ ግን የሚያስደንቅ አይደለም::እንደ እኔ ከሆነ እያንዳንዱ ባለሀብት አንድ ለትውልድ የሚጠቅም ማስታወሻ እየተወ ማለፍ አለበት የሚል እምነት አለኝ::በሌላ በኩል ከመንግስት ጎን በመሆን አገለግላለሁ:: በተለይ በክፍለከተማዬ የሚጠበቅብኝን ሁሉ በማድረግ እየተንቀሳቀስኩ ነው ። ልደታ ወደሚባለው አካባቢ ለወጣቶች ሜዳ እየሰራን ነው::

**አዲስ ዘመን፡- የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ነዎትና እስኪ ስለእሱ እናንሳ? ምክር ቤት ገብቼ አሳካዋለሁ ብለው ያሰቡትንስ እያሳኩ ነው ማለት ይቻላል?**

**ዶክተር እመቤት፡-** በምክር ቤቱ የማሕበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ጸሐፊ ነኝ::በመሆኑም ማህበራዊ የሆኑ ጉዳዮች በሙሉ ይመለከቱኛል::በዚህ ውስጥ ደግሞ መልካምነትን እንዳስተምርበት እድል ይሰጠኛል::የቋሚ ኮሚቴ ኃላፊዋ ወይዘሮ ዘይነብ ሽኩር በጣም ጠንካራ በመሆናቸው ለሰው ያልተገለጹ ብዙ ነገሮችን እየሰራን ነው፡፡

ሕልሜ ነው ብዬ አስብ የነበረው የዓባይ ግድብ ነው::ይህ ደግሞ ያለምንም ጥርጥር ወደስኬት ማማ የመጣ ጉዳይ ሆኗል::በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ቅድመ ንግግሬ የነበረው ሌላው ቢቀር እስኪ ዓባይን እንይ የሚል ነበር::ሌላው ደግሞ እየተከናወኑ ያሉ ትልልቅ አገራዊ ፕሮጀክቶች ጠቀሜታቸው ለህዝብ በመሆናቸው እሱም ላይ እየታየ ያለውስኬት አስገራሚ ነው::ሕዝቡም ለምርጫ እድል የሰጠን እነዚህን ፕሮጀክቶች እንዲሁም የተማሪዎች የምገባ መርሃግብር ላይ ተደግፈን ባደረግነው ንግግር እንጂ እነሱን መርሃግብሮች ወይም ፕሮጀክቶች እኛ ተመራጮች ሰርተናቸው አይደለም::ምክንያቱም በምርጫ ቅስቀሳው ወቅት ፍቀዱልንና እነዚህንም ፕሮጀክቶች እናስቀጥል ብለን ነው ለህዝቡ ስንናገር የነበረው::

**አዲስ ዘመን፡- እንደምክር ቤት ተመራጭነትዎ ወጣቱን ምን መምከር ይሻሉ?**

**ዶክተር እመቤት፡-** ከአንድ መንግስት ቢሮክራሲ መጥፋት አለበት ብዬ አምናለሁ::መማር እየፈለገ ያልተማረ እንዲሁም ተምሮም የተቀመጠ ወጣት አለ::ይህን ጉዳይ ለማስተካከል በመጀመሪያ ከወጣቱ ዘንድ ተነሳሽነቱ መምጣት አለበት::ስራ ሳይንቅ እየሰራ መማር ይችላል::በእርግጥ ደግሞ ወጣቱ አሁን የሚታየው ጭላንጭል የሆነ ነገር አለና ተስፋ የሚቆርጥ አይመስለኝም:: ሌላው ደግሞ የዓባይ ግድብም ሊነጋ ነው፤ ደርሼላቸኋለሁ እያለን ነው::ይህን የሚለው ለትውልዱ ነው::ከዚህ ፕሮጀክት ሌሎች ፕሮጀክቶችን መስራት እንማራለንና ለወጣቱ ብዙ ተስፋ አለ::

አገራችን ያልተነካች እንደመሆኗ ብዙ ማዕድናትን የያዘች ናት፤ ይልቁኑ ለዚህ ጉዳይ በዘርፉ ብቁ ለመሆን በትምህርት ዝግጁ ልንሆን ይገባል::እኛ በቅኝ ስላልተገዛን ብዙ ነገራችን ያልተነካካ ነው::ስለዚህም ወጣቱ በዛ ለመሳተፍ ተስፋ በማድረግ አይኑን መክፈት መቻል አለበት::ያሉንን ማዕድናት በአግባቡ መጠቀም እንድንችል በዘርፉ ኮሌጅ መከፈትና መጠናከር አለበት::መማር ያለበት ዶክተር፣ ኢንጂነር ብቻ መሆን የለበትም፤ የአገራችንንም ማዕድን ማውጣት የሚችል ኃይል እንዲኖረን በዘርፉ መማር መልካም ነው::ሁልጊዜ ፈረንጅ መለመን አይገባም::

በአጠቃላይ ትውልዱ አደራ የምለው ጉዳይ በቀጣናውም በአህጉሩም ደረጃ ምንም እንኳ ብዙ ተግዳሮት ቢኖርብንም የቀድሞ የበላይነታችን እናስጠብቅ::ይህ ደግሞ የሚጀምረው ወደእርሻው ፊታችንን በማዞርም ጭምር ነው፤ የተማረ አርሶ አደር መሆን ክብር ነው::የኑሮ ውድነትን ሰርተን ነው መቀየር የምንችለው እንጂ የፈረንጅ እጅ ጠብቀን አንዘልቀውም::ወጣቱ አንድ እንዲያውቀው የምፈልገው ነገር ቢኖር በሌላው ዓለም ላይ ያለው ወጣት ስምንት ሰዓት ብቻ ስለሰራ ሳይሆን ከ12 እስከ 16 ሰዓት በመስራት ነው ኑሮው የተሻሻለው፡፡

ሌላው ደግሞ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሰራተኛ በጠቅላላ አንድ ስራን ብቻ ሰርቶ ኑሮን ለማሸነፍ መታገልን ማቆም አለበት:: ተጨማሪ ስራዎችን ለመስራት ዝግጁ መሆን አለበት:: በመንግስት ደግሞ ይህ ጉዳይ የተሳለጠ እንዲሆን ቢያንስ የሌሊት የትራንስፖርት አቅርቦትን ማመቻቸትና የሰላሙን ሁኔታ ማስጠበቅ ይኖርበታል::የጨለማውም ጊዜ አብቅቶ ሌሊቱ በብርሃን ሊተካ የግድ ይላል::ምናልባትም ከዚህ በኋላ መብራት በፈረቃ ወደሚለው ጉዳይ እንገባለን ብዬ አላስብም::ይህ ከሆነ ቀን በነርስነት ሙያ ስትሰራ የቆየች ልጅ ማታ ቢያንስ እስከ አራት ሰዓት ሱቅ መሸጥ ትችላለች::ቤታችን ውስጥ እስከ አራት ሰዓት ድረስ ወይ ቡና ስንጠጣ አሊያም በሆነ ባልሆነው ጉድ ጉድ ስንል እንቆያለን::ይህ ካልሆነ በማማረር ኑሯችንንም ሆነ አገራችንን ከፍ ማድረግ አንችልም::ሰው በስራ ሲወጠር አላስፈላጊ የሆኑ የማህበራዊ ትስስር ገጽን በማየት ለነቀፋ ወይም ለምሬት አይዳረግም እላለሁ::

**አዲስ ዘመን፡- የሕይወት ተሞክሮዎንና አርዓያነትዎን ለአንባቢዎቻችን ስላጋሩን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**ዶክተር እመቤት፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

## ማህደረ ጤና

# ታካሚዎችን ከወጪና እንግልት የታደገ ማዕከል

አስናቀ ፀጋዬ

ከዓለም ጤና ድርጅት ጋራ የላንሴት ግሎባል ኮሚሽን ኦን ቪዡዋል ኬር የሚባለው ኮሚቴ በየአመቱ ሪፖርት ያወጣል:: በቅርቡ ባወጣው ሪፖርት መሰረት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ1 ቢሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች የዕይታ ችግር እንዳለባቸው አረጋግጧል:: በኢትዮጵያም ከእይታ ጋር በተያያዘ ችግር ያለባቸው ሰዎች ቁጥር ከፍተኛ ስለመሆኑና በተለይ ደግሞ አገሪቷ በትራኮማ የአይን ህመም ከዓለም ቀዳሚዋ እንደሆነች ይነገራል::



በህብረተሰቡ በኩል ለአይን የሚደረገው ጥንቃቄ ዝቅተኛ መሆን፣ ጥራት ያለውና ሁሉንም ተደራሽ ያደረገ የአይን ህክምና ተቋማት እንደልብ አለመገኘትና የአይን ህክምና ባለሙያዎች ቁጥር አነስተኛ መሆን ደግሞ ለችግሩ መባባስ አይነተኛ ሚና ይጫወታል:: በአሁኑ ጊዜ ግን በመጠኑም ቢሆን የአይን ህክምና ተቋማትና የዘርፉ ባለሙያዎች ቁጥር እየጨመሩ መምጣታቸው ለብዙሃን ተስፋ ሰጥቷል:: ለዚህም ከሰሞኑ በአለርት ሆስፒታል የተከፈተው የአይን መነፅር ማምረቻ ማእከል ተጠቃሽ ነው::

ዶክተር ሰለሞን ቡሳ በአለርት ሆስፒታል የአይን ህክምና ክፍል ኃላፊ ናቸው:: እርሳቸው እንደሚሉት የአይን ህክምና ክፍል በአለርት ሆስፒታል ሲቋቋም በአንድ ክፍል ውስጥ በአንድ ሀኪም ብቻ ነበር:: የአይን ህክምና ክፍሉ ሲጀመር ደግሞ ለስጋ ደዌ ህመምተኞች ተብሎ ነበር:: በዚህ ጊዜ የስጋ ደዌ ታማሚዎችን አይናቸውን ለማዳን በሚል ሲ ቢ ኤም የተባለው የጀርመን ግበረ ሰናይ ድርጅት አንድ ጀርመናዊ የአይን ስፔሻሊስት ልኮ የአይን ህክምናው በአለርት ሆስፒታል እንዲጀመር ተደረገ::

ዛሬ ላይ የአይን ህክምና ክፍሉ እየተስፋፋ ሄዶ ለመላ አገሪቱ ከፍተኛ የአይን ህክምና አገልግሎት የሚሰጥ ለመሆን በቅቷል:: ይህ የአይን ህክምና ተቋም ስምንት የአይን ስፔሻሊስት ሃኪሞችና አራት የመነፅር ባለሙያዎች አሉት:: በአልትራ ሳውንድ፣ ባዮሜትሪክና በመሳሰሉት መሳሪያዎችም የተደራጀ ነው:: ከፍተኛ ቁጥር ያለው የአይን ቀዶ ህክምናም በአይን ህክምና ተቋሙ ይሰራል:: በርካታ የአይን ታካሚዎችም ወደ ተቋሙ መጥተው ይታከማሉ::

ወደዚህ ሆስፒታል ሪፈር ተፅፎላቸው የሚመጡ የአይን ታካሚዎች ሆስፒታሉ ከከተማው ወጣ ያለ በመሆኑ የታካሚዎችን እንግልት ለመቀነስ በእለቱ ህክምናቸውን አግኝተው ይሄዳሉ:: ቀዶ ህክምናም ቢሆን በሁለት ሳምንት ውስጥ ይጠናቀቃል::

እንደ ሃላፊው ገለፃ በሆስፒታሉ የአይን ታካሚዎች በአብዛኛው ድሆች ናቸው:: የጤና መድህን አገልግሎት በመጀመሩ ጥቂት ሰዎች ናቸው የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን የቻሉት:: እነዚህም ቢሆኑ እንደ ግላውኮማ የአይን ግፊት የሚፈጥር በሽታ ያለባቸው ሰዎች መድሃኒቱ የማያቋርጥ በመሆኑና የመድሃኒቱ ዋጋም ከፍተኛ በመሆኑ መድሃኒቱን ለመግዛት ሲቸገሩ ይታያል:: ለህክምናውም ከፍተኛ ወጪ ያወጣሉ:: በተጨማሪ ደግሞ የእይታ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች፣ ልጆችና አዋቂዎች መነፅር ሲታዘዝላቸው መነፅሩን ለመግዛት አቅም ያንሳቸዋል::

ከዚህ በመነሳት በሆስፒታሉ መነፀር እዛው እንዲሰራና አንድ ሰው መነፅር ሲታዘዝለት እዛው ተሰርቶ እንዲሰጠው የሚያስችል የመነፅር ማምረቻ ማእከል ተከፍቷል:: የጤና መድህን አገልግሎት ተጠቃሚ ያልሆኑ፤ ፍጹም ደሃ የሆኑትና የስጋ ደዌ ተጠቂ የሆኑት ደግሞ የመነፅር አገልግሎቱን በነፃ እንዲያገኙ ይደረጋል::

የመነፅር ማምረቻ ማእከሉ በሚሰራበት ጊዜ ከዚሁ ጋር በማያያዝ ህብረተሰቡን እያሳወረ ያለውን በስኳር በሽታ ምክንያት የሚከሰተውን የሬቲና መድማት፣ ውሃ መቋጠርና የመሳሰሉትን ነገሮች ለመፍታት እየተመረመሩ በጨረር የሚታከሙበት ክፍል ተዘጋጅቷል:: ለዚህ የሚያስፈልገውም መሳሪያ ተሟልቷል::

ከዚህ በተጨማሪም የአይን ዋናውን የመመልከቻ ግድግዳ ሬቲና ደረጃውን የሚመረምርና የሚያሳይ ክፍልም ከነመሳሪያዎቹ ተዘጋጅቷል:: እንዲህ አይነቱ ምርመራ ብዙ ሆስፒታሎች ላይ የሌለ በመሆኑ ይህን አይነቱን የምርመራ አገልግሎት ለሚፈልጉ ታካሚዎች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ እድል የሰጠ ነው::

ማእከሉን ገንብቶ ለማጠናቀቅ አምስት ወራት የፈጀ ሲሆን ለአጠቃላይ ግንባታውም 7 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር ወጪ ሆኗል:: ይህንንም ሙሉ ወጪ የሸፈነው ሲ ቢ ኤም /ክርስቲያን ብላይንድ ሚሽን/ የተሰኘ የጀርመን ግብረሰናይ ድርጅት ነው::

በሬቲና ጨረር ህክምና ክፍል በቀን እስከ 20 የሚጠጉ ታካሚዎች የሚስተናገዱ ሲሆን በመነፅር አገልግሎት ደግሞ እስከ 30 የሚሆኑ ሰዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል::

በአለርት ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር ዶክተር አድማሱ ትብለጥ በበኩላቸው እንደሚናገሩት የመነፅር ማምረቻ ማእከሉ የአይን ህክምና ማስፋፊያ አንዱ አካል እንጂ አዲስ ፕሮጀክት አይደለም:: ከዚህ ቀደም የሬቲና ጨረር ህክምናና ደረጃውን የጠበቁ የመመርመሪያ ክፍሎች አልነበሩም:: ከዚህ አንፃር ከመነፅር ማምረቻው በተጨማሪ እነዚህ የሪቲና ጨረር ህክምናና ምርመራ ክፍሎች ተከፍተዋል::

በተለይ ታካሚዎች መነፅር ሲታዘዝላቸው መነፅር ፍለጋ ሲንገላቱና ለመነፅሩም ከፍተኛ የሆነ ወጪ ሲያወጡ ይታያል:: ከዚህ አንፃር ማዕከሉ ማህበረሰቡ በተለይ ደግሞ ህፃናት ታክመው መነፅር ለማግኘት እንዳይነከራተቱና ከፍተኛ ወጪም እንዳያወጡ ሊያደርግ የሚችልና መነፅሩን እዚሁ አምርቶና ለክቶ ለታካሚዎች ለመስጠት የሚያስችል ነው::

ከሲ ቢ ኤም ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር የሚሰራውና በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ስር ያሉ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያሉ ህፃናት ተማሪዎችን ለማንኛውም የአይን ችግር በመለየት መነፅር የሚስፈልጋቸውን በነፃ ለመስጠትም ጥረት እየተደረገ ነው:: ከዚህ በኋላ የዕይታ ችግር ያለባቸው ህፃናት ተለይተው መነፀር ተዘጋጅቶላቸው የሚሰጣቸው በማእከሉ መጥተው ይሆናል:: ከዚሁ ድርጅት ጋር በመተባበር በቅርቡ ወደ ማህበረሰብ ልየታ ለመግባትም ማእከሉ ያግዛል::

ማዕከሉ ህፃናትን ታሳቢ ያደረገና የመነፅር ስራ አገልግሎቱም ለህፃናቱ በነፃ የሚደርስ ነው:: አዋቂዎችም በተመሳሳይ በተመጣጣኝ ዋጋ በማዕከሉ ተጠቃሚ ይሆናሉ:: ዝቀተኛ ገቢ ያላቸው ደግሞ አገልግሎቱን በነፃ እንዲያገኙ ይደረጋል::

ማዕከሉ መነፅሮችን ለማምረት የሚያስችሉ ክፍሎች፣ ማሳያ ክፍሎችና የሬቲና ጨረር ህክምናና የሬቲና ደረጃ መመርመሪያ ክፍሎችን አቅፏል:: ባጠቃላይም በማእከሉ ስምንት የአይን ስፔሻሊስቶች፣ አራት የመነፅር ባለሙያዎችንና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ይዟል:: በቀጣይም ለሌሎች ባለሙያዎች መነፅሩ እንዴት እንደሚሰራ ስልጠና የሚሰጣቸው ይሆናል::

የዚህ ማእከል ግንባታ ተጠናቆ ወደ ስራ መግባት መንግስት ለህክምናው ዘርፍ የሰጠው ትኩረት አንዱ ማሳያ ነው:: የመንግስት ሆስፒታሎች ባላቸው አቅም ለህብረተሰቡ ለመድረስ ከሚደረገው ጥረት ውስጥም አንዱ ነው:: ሁሉን አቀፍ የአይን ህክምና አገልግሎት ለመስጠት የሚደረገው ጥረት አንዱ አካልም ነው:: በቀጣይ ሃብታምም ሆነ ደሃ፤ ህፃንም ሆነ አዋቂ በማእከሉ መጥቶ ሲታከም መነፅር ሌላ ቦታ ሄዶ እንዳይገዛ የሚግዝ ጭምር ነው::

የአለርት ሆስፒታል ዋና ስራ አስፈፃሚ ዶክተር እስማኤል ሸምሰዲን እንደሚናገሩት በኢትዮጵያ የእይታ ችግር ያለባቸው በተለይ ደግሞ በትራኮማ የአይን በሽታ የሚሰቃዩ ዜጎች ቁጥር ከፍተኛ መሆኑ ያስቆጫል:: በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ላይ ለመስራት የሚያስችል እድልም አለው:: በአገሪቱ ከዚህ በፊት የሉም ተብለው የሚታሰቡ እንደ ስኳርና ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ካታራክትና መሰል የአይን ህመሞች ከፍተኛ ደረጃ እየያዙ መጥተዋል::

ስለአይን ህክምና ሲታሰብ ሁሉን አቀፍ የአይን ህክምና መስጠት የሚችል ተቋም መገንባት ወሳኝ ነው:: ለዚህም አለርት ሆስፒታል የአይን ህክምናን እንደቀዳሚ የትኩረት አቅጣጫ አድርጎ በመውሰድ እየሰራ ይገኛል:: ለዚህም ሲ ቢ ኤም የተሰኘው የጀርመን ግብረሰናይ ድርጅት ድጋፍ ያደርጋል:: ከነዚህም ድጋፎች ውስጥ አንደኛው የክላስተር ፕሮጀክት ነው:: በዚህ ፕሮጀክት አስራ ሶስት ሆስፒታሎችን አለርት እየመራ የአይን ህክምና መሳሪያዎችና ግብአቶችን የሚያገኙበትንና በመላው ኢትዮጵያ ያሉ ህክምናውን ማግኘት የማይችሉ ሰዎችን ለመደገፍ ጥረት ያደርጋል::

ዋና ስራ አስፈፃሚው እንደሚሉት የአይን ችግር ሲባል አዋቂዎችን ብቻ ሳይሆን ህፃናትንም የሚነካ በመሆኑ ይህንኑ መሰረት በማድረግ ከ ሲ ቢ ኤም ጋር በመላው ኢትዮጵያ አስራ ሶስት ሆስፒታሎች የሚሳተፉበት ፕሮግራም አለ:: ይህም በቀጣይ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል::

በሌላ በኩል የአይን ህክምናውን ህፃናት ጋር ለማድረስ አለርት ሆስፒታል የትምህርት ቤት ፕሮግራም ጀምሯል:: በዚህ የትምህርት ቤት ፕሮግራም በርካታ የእይታ ችግር ያለባቸው ህፃናት ተለይተዋል:: አንድ ሺ የሚጠጉ ህፃናት ደግሞ መነፅር ለመውሰድ ተዘጋጅተዋል::

ይህ ፕሮጀክት በሙከራ ደረጃ ያለ ሲሆን በመላው አገሪቱ እንዲስፋፋና አገራዊ ፕሮጀክት ሆኖ ትምህርት ቤቶች የአይን ህክምናው አካል እንዲሆኑ አለርት ሆስፒታል በቀጣይነት ተጠናክሮ ይሰራል::

ከዚህ ባሻገር ከጤና ሚንስቴር በሚደረግ ድጋፍ የጤና ህክምና ለማስፋፋት መሰረታዊ የአይን ህክምና ስልጠና ፕሮግራም በመቅረፅ ከተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች የጤና ባለሙያዎች ወደሆስፒታሉ መጥተው እንዲሰለጥኑና በችገራቸው ጊዜ የማማከር አገልግሎት በቴሌ ሜዲስን እንዲገኙ ለማድረግ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ:: በዚህም በሁለት ዙር በመሰረታዊ የአይን ጤና ህክምና ባለሙያዎችን ማሰልጠን ተችሏል::

አሁን ከተገነባው የአይን መነፅር ማምረቻ ማእከል በተጨማሪ የህፃናት የአይን ህክምና ማዕከል ራሱን ችሎ በቀጣይ የሚገነባ ይሆናል:: ለዚህም በሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ውስጥ ቦታ ተለይቷል:: ግንባታውም በቅርቡ ይጀመራል ተብሎ ይታሰባል:: እስከዛው ግን አሁን ላይ የተገነቡና ከዚህ ቀደም የነበሩትን የአይን ህክምና ክፍሎች የማጠናከር ስራ ይሰራል:: በቀጣይም አለርት ሆስፒታል በአፍሪካ በተመረጡ የህክምና ዘርፎች መሪና ምሳሌ ሊሆን የሚችል ተቋም እንዲሆን በጥንካሬ ይሰራል::

# ነፃ ሃሳብ



በ(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# ትዕቢት ውድቀትን ይቀድማል!

**የዘመናችን የኔሮ አልጋ ወራሾች፤**

ሕወሓት ለኢትዮጵያ መከራ፣ ለሕዝቧ የስቃይ ምንጭ ሆኖ የተተከለ መርገምት ነው። በባዕድ ቋንቋ እንግለጸው ከተባለ "TPLF:- The problem child of Ethiopia" ልንለው እንችላለን። ይህ የሽብር ቡድን ግማሽ ክፍለ ዘመን ለሚጠጋ ዓመታት ኢትዮጵያን ሲያምሳት፣ ምድሪቱን በደም አበላ ሲያጨቀይ፣ የተከበረውን የትግራይ ሕዝብ ማቅ በማልበስ ለመከራና ለእንባ እንደዳረገ "ለነጭ ጳጉር" ሊበቃ ችሏል። ያለ ባሩድ ሽታ መተንፈስና ያለ ደም ግብር መኖር የማይችሉት የዚህ አሸባሪ ቡድን መሪዎች፤ ሰብዓዊነት ለሚሉት "ክብር" ደንታ የሌላቸውና በሞትና በእልቂት የሚስቁ የዘመናችን ኔሮዎች ናቸው ማለት ይቻላል። ሕወሓት የተወከለበት የሮማው መሪ የኔሮ ታሪክ እንደሚከተለው በአጭሩ ይታወሳል።

በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ከጥቂት የሩቅ ምሥራቅ መንግሥታት በስተቀር አብዛኛዎቹ የወቅቱ ሀገራት በሮም አገዛዝ ሥር ወድቀው እንደነበር የዓለም ታሪክ ይነግረናል። የሮማው ገዢ የኔሮ የንግሥናና የገናናነት ዓመታት የሚባሉት ከ54 - 68 ዓ.ም የነበሩት 14 ዓመታት ነበሩ። ኔሮ ጎላ ባለ ሁኔታ የሚታወቀው በግዴለሽነቱ፣ በጨካኝነቱ፣ በአዝማሪ ወዳድነቱና በገንዘብ አባካኝነቱ ነበር። የሕዝቡን ገንዘብ ሲያራቁት ይሉኝታም ሆነ ስጋት ፍጹም በስሜቱ እንደማይዞር ግለ ታሪኩ ይመሰክራል። እያደርም ትዕቢቱና እብሪቱ እየገነነ ሄዶ ሕዝቡን መጨቆንና መግደል ዋናኛ ስራው እስከ መሆን ደረሰ።

በ64 ዓ.ም የሮም ቤተመንግሥትን የሚያስንቅ ወርቃማ ቤት (Golden House) ለራሱ በገጠራማው የከተማዋ ዳርቻ በኤስኩሊን (Esquiline) አስገንብቶ ሲያበቃ የነባሯን የሮም ከተማ የዝና ተቀናቃኝነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲያበቃ ወሰነ። የእብደቱን ድርጊት የፈጸመውም በመጠጥ ኃይል ክፉኛ ሰክሮ በሰገነቱ ላይ ቆሞ እየሳቀ አብዛኛውን የሮም ከተማ ክፍል በእሳት አጋይቶ የዶግ አመድ በማድረግ ነበር። እንዳሰበውም ተሳካቶለት ሮም በአንድ ምሽት ወደ ትቢያነት ተለወጠች።

የተመኘው ወርቃማው ቤተመንግሥቱ ተሰርቶ እንደተጠናቀቀና የሮም ከተማ በወደመች በአጭር ጊዜ ውስጥ ግን ሕዝቡና ሹማምንቱ በሚያስተውሉት የመሪያቸው ጭካኔና የእብደት ድርጊት ትእግስታቸው ስለተሟጠጠ የኔሮ ገናናነትና ፈላጭ ቆራጭነት እያደር እየቀዘቀዘ በመሄድ የሕዝብ ተቃውሞና አመጽ በየክፍለ ሀገራቱ መቀጣጠል ጀመረ። አምርረው የሚቃወሙትንና ከመንበረ ስልጣኑ ሊያስወግዱት ሙከራ ያደረጉትን ለውጥ ፈላጊ ዜጎቹን በአሰቃቂ ሞት እየቀጣ ዕድሜውን ለማራዘም ሙከራ ቢያደርግም የተቀጣጠለው የሕዝብ አመጽ ግን በአጭሩ ሊበርድና ሊገታ አልቻለም።

በመጨረሻም የተቃዋሚዎቹ ቁጣ ገንፍሎ በመውጣት የኔሮ ፍጻሜ መቃረቡ ተረጋገጠ። አንዴ የእብሪቱና የትምክህቱ ዋንጫ ሞልቶ መገንፈል ጀምሯልና የሕዝቡን ቁጣ ማንም ሊያስቆም አልተቻለውም። በራሱ በኔሮ ሠራዊት ውስጥ ሳይቀር ተቃውሞው በከፍተኛ ሁኔታ ከዳር ዳር እንደ ወላፈን በመግለብለቡ ፍጻሜው እየተቃረበ መገስገስ ጀመረ።

ነገሮች መባባሳቸው ያባነነው ኔሮ ከተቀሰቀሰበት የሕዝብ አመጽ አምልጦ ለመሄድ ሮምን ወደ ኋላው ትቶ በሽሽት ላይ እያለም አንዱን የቅርቡን ሰው አግኝቶ ተማርኬ እጄን ከምሰጥ በአንተ እጅ እንድትገለኝ ብሎ ስላዘዘው በዚሁ የውርደት አሟሟት ሕይወቱ አልፎ አሳፋሪ ታሪኩ ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገር ለማስተማሪያነት ሊውል በቅቷል።

የሕወሓት መሪዎች እኩይ ድርጊት የአንድ ሳንቲም ገጽታ ያህል ከሚቀራረበው የኔሮ ታሪክ ጋር ማመሳሰላችን ቢያንስ እንጂ የሚበዛ አይሆንም። እብሪትና ትምክህት የተጣባቸው የርኩስ መንፈስ ካዳሚዎቹ የዘመናችን የኔሮ አምሳያ የሕወሓት መሪዎች የዚያ ጨካኝ ሮማዊ መሪ መንትያ ወንድሞችና እህቶች ናቸው ብንል ከእውነታ አያርቀንም።

የሰሜን ዕዝን ሠራዊት ከድተው ያንን ሁሉ ግፍ ሲፈጽሙ የሠራዊቱ አባላት የሕዝብ ልጆች መሆናቸውን እንኳን ልብ ያሉት አይመስልም። ልጆቹ በግፍ የተሰውበትና መከራ የወደቀበት የኢትዮጵያ ሕዝብ በቸልታ ያልፈናል ብለው አስበው ከሆነም የጅልነታቸው ቀዳሚ መገለጫ ነው ማለት ይቻላል። ጥቂት የማይባሉት የሕወሓት መሪዎች የእብሪታቸውና የግፋቸው ውጤት ምን እንዳስከተለባቸው የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው። አንዳንድ የአሸባሪው ድርጅት መሪዎችም ልክ እንደ ኔሮ ግፋቸው ሲያቅበዘብዛቸው መና ሆነውና ትቢያ ለብሰው በምድረ በዳ እንደቀሩ የሚረሳ አይደለም።

ከውርደት ሞት የተረፉትም ቢሆኑ በምን ዓይነት ሁኔታ ከጎሬያቸውና ከተሸሸጉበት ዋሻ እጃቸውን ለምርኮ ከፍ አድርገው በመዘርጋታቸው ለነፍሳቸው ትድግና እየተማጸኑ ምህረት እንደጠየቁ ታሪክም እኛም ምስክሮች ነን። ከጥቂት ወራት በፊት እብሪትና የደም ጥማት ያክለፈለፋቸው የሕወሓት ሠራዊት አባላት "ድሉ የሰመረላቸው መስሏቸው" ንጹሐንን እየፈጁ፣ ሺህዎችን እያፈናቀሉና የሕዝብና የመንግሥት ንብረትን እያወደሙ ወደ መሃል ሀገር ሲገሰግሱ በሳተናው ሠራዊታችን፣ በሕዝባዊ ሠራዊትና በሚሊሺያ ጀግኖቻችን ክፉኛ ተመትተው ተረት እንደሆኑ አይዘነጋም።

እብደት ዓይነት አለው። የሕወሓት መሪዎችን እብደት ለመግለጽ ግን ያዳግታል። በአስተሳሰባቸው ብቻም ሳይሆን በህሊናቸው ጭምር ጨርቃቸውን ጥለው የማንነታቸውን እርቃን በማጋለጥ መሳቂያና መሳለቂያ መሆናቸው ለአባባላችን ጥሩ ማስረጃ ይሆናል። እንኳን ሰብዓዊ ፍጡር ቀርቶ የዱር እንስሳት እንኳን የወገናቸውን ሞት ሲመለከቱ በቋንቋቸው ሀዘናቸውን እየገለጹ ያነባሉ፤ ደመ ነፍሳዊው ልባቸውም እንዴት እንደሚሰበር መመልከት የዕለት ተዕለት ክስተት ነው።

በአብዛኞቹ የትግራይ እናቶችና አባቶች ቤት የሞት መርዶ መደመጥ እንግዳ አይደለም። ልጆቻቸው ከጉያቸው እየተነጠቁ በማያምኑበት ጦርነት ተማግደው ከንቱ ሆነው የቀሩት ከብዛታቸው የተነሳ "ይህን ያህል ቁጥር ነው" ብሎ ለመግለጽ እንኳን እንደሚያስቸግር ተደጋግሞ ተገልጿል። እውነታው ለጊዜው የተድበሰበሰ ቢመስልም የታሪክ ዐይን በንስር ስለሚመሰል ነግ ተነገወዲያ የተሰወረው እየተገለጠ፣ የተከደነው እየተከፈተ የአሸባሪው ሕወሓት ገመና ሲፈተሽ ጉድ የሚያሰኙ ግፎች ይፋ ተገልጠው ለአደባባይ እንደሚበቁ ይታመናል። እውነት ተደብቆና ለዘለዓለም ተዳፍኖ ስለማይቀር።

ሕወሓት ከአሁን ቀደም የፈጸመው እብሪትና የግፍ ድርጊት የተረሳ ይመስል ዛሬም የተራረፉ የምስኪን የትግራይ ልጆችን ከፊት አሰልፎ ከቀናት በፊት በሀገሪቱ ላይ ለሦስተኛ ጊዜ ጦርነት መክፈቱ በምን ቋንቋ እንደሚገለጽ ግራ ያጋባል። ከአለት ጋር መላተም ምን ውጤት እንደሚያስከትል መሪዎቹ ጠፍቷቸው ነው ለማለት አያስደፍርም። የትግራይን ምድር ተተኪ አልባና የአኬልዳማ ምድር ማድረጉ ለማንና ለምን እንደሚበጅም ግራ ያጋባል።

የትግራይን ወጣቶች "ግፋ በለው!" እያሰኙ እነርሱና ቤተሰቦቻቸው ግን በተለያዩ ሀገራት ተንደላቀው የሚኖሩት ህሊና ቢሶቹ የስልጡን ሀገራት "የአደባባይ ተንከባላዮች" እንደሚደሰኩሩት "ጦርነት በከበሮ የሚደምቅ ባህላዊ ጭፈራ" ሳይሆን፤ የደም፣ የአካልና የንብረት ምንዳ የሚያስከፍል አሰቃቂ ትራጄዲ ነው። ወጣቱን ወደ እሳት እየማገዱ እነርሱ ግን ጣቶቻቸውን ኮምፒውተር ላይ ሰክተው ሌት ተቀን የሚያራግቡት የሀሰት ትርክትና ፕሮፓጋንዳ ዞሮ ዞሮ የትግራይ ሕዝብ እውነታውን ሲረዳ አፈሙዙን ወደ እነርሱ አዞሮ የኔሮ ታሪክ እንደሚደገምባቸው አልገባቸውም ወይንም ገብቷቸውም ተስፋ ቆርጠዋል።

የትግራይ ሕዝብ በእነዚህ እኩይ ልጆቹ የመከራ እንጀራ እየበላ እስከ መቼ ኑሮውን ይገፋል? እስከ መቼስ ለከንቱ ጦርነት ልጆቹን የአረር ማብረጃ ማገዶ ማድረግን ምርጫው ያደርጋል? መሪ ተብዬዎቹና የቅርብ ጀሌዎቻቸው በውጭ ሀገራትና በሀገር ውስጥ በተንደላቀቀ ኑሮ እየኖሩ ሕዝበ ትግራይን በመከራ ወላፈን ሲያንገበግቡት እንዴት በቃን ብሎ የተገፋው ወገን አቅሙን ማሳየት ይሳነዋል? በእርዳታ የመጣን ነፍስ አድን እህል በምስኪን የትግራይ ወጣቶች ሕይወት እየለወጡ እነርሱ ሲንደላቀቁ ሕዝቡ በነቂስ ተነስቶ ሃይ ላለማለት ለምን እንደማይደፍር ግራ ያጋባል። የሕዝቡ አጠቃላይ ድቀት በምን ሚዛን እየተመዘነ ወይንም እየተነጻጸረ እንደሚገለጽ ለማሰብ ልብን ፍስስ ስለሚያደርግ ከዚህ በላይ ቃላትን አስማምቶ በማሳካት ስሜትን ለመግለጽ መሞከር እጅጉን ይፈትናል።

እርግጥ ነው ምንም ዓይነት እርምጃ በንፁሐን ላይ ለመውሰድ የመሪዎቹ ጭካኔ መጠንም ሆነ ዓይነት እንደሌለው በቅጡ ይታወቃል። ለበቀልም ሆነ ለክፉት ድርጊቶች የወያኔ መሪዎች እንደማይመለሱም ግልጽ ነው። ነገር ግን እስከ መቼ የትግራይ እናቶችና አባቶች ፍርሃት አቆርፍዷቸው እንዳነቡና ከል እንደለበሱ አልቅሰው ኖረው እያለቀሱ ያልፋሉ?

በጽዮን ማርያም ቤተክርስቲያንና በነጃሺ ደጃፍ በፈጣሪ መንበር ሥር የሚፈሰው የሕዝበ ትግራይ እንባስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚቆመው እንዴትና በምን ብልሃት ነው? ሕዝቡ ፈጣሪውን በመተማመን ኅብረት ፈጥሮ ለመከራ የዳረጉትን ጥቂት ጨካኝ መሪዎች "በቃችሁ!" ብሎ በቁጥስ አደባባይ ወጥቶ ለፍርድ አሳልፎ ሊሰጣቸው ይገባል። በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ሀገራት እየኖሩ ጦር የሚያሰብቁ የደም ነጋዴ ተቆርቋሪ ነን ባይ "የእንግዴ ልጆቹንም" ሕዝቡ "እምቢዮ! ሞትና መርዶ ሰለቸን! መረረን!" ብሎ "የሕዝብ ድምጽ የእግዜር ድምጽ" እንዲሉ አፋቸውን ሊያዘጓቸው ይገባል።

በሌሎቹ የሀገራችን ክልሎች ስለ ሰላምና ስለ ልማት እየተወራ በትግራይ ምድር ግን ሕዝቡ ሞትና ፍርሃት ከነገሠበት ግዞት ነፃ እንዲወጣ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ውዴታ ብቻም ሳይሆን ግዴታውም ጭምር ነው። የትግራይ ሕዝብ ግራ ተጋብቷል። በአንድ በኩል ልጆቼ በሚላቸው እኩዮች ሸክሙ በዝቶ አጉብጦታል። በሌላ በኩልም ከተቀሩት ወንድምና እህት ሕዝቦች ጋር እንዲቆራረጥ በሀሰት ፕሮፓጋንዳ ግራ ተጋብቷል።

በትግራይ ክልል የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት የሚያሰሙት የደውል ድምጽ ፈጣሪ የሚመሰገንበት "የስብሀት ለአምላክ" መወድስ ሳይሆን "ኤሎሄ! ኤሌሄ ላማ ሰበቅተኒ!" የሚል መቃተት ነው። የየመስጊዶቹ አዛንም "ፈጣሪ አምላክ ሆይ!" ለምን ረሳኸን!? ለምንስ በጨካኞች እጅ አሳልፈህ ሰጠኸን" የሚል ምሬት የሚስተጋባበት ነው። ይህን መሰሉ የወገኖቻችን መቃተት ተሰምቶን ሕዝቡን ከተቆራኙት የጨካኝ እጆች አርነት እንዲወጣ በጸሎትም በበጎነትም ልንደገፈው ይገባል።

መንግሥት ሰላምን ለማስፈን በቁርጠኝነት እየሄደበት ያለው ዕቅድ እንዲሳካም አጠናክረን ድጋፋችንን ልንገልጽለትና ልናግዘው ይገባል። እንደዚህ ጸሐፊ እምነት ከምንጊዜውም ይልቅ የትግራይ ሕዝብ የወገኖቹን ድጋፍ በብርቱ የሚፈልግበት ወቅት አሁን ነው። አረመኔዎቹ የሕወሓት መሪዎች ከምድረ ገጽ ጠፍተው ታላቁ የትግራይ ሕዝብ ነፃ እንዲወጣ ዜጎች በመረባረብ አቅማቸው የፈቀደውን ሁሉ ሊያደርጉ ግድ ይላል።

አሸባሪው ቡድን ዳግም የከፈተብን ወረራ በአጭሩ እንደሚቀለበስ ባያጠራጥርም ለመከላከያ ሠራዊታችንና በጎኑ ተሰልፈው መስዋዕትነት ለሚከፍሉት ጀግኖቻችን እንደተለመደው የሞራልና የማቴሪያል ስንቃቸውን አጠናክረን ልንደግፋቸው ይገባል። የትግራይ ሕዝብ ሆይ! መላው የሀገርህ ልጆች በጉዳትህ ማዘናቸው አልቀረም። እነዚህ የታሪክ አራሙቻዎች በፍጥነት ተነቅለው እንደተለመደው በየእምነት ተቋማቱ ደጀ ሰላም ላይ አብረን ፈጣሪን የምናመሰግንበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም።

በሁሉም ዘርፍ የገጠመህን ስብራት ተረባርበን ልንጠግንልህ ዝግጁ ሆነን እየተጠባበቅን ነው። ጦርነት ለማንም እንደማያዋጣ በአሸባሪነቱ ጨክኖ ልቡ ለደነደነው ሕወሓትና ለልበ ድፍኖቹ መሪዎቹ መልእክታችንን በሚገባቸው ቋንቋ አድርስልን። የትግራይ ሕዝብ የኢትዮጵያ ፈርጥ ነው። የተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብም ለትግራይ ውበት ነው። መከራው ያልፋል። እጅ ለእጅ ተያይዘን ፈጣሪን የምናመሰግንበት ጊዜም ሩቅ አይሆንም። የዘመናችን የኔሮ ደቀመዛሙርት የሕወሓቱ መሪዎችና ጋሻ ጃግሬዎች የሚጠፉት በራሳቸው እጅ ወይንም ከራሳቸው በወጣ ኃይል ነው። ይህ መልእክት ትንቢት ሳይሆን እውነት ነው። ለምን ቢሉ ሁሌም ትዕቢት ውድቀትን ይቀድማልና።

ሰላም ይሁን!

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተናጋሪው ዶሴ

## በ"ወደድኩሽ" የጠፋች ነፍስ

**አስመረት ብስራት**



በፍቅር ላይ የተመሰረተ ትዳራቸውን ለማቅናት ሁለቱም ደፋ ቀና የሚሉ ባልና ሚስት ናቸው። ፍቅራቸው ከቤት አልፎ ለሌሎች የሚታይ የተለየ አይነት ነው። ከማጣት እስከ ማግኘት በጋራ ያሳለፏቸውን ቀናት በትዝታ ማህደሮቻቸው በደማቅ ቀለም ፅፈዋል። መደጋገፍ መከባበራቸውን ለተመለከተ በአንድ ቋንቋ ሲናገሩ፤ በአንድ ልብ ሲጣመሩ ላየ ሁሉ "እውነትም ባልና ሚስት ከአንድ ምንጭ ይቀዳሉ" ሳይል አያልፍም።

ፀብ በቤታቸው ታይቶ አይታወቅም ቢባል ማጋነን አይሆንም። ከፍቅራቸው የተነሳ በሀሳብ አለመግባባት እንኳን ቢኖር ወደ ኩርፊያ ወደ ጭቅጭቅ ሳያድግ እዛው ላይ በአጭሩ ቋጭተው ወደ ነበረ ፍቅራቸው ይመለሱ ነበር። ለልጆቻቸው አርአያ የሆኑ፤ በመንገር ሳይሆን በመኖር ልጆቻቸው መልካም ስነ ምግባር ኖሯቸው እንዲያድጉ የሚያደርጉ ባልና ሚስት ነበሩ። ፍፁም ትህትናና ሰላም በቤታቸው የሰፈነ የሚያስቀና ፍቅር የነበራቸው ሰዎች ስለመሆናቸው የሚያውቃቸው ሰው በሙሉ ይናገሩላቸዋል። አይደለም ለረጅም ጊዜ ተለያይተው፤ በስራ ምክንያት እንኳን ቀን ሙሉ አብረው አለመዋላቸው የሚያነፋፍቃቸው አይነት ናቸው።

"ስስቴ ናት በሙሉ አይኔ አይቻት አላውቅም፤ አጠገቤ ሆና ትናፍቀኛለች። ሁለመናዋ በሕይወት መኖሬን የሚያረጋግጥልኝ እድሜዬ እንዲረዝም የምታደርገኝ ልዩ ፍጥረት ናት ይላል ባለቤቷ ስለ ሚስቱ በጠየቁት ቁጥር። የእሷም መልስ ይህንኑ ነው የሚመስለው ከሱ ተለይቼ መኖር የምችል አይመስለኝም። ፈጣሪዬ ከእሱ ፊት ያድርገኝ" በማለት አክብሮቷን፤ በስስት ፍቅሯን ትገልፃለች።

### ተወዳጇ ሴት

የደም ገንቦ ከሚባሉት ሴቶች መካከል ትመደባለች። ጨዋ ስራዋን፣ ትንሽ ትልቁን የምታከብር አይነት ሴት ናት። ይህች መልክና ፀባይ አሟልቶ የሰጣት ሴት ቤተሰቧን አክባሪ ትዳሯንም ወዳድ ናት። ቤተሰቡ ከእንቅልፉ ሳይነሳ ቀድማ ተነስታ ቁርሱን ቡናውን ስታደርስ ማንም አይስተካከላትም።

ከባለቤቷ ጋር ያላቸው መልካም ግንኙነት ለሰፈር ምሳሌ አድርጓቸዋል። ተወዳጅዋ እመቤት ፈፅማ ትዳሯን የምታከብር ለቤተሰቧ ሕይወት መቃናት ሌት ከቀን የምትደክም ጠንካራም ሴት ናት። የቤቷን ስራ ጨርሳ ወደ መስሪያ ቦታዋ ስትደርስ በዛም የተሰጣት ኃላፊነት ላይ ተግታ የምትሰራ ዘወትር አዲስ ነገር ለመማር የምትታትር ናት።

የስራ ቦታዋን እንደምትወድና እንደምታከበር አለባበሷ ምስክር ነው። ጥንቅቅ ያለ የቢሮ አለባበስ ለብሳ ነው በስራ ገበታዋ ላይ የምትገኘው። ኃላፊነቷን በፈገግታ ያለ ምንም መከፋት የምታከናውነው ይች ሴት አጠገቧ የደረሰ ባለ ጉዳይ በሙሉ ፊቱን ቀጨም አድርጎ ሲመለስ ታይቶ አይታወቅም።

### በቁም ቅዠት ውስጥ የገባው አፍቃሪ

ፈገግታ ከፊቷ የማይጠፋውን ይህችን ሴት በልቡ ተመኝቶ አይኑን የጣለባት አንድ ሰው ነበር። ለቤት ለደጁ አድባር፤ ውብ ጠንቃቃ ሴትን አይቶ ማለፍ የከበደው ይህ ሰው ባለትዳር መሆኗን እስኪረሳ ድረስ በፍቅር አቅሉን ሳተ። እሷ የኔ ብቻ ናት በሚል የህልም ዓለም መዋኘት ከጀመረ ሰነባብተ።

ይህ ቅዠቱን እውን ለማድረግ የሌላ ሰው ሚስትን የተመኘው ይህ ሰው ለዚህች ቀና ልብ ላላት ባለቤቷን አክባሪና ታማኝ ሴት ሀሳቡን ያካፍላታል። ይህ ጉዳይ መሆን እንደማይችል በፍቅር ዓለም ከባለቤቷ ሌላ ሰው መመልከት የማትችል መሆኑን በትህትና ታስረዳዋለች። ጉዳዩ አልዋጥለት ያለው ይህ ሰው በምንም ተአምር ከእኔ ውጭ የሌላ ሰው መሆን አትችይም በማለት ዛቻና ማስፈራሪያ ያደርስባት ጀመር።

በወጣች በገባች ቁጥር "ያንን ጉዳይ እንዴት አደረግሽው ?" በማለት መውጫ መግቢያ ያሳጣታል። ይህ ሰው ሀሳቡን እንዲቀይር ደጋግማ ወትውታውም ነበር። በምንም የቃላት ጋጋታ የማስረዳት ሙከራ ሀሳቡን አልቀይር ይላል። በማይሆን ፍቅር ልቡ ታወረ። ሆኖም እንዲህ አይነት ሰው ሊያጋጥም ይችላል ብላ በማሰብ ነገር ግን እርሷ ላይ እንዲወርድላት ሽማግሌም ልካበት ነበር።

ሆኖም ግን ልቡም አይኑም ታውሯልና የፈለኩትን ነገር በሀይል ማድረግ እችላለሁ በሚል አስተሳሰብ የግድ የእኔ መሆን አለብሽ ካለበለዚያ ግን በሕይወት አትኖሪም በማለት ያስፈራራት ጀመር። ሁልጊዜ ስለሚፎክርና ስለሚዝት ከወሬ ያለፈ ጉዳት ያደርስብኛል የሚል ሀሳብ ተሰምቷት አያውቅም ነበር።

### ያልታሰበው የጭካኔ በትር

ጥር 2 ቀን 2011 ዓ.ም ከረፋዱ አምስት ሰአት ከሰላሳ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ወረዳ አንድ ልዩ ቦታው ሳባ ሕንፃ ውስጥ በሚገኘው የንፋስ ስልክ ላፍቶ ወረዳ ፋይናንስ ቢሮ ውስጥ ወይዘሮ መዓዛ ካሳ የተለመደ ስራዋን በተለመደው ትጋት እያከነወነች ነበር።

ከዚህ ቀደም የፍቅር ጥያቄ አቅርቦላት ባለትዳር እንደሆነች የገለፀችለት አቶ ጌታቸው ዓለምፀሐይ ክፍሉ ኮስተር ያለ ፊት በማሳየት ወደ እሷ አቅጣጫ ሲመጣ ተመለከተችው። ሆኖም እንደተለመደው ተናግሮ ዝቶና አስፈራርቶ ይሄዳል በሚል መንፈስ ዘና ብላ ተቀበለችው። ልክ እንደመጣ ለመጨረሻ ጊዜ እንደሚጠይቃትና የፍቅር ጓደኛው ካልሆነች እንደሚገላት በቁጣ ነገራት። እሷ ደግሞ ባለትዳር እንደሆነችና የፍቅር ጥያቄውን መቀበል እንደማትችል ቁርጥ ባለ አማርኛ መለሰች። ይህንን አስረግጣ ብትገልጽለትም የግድ አብረው መሆን እንዳለባቸው ይወተውታታል። ምንም ለወጥ ለሌለው ሀሳብ ጊዜውን ማጥፋት እንደማይኖርበት ተናግራ ፊቷን ወደ ስራዋ መለስ አደረገች።

በቢሮው ውስጥ የነበሩ ሰዎችም የተለመደው ጭቅጭቃቸው ነው በሚል ለጉዳዩ ቁብ ሳይሰጡት ስራቸውን ያከናውናሉ።

ወይዘሮ መዓዛ ለፍቅር ጥያቄው ፈቃደኛ የማትሆን እንደሆነ የተረዳው አቶ ጌታቸው "ለምን ጥያቄዬን አልተቀበለችኝም?" በሚል ምክንያት ከዚህ በፊት እንደዛተው በጎኑ ደብቆ የያዘውን ቢላዋ በማውጣት በሥራ ገበታዋ ላይ እያለች ያባርራታል። ቢላዋ አውጥቶ እያባረራት ያለውን ሰው ለማምለጥ ከቢሮ ወጥታ ስትሮጥ ፍርሃት ያስተሳሰረው እግራ ተጠላልፎ ደረጃ ላይ ወደቀች።

በወደቀችበት ቀና ብላ በተማፅኖ አይን ተመለከተችው። እንዲተዋትም በፍርሃት ድምፅ ተማፀነችው። የተማፅኖዋን ድምፅ ከምንም ያልቆጠረው ይህ ሰው ምንም አይነት ርህራሄ ሳያሳይ በቀኝ እና በግራ ሆዷ ላይ ደጋግሞ በመውጋት የሆድ ዕቃዋ ወደ ውጭ ወጥቶ ሕይወቷ እንዲያልፍ ያደርጋል።

ይህ ጉዳይ ይፈፀማል ብለው ያልጠረጠሩትም የስራ ባልደረቦች ሩጫውን ተከትለው የወደቀችበት ቢደርሱም ከጥቃቱ ሊያስጥሏት ሳይችሉ ይቀራሉ።

ይህን በማድረጉ እርካታ የተሰማው የሚመስለው ገዳይ ብዙም ሳያንገራግር በፖሊስ ቁጥጥር ስር ይውላል። በፖሊስ ቁጥጥር ስር ሲውል ምንም አይነት የጥፋተኝነት መንፈስ ፊቱ ላይ እንዳልተነበበ በወቅቱ የነበሩት ሰዎች ይናገራሉ።

### ግማሽ አካሉን በግፍ የተነጠቀው ባል

የወይዘሮ መአዛ ባል በሰላም ደህና ዋይ ብሎ ጉንጯን ስሞ የተለያትን የባለቤቱን ሞት የሰማው በስልክ ነበር። መጀመሪያ ሲሰማ ቀለድ መስሎት ነበር። ባለቤቱ መጎዳቷንና ሆስፒታል መሆኗን የነገረው ፖለስ እንዲረጋጋ አድርጎ የተፈጠረውን ሲያስረዳው የሰማውን ባለማመን ሰሜት እራሱን ስቶ ወደቀ። ከወደቀበት ደጋግፈው ያነሱት ሰዎች ጋር በመሆን ወደ ሆስፒታል ሲደርስ ያች የዋህ ደግ የቤቱ ዋልታና ማገር ሚስቱ ዳግም ላትመለስ አሸልባለች። ወጥታ እስከምትገባ የማታምነውን ቤቷን፤ ፍቅሯ ከእለት እለት የማይነጥፈውን ባሏን፤ በስስት በሙሉ አይኗ አይታቸው የማታውቃቸውን ልጆቿን እንደዋዛ በትና አለፈች።

ወደ እእምሮው ብዙ ሀሳብ መጣ የልጆቹን ሁኔታ አሰቦ እሷ የደፈነችው ትልቅ የቤት ሽንቁር ተከፍቶ ታየው። በሀዘን ተንቀጠቀጠ፤ የሚይዘው የሚጨብጠውን አጣ። እንባ የሀዘን መብዛት የሚመልሳት ቢሆን የባለቤቷ ሀዘን ብቻውን ከሞት መንጋጋ ፈልቅቆ ያስቀራት ነበር።

ያች የንጋት ፀሐይ ባለቤቱን፤ ያችን አብሮ አደግ እህቱን፤ የልጆቹን እናት ግማሽ አካሉን ያሳጠውን ሰው ምን ቢያደርገው መርካት እንደሚችል አያውቅም። ሀዘን የቦረቦረውን አንጀቱን አስሮ ከአይኗ ስር ልታጣቸው የማትፈልጋቸውን ልጆቿን እናትም አባትም እንደያጡ አቅሉን ሰብሰብ ማድረግ ጀመረ።

ምንም ይሁን ምን በወደድኩሽ ምክንያት የሚስቱን ሕይወት ያሳጠውን ሰው በህግ ፍትህ እንዲሰጠው እየተማፀነ ግራ በተጋባ ስሜት ተቆራምዷል። "ፍትህ ይሰጠኝ ፤ ህግ ይፍረደኝ...." እያለ ማንባቱን ማቆም ተስኖታል።

### የፖሊስ ምርመራ

የተበዳዮችን እንባ ለማበስ ከህግ የበለጠ መቅጣት ማነጽ ማስተማር የሚችል የለምና የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ይህን አሰቃቂ ወንጀል የፈፀመውን ሰው በቁጥጥር ስር ካዋለ በኋላ ለዚህ ተግባር መንስኤ ያለውን በምርመራ አጣርቶ በሴቶች እና ሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት በከባድ የሰው መግደል ወንጀል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት በዐቃቤ ሕግ ክስ ቀርቦበታል።

በምርመራ ወቅት "የወደድኩሽ ጥያቄ አቀረብኩላት፤ እንቢ አለችኝ ገደልኳት" በማለት የእምነት ክህደት ቃሉን የሰጠው ተከሳሽ በፖለስ ቁጥጥር ስር ሆኖ በምርመራ ላይ እያለ ከእስር ያመልጣል። ይህ ሰው ከባድና ዘግናኝ አሰቃቂ ወንጀል ፈፅሞ እንኳን ጸጸት አልተሰማውም ነበር። በጭካኔ የፈፀመው ወንጀል ሳይበቃው አሁንም ከእስር ቤት አምልጦ በነፃነት እንዲንቀሳቀስ ያስቻለው ጉዳይ ምን ይሆን? የሚል ጥያቄ በልባቸው የያዙት ፖሊሶች ባላሰቡት አጋጣሚ ከእጃቸው የወጣውን ወንጀለኛ ማፈላለግ ቀጠሉ። ምንም እንኳን በተከሳሹ ላይ የተደረገው ምርመራ ተጠናቆ ጥፋተኛ የሚያስብል ውሳኔ እንዲወሰነበት መዝገቡ ወደ አቃቤ ህግ ቢላክም ተከሳሹን ማግኘት አልተቻለም ነበር። ይሄ ተፈላጊ ወንጀለኛ በማምለጡ ምክንያት ክሱ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል።

ተከሳሹ ሆነ ብሎ የተሰወረ በመሆኑ ዐቃቤ ሕግ የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ በሚያሰማበት ጊዜ የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ የመጠየቅ እና የመመርመር መብቱ ታልፎ ፍርድ ቤቱ በዐቃቤ ሕግ የቀረበው ማስረጃ በበቂ ሁኔታ ተከሳሹ ድርጊቱን የፈጸመ መሆኑን አስረድቶ ውሳኔ ተሰጥቶት በተገኘበት እንዲያዝ ማዘዣ እንዲወጣ ጠይቋል።

ወንጀል ሰርቶ በሰላም መኖር የማይቻል መሆኑን ለማሳያ ፖሊስ ሌት ከቀን ባደረገው አሰሳ ከእስር ቤት ያመለጠውን ወንጀለኛ አድራሻውን በመቀያየር የተለያዩ የከተማይቱ ክፍሎች ሲዘዋወር ፖሊስ ከህብረተሰቡ በደረሰው ጠቆማ መሰረት እግር በእግር ተከታትሎ ለፍርድ ሊያቀርበው ችሏል።

### ውሳኔ

ወንጀለኛው ያልተገኘ በመሆኑ እንዲሁም መብቱን ጠብቆ የዐቃቤ ሕግን ክስ እና ማስረጃ ያላስተባበለ በመሆኑ የጥፋተኛነት ፍርድ በመስጠት ነሐሴ 4 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኖበታል። ይህ ውሳኔ ከተወሰነ በኋላ ወንጀለኛው በፖሊስ ቁጥጥር ስር በመዋሉ ተከሳሹ እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ ውሳኔው ተፈፃሚ እንዲደረግ ብይን ተሰጥቷል። መዝገቡ ተዘግቶም ወደ መዝገብ ቤት ተልኳል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ስማችንን እንኑር

ተገኝ ብሩ

አንዳንዴ ስም ከምግባር ጋር ሲገጥም ደስ ይላል። የሰዎችን ተግባርና ስብዕና ተመልክተን ልንወዳጃቸው እንፈልጋለን። በሂደት ስማቸውን ስንሰማ ወይም ሲነግሩን ከተግባርና ባህሪያቸው ጋር የተገናኘ ሲሆን ያስገርመናል። መልካም ተግባር ላይ የምናገኘው ሰው መልካሙ እባላለሁ ሲለን፤ ለሰዎች ፍቅርን ያለ ስስት የሚቸር ሰው ደግሞ ፍቅሩ እባላለሁ ቢለን ግጥምጥሞሹ ያስገርመናል። ስምና ተግባር፤ ባህሪና መጠሪያ ግጥምጥም ሲል ደስ ያሰኛል።

ደግሞ በተቃራኒው ስምና ተግባሩ የማይገጥም፤ ባህሪው ከስራው ጋር የማይጥምም ሰው አለ። አስቡት የሺ ጥላ ተብሎ ለራሱ እንኳን ጥላ መሆን አቅቶት ሰውን ተደግፎ ሌላን ተመርኩዞ የሚኖር። ኧረ እንደውም የሌላውን ጥላ የሚያጠፋ ሊሆን ይችላል። እናቱ መብራቴ ብላ ተስፋ የጣለችበት ልጅዋ መብራት መሆኑ ቀርቶ የእናቱንም የራሱንም ተስፋ የሚያጨልም ዱርዬ ሲሆን ስምና ተግባር ለየቅል ይሆናል። ተግባርና ስማቸው ለየቅል የሆኑ ሰዎች ሲገጥሙን የበፊቶቹን ያህል ባያስገርሙንም ተግባራቸውን አይተን ስማቸውን ስንሰማ "አይ.." ሳያስብሉን አይቀሩም።

አንድ ስማቸው ከግብራቸው ጋር ግጥምጥም የሚልብኝ ሁሌም ሳያቸው ሰውነት ተላብሰው፣ ሰው የሚያሰኝ ንጥር ስብዕና የተላበሱ ሰው ትውስ ይሉኛል። አመለ ሸጋና ጥበበኛው ጋሽ ጥበቡ። አባ መላው ነገሮችን በጥበብ መፍታት የሚችሉ የሰፈሬ ሰው ናቸው። እኔ ጋሽ ጥበቡን ሳስብ ስማቸው የወጣው ዘግይቶ ጥበበኛ መሆናቸው ታውቆ ነው የሚል ጥርጣሬ አለኝ። ቤተሰቦቻቸው ስም ያወጡላቸው ቆይተው ጥበበኛ መሆናቸው ሲያውቁ "ይሄ ልጅማ ጥበቡ እንበለው" ያሉ ነው የሚመስል። የልጃቸውን ባህሪ አይተው ጠብቀውና አረጋግጠው ነው "ጥበቡ" ብለው የሰየማቸው በሚል የአካባቢው ነዋሪዎች ይጠራጠራሉ።

ጋሽ ጥበቡ ከሲታ ናቸው። ከሰውነታቸው ቅጥነት አንፃር እሳቸው ጥበበኛ ባይሆኑ ይህቺ ፈታኝ የሆነች ዓለም እንዴት ትፈትናቸው እንደነበር መገመት አይከብድም። "ሳይደግስ አይጣላም" ነው የሚባል። አለ አይደል፤ ሰው ቀጥኖና ኮስምኖ ሲታይ በሽሙጥ "አንተ እፍ ቢሉህ 50 ሜትር ትርቃለህ" ተብሎ በተደጋጋሚ የሚሾመጥ አይነት ቅጥነት ያላቸው ናቸው። ግን ደግሞ ወፍራም ምላስ የታደሉ ናቸው።

ቅጥነታቸውን አይቶ ሊዳፈራቸው የሚቃጣ ጎረምሳ፤ በወፍራሙ ምላሳቸው ያላጉታል። በነገር ወስፈያቸው ያርቁታል። ሁሉንም እንዳመጣጡ ነው የሚመልሱት። ሁሉም ከጡንቻ በላይ የሆነ ምላሳቸውን ስለሚፈራ አንዳች ነገር ደፍሮ የማይላቸው በጥበባቸው የተከበሩ ሰው ናቸው።

ታዲያ የጋሽ ጥበቡ ምላስ ስድብን ብቻ ሳይሆን መላንም የታጠቀ ነው። የተናገሩት ጠብ የማይል አንደበተ ርቱእ ናቸው። ሲያወሩ አጀብ የሚያስብሉ፣ አፍ የሚያስከፍቱም ናቸው። ነገር ሳያከብዱ ውስብስብ ነገሮችን በቀላሉ ፈተው የሚያስረዱ፣ መላን የሚጠቁሙና ለብዙ ችግሮች መፍትሄ የሚያመላክቱ ናቸው። "አባ መላ" የሚላቸውም ይበዛል። ብቻ ጋሽ ጥበቡ በጥበብ ከባዱን ኑሮን እንደ ጉድ ነው ጢባ ጢቤ የሚጫወቱበት።

መኖር ያውቁበታል፤ አኗኗርና ጉዳይ ላይ ይጠበባሉ። ሰፈር ውስጥ ሰው ሲጣላ እንዴት እናስታርቅ መላ ፍለጋ እሳቸው ጋር ይኬዳል። ጉዳይ አልሳካ ሲል እንዴት ብፈታው ይሻላል ብሎ የሚቀርባቸው ወዳጅ ይበረክታል። ሁሉንም በመልክ መልኩ ፈር ያሲዙታል። ለታመመ መድሃኒት ያዛሉ፤ የኤሌክትሮኒክስ እቃ ለተበላሸበት አበጅተው ይመልሳሉ፣ ቤት ለፈረሰበት እጀ ወርቅ አናጢም ናቸው። እናም ያስገርሙኛል። ስለ ኢትዮጵያውያን ጥበበኛነት ተደጋግሞ ሲነገር እኔ ጋሽ ጥበቡ ይታወሱኛል።

በዛሬው ትውልድ ግን ጥበቡ የሚባሉ ሰዎች ስያሜ ካልሆነ በቀር የአባቶቻችንን ጥበብ እንደ ስማቸው የወረሱ ቀንሰውብኛል። ለጉዳዮቻችን መላ የሚያበጅ አልሳሳም ትላላችሁ? ጥበበኛ ብንሆን እንዲህ እርስ በርስ የምንፋጅበት፤ አንድነት ላይ ሽፍተን መነጣጠል የመረጥንበት ግራ የገባ ማነሳችን መፍትሄ ባበጀን ነበር። ለማሕበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውሳችን መፍትሄ ባበጀን ነበር።

ጎበዝ ስማችንን ብንኖር እኮ ወደ መልካም ገፃችን እንመለስ ነበር። የአብዛኞቻችን ስም መልካም የሚባል ትርጓሜ ያለው ነው። ተግባራችን ከስማችን ጋር አልገጥም አለ እንጂ። ዛሬ ላይ ፍቅር የተባሉ ስሞች በዝተው ስማቸውን ግን አይኖሩትም። ሰላም የሚባሉ እልፎች በርክተው ጦርነት ሲሰብኩ፣ ግጭትን ሲያበረታቱ ይስተዋላል።

በነገራች ላይ ሰዎች በተለያየ ልማድና ገጠመኝ የሚያወጡት ስም በሰዎች ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል። ስለዚህም በስም አወጣጥ ላይ ጥንቃቄ ቢደረግ መልካም ነው የሚባለው ለዚያ ነው። ብቻ የብዙዎች ስም መልካም ትርጓሜ ያለው ነውና ሰዎች ስማቸውን ቢኖሩ፣ ስማቸውን በተግባራቸው ቢተረጉሙ መልካም ይሆናል የሚል እምነት አለኝ።

አንዳንድ ስሞች በራሳቸው ትርጓሜያቸውን ስንሰማ ሊያስገርሙን ይችላሉ። ለምሳሌ አሸብር፣ ቅጣው፣ ደም መላሽና የመሳሰሉት። ግን ብዙ ጊዜ እነዚህን ስሞች የተላበሱ ሰዎች ከስማቸው ጋር የተገናኘ ተግባር ላይ አይገኙም። እንደውም ተቃራኒ ናቸው። ባይሆኑ እኮ እነ አሸብር ሲያሸብሩን ሊኖሩ ነው። ነገር ግን እነ አሸብር፣ ሲያሸብሩ የምናገኛቸው ላይሆኑ ይችላሉ። እንደ ደም መላሽና ቅጣው የተባሉም ተግባራቸው ለየቅል ነው። እናም እነ አሸብር ስማችንን እንኑር ወይም እንተግብር ያልኳችሁ አይደለም።

ጋሽ ጥበቡን ሳስብ ሁሉም እንደሳቸው ስሙን በኖረ እላለው። በነገራችን ላይ እኛ ኢትጵያውያን ነገሮችን በጥበብ መመልከት የተሳነን ቢመስልም ጥበበኞች ነን። ጥበበኛ አይደለንም ብለን ብንሞግት እንኳን ይችን አገር በጥበብ ያቆዩልን አባቶች ጥበበኛ መሆናቸውን መካድ አንችልም። ስለዚህ እኛ የጠቢባን ልጆች ነን ማለት ነው። ስለዚህ የሁላችንም ስያሜ በጥበብ የተቃኘ ነውና ጥበብ ላይ ይደርሳል።

ጥያቄው ከጥበበኛ አባቶቻችን የወረስነውን ጥበብ እንዴት መተግበር ያቅተናል ነው። ሕሄ ቁጭት ሊፈጥርብን ይገባል። የአባቶቻችንን ጥበብ እንላበስ። የራቀንም እሱ ነውና።

ብዙዎቻችን መልካም ነገር እናስባለን፣ ያ መልካምነትና ተስፋ እንዲጋባብን ደግሞ ለልጆቻችን ስም ስናወጣ ብዙ እናስባለን። ነገር ግን እኛ ባባቶች ቀድሞ የተሰጠን መልካም ስያሜን ስንኖር አንይታይም። ከዚያ ስለራቅንና ስማችንን ስለማንኖር አዲሱን ትውልድ በፍቅር ገርተን አብሮ እንዲቆም ለማድረግ ተስኖናል።

አባቶች ያቆዩትን ጥበብ ተረክበን ሌላ ጥበብ አክለንበት ቀድመን የጀመርነውን ሥልጣኔ በአገራችን ህዳሴ በማቃረብ እንድገመው። የያዝናቸው እና የተሰየምንባቸውን መልካም ስሞች እንኑራቸው። ዛሬ ላይ በጥበብ መጓዝና ነገን አስቦ መስራት ያስፈልጋል። የጠቢባን ምድር የሆነችው አገራችን ጥበቧን መጠቀም የምንችለው ሰላሟ ሲበረከት ነውና።

# ዓለም አቀፍ

## የትራምፕ ቤት እንዲበረበር ያዘዙት ዳኛ ዝርዝር መረጃዎች ይፋ እንዲሆኑ አዘዙ

የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬziዳንት ዶናልድ ትራምፕ መኖሪያ ቤት እንዲፈተሽ ትዕዛዝ የሰጡት ዳኛ ብርበራውን እንዲያጸድቁ ያደረጓቸው ሰነዶች ይፋ እንዲሆኑ አዘዙ። በዐቃብያነ-ሕግ የተሰበሰቡትን ማስረጃዎች ብሎም ለችሎቱ ያቀረቡት ቃለ መሃላ ሰነድ ቅጂ ይፋ የሚሆን ከሆነ ስለምርመራው ተጨማሪ መረጃዎችን ይፋ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል።

የአገሪቱ የፍትህ ሚኒስቴርም መረጃው ይፋ የሚወጣ ከሆነ በሂደት ላይ ያለውን ምርመራ ይጎዳል ሲል ወቅሷል። የብርበራ ማዘዣው እንደሚገልጸው ትራምፕ የፕሬዚዳንትነት ጊዜያቸው ካበቃ በኋላ ከኋይት ሀውስ ወደ ቤታቸው የመንግሥትን መዛግብት አላግባብ ወስደዋል በሚል ወንጀል በመጠርጠራቸው ነው ኤፍቢአይ ምርመራውን የጀመረው።

የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች ከሥልጣናቸው ሲለቁ ሰነዶችን እና ኢሜሎችን ወደ ብሔራዊ ቤተ መዛግብት የማስተላለፍ ግዴታ አለባቸው። የቀድሞው ፕሬዚዳንት ትራምፕ የቀረበባቸውን ውንጀላ ውድቅ ያደረጉ ሲሆን መርማሪዎች በፍሎሪዳ በሚገኘው ቤታቸው ውስጥ አግኝተነዋል ያሏቸውን ሚስጥራዊ ሰነዶች እርሳቸው ቀድመው ያሳወቁ መሆናቸውን አስረድተዋል።


ጉዳዩ ላይ የተሰየሙት ዳኛ ብሩስ ራይንሃርት ትናንት በሰጡት ትእዛዝ ዛሬ ዓርብ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ ዝርዝር መረጃዎችን የያዘው የቃለመሃላ ሰነዱ እንዲለቅ አዘዋል። ዳኛው ዐቃቤ ሕግ የምስክሮችን፣ የሕግ አስከባሪ አካላትን፣ ያልተከሰሱ አካላትን ማንነት እንዲሁም የምርመራውን ስልት፣ አቅጣጫ፣ ወሰን፣ ምንጭ እና ዘዴ የሚገልጹ የሰነዱን ክፍሎች ይፋ እንዳይሆኑ አሳማኝ ምክንያት በማቅረቡ እነዚህ ዝርዝሮች ይፋ በሚሆነው ሰነድ ውስጥ እንደማይካተቱ ተናግረዋል።

የፍትህ ሚኒስቴር በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መሠረት የቅጣት ውሳኔዎችን የያዘ የቃለ መሃላ ቅጂ ለችሎቱ ማስገባቱን አስታውቋል። የተሻሻለው ሰነድ ትራምፕ ምስጢራዊ ሰነዶችን በፕሬዚዳንትነታቸው የመጨረሻ ቀናት ለምን እንደወሰዱ እና በፓልም ቢች ውስጥ ተከማችተው በነበሩበት ጊዜ ምን እንደፈጸሙ ፍንጭ ሊሰጥ ይችላል ተብሎ ይጠበቃል።

የተለያዩ የዜና አውታሮች ጉዳዩ ላይ የሕዝብ ጥቅም ስላለው ብሎም የፍተሻውን ታሪካዊነት ከግምት ውስጥ በመክተት ሰነዱን ለሕዝብ ለማውጣት ችሎቱን ጠይቀዋል። የፍትህ መሥሪያ ቤቱ በበኩሉ ይህ የሚሆን ከሆነ በሂደት ላይ ያለውን ምርመራ ሊጠገን የማይችል ጉዳት ሊያደርስበት ይችላል ሲል እርምጃውን ተቃውሟል።

ከውስጡ የሚወጡት መረጃዎች ሲቀነሱም ሰነዱን "ትርጉም የለሽ" ያደርጉታል ብሏል። ትራምፕ እና ጠበቃቸው ፍተሻው ፖለቲካዊ ይዘት ያለው እና ሕገ ወጥ ነው ያሉ ሲሆን ምንም መረጃ ያልተቀነሰበት ሰነድ እንዲለቀቅ ጠይቀዋል። የትራምፕ ቃል አቀባይ ቴይለር ቡዶዊች ይዘቱን "ለመደበቅ" የሚደረገው ጥረት "አስቂኝ" እና "የመንግሥት ሙስናን ለመደበቅ ያለመ ሊሆን ይችላል" ብለዋል።

በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ የዶናልድ ትራምፕ የጠበቆች ቡድን ምርመራው እንዲታገድ ብሎም ገለልተኛ የሦስተኛ ወገን ጠበቃ እንዲመጣላቸው እና ኤፍቢአይ በፍተሻው ወቅት የወሰዳቸውን ሰነዶች እንዲከታተል መጠየቁን ቢቢሲ ዘግቧል።



## በመረጃ መዝባሪዎች የተዘረፉ ወታደራዊ ሰነዶች ለሽያጭ መቅረባቸው ኔቶ ምርመራ እንዲጀምር አደረገ

የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃልኪዳን (ኔቶ) በመረጃ ሰርሳሪዎች ተመዝብረው በበይነ መረብ ለሽያጭ የቀረቡ ወታደራዊ ሰነዶችን ጉዳይ እየመረመረ ይገኛል። ከተሰረቁት ሰነዶች መካከል የኔቶ አጋሮች በዩክሬን የሚጠቀሙባቸውን የጦር መሣሪያዎች የሚጠቁመው ይገኝበታል።

የመረጃ ሰርሳሪው ቡድን ወታደራዊ ሰነዶች መስረቃቸውን ተከትሎ ኔቶ ዝርፊያው ሊያሳድርበት የሚችለውን ተጽዕኖ እየመረመረ ይገኛል። መረጃ ሰርሳሪዎቹ ከግዙፍ የአውሮፓ መሳኤሎችን ጨምሮ የተለያዩ መሣሪያዎች አምራች ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ሰርቀው ለሽያጭ አቅርበዋል።

ኤምቢዲኤ ሚሳኤል ሲስተምስ የተባለው የጦር መሣሪያ አምራች ድርጅር መረጃዎቹ እንደተሰረቁ አምኗል።ነገር ግን ከሰነዶቹ መካከል ምስጢራዊ የሆኑት የዚህ ድርጅት እንዳልሆኑ አሳውቋል። ድርጅቱ ዋና መቀመጫው ፈረንሳይ ሲሆን፣ ሰነዶቹ የተሰረቁት ከጣልያን እንደሆነና ምርመራ እንደተከፈተ ገልጿል።

የኔቶ ቃል አቀባይ "ከኤምቢዲኤ ተሰረቁ የተባሉትን ሰነዶች እየመረመርን ነው። የኔቶ ኔትወርኮች ላይ ጥቃት ስለመሰንዘሩ የሚጠቁም ነገር አላገኘንም" ብለዋል። የተሰረቁት ሰነዶች በዋናነት በሩሲያ ስውር የበይነ መረብ ገጾች በ15 ቢትኮይን (ወደ 18 ሺህ ዩሮ ገደማ) ለሽያጭ የቀረቡ ሲሆን፣ የመረጃው መጠን 80 ጊጋባይት ይጠጋል።

እስካሁን ቢያንስ አንድ ሰው መረጃውን መግዛቱ ተገልጿል። መረጃ ሰርሳሪዎቹ ያወጡት ማስታወቂያ "በምስጢር የተያዙ ወታደራዊ ፕሮጀክቶች ውስጥ ስለሚሠሩ ሠራተኞች መረጃ አግኝተናል። ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ስለተደረሱ ስምምነቶች እንዲሁም የዲዛይን ዓይነቶች ምሥልና ተንቀሳቃሽ ምስልም አግኝተናል" ይላል ሲል ቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።



## መጋቢ አዕምሮ

# ለምቶ ማልማት፤ ተገንብቶ መገንባት!

**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያን የረገጠ ታዳጊ የዛሬው የመነሻ ታሪካችን ነው:: ታዳጊው ከኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ተወልዶ ከባህርማዶ ያደገ ነው:: ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ አዲስ አበባን እየጎበኘ ያለ ታዳጊ:: የክረምቱ ዝናብ እየዘነበባቸው የታክሲ ወረፋ የሚጠብቁ ሰዎችን ተመልክቶ ግር የተሰኘ:: ለግርታው መፍትሔን ፍለጋ እናቱን "እማማ እኒህ ሰዎች ለምንድን ነው የቆሙት?፤ ለምንስ ወደየቤታቸው አይሄዱም? ለምን ቆመው በዝናብ ይመታሉ? ብሎ ጠየቀ:: የእናቱ ምላሽ ትራንስፖርት እየጠበቁ መሆኑን መንገር ነበር::

ታዳጊው ፊት ላይ ጥልቅ ኀዘን ይነበባል:: በዝናብ የሚደበደቡ ሰዎችን እያየ ሳይጭኑ ማለፍ ይቸግረውና "ለምን የሚያልፉት ሰዎች ሁሉም እየጫኑ አይሄዱም?፤ ለምንስ እኛም ሰው አንጭንም?" ብሎ ይጠይቃል:: እናትም የማያውቁትን ሰው የመጫንን አደገኛነት ለማስረዳት ትሞክራለች:: ልጁ ጥያቄውን በመቀጠል "የሚጭኑትስ ታክሲዎችሽ አደገኛነቱ አይመለከታቸውም እንዴ?" ብሎ ይጠይቃል:: እናትም "እነርሱማ ስራቸው ስለሆነ ነው" ትላለች:: እሺ "መንግሥት ለምን መኪና እንዲያገኙ አያደርጋቸውም?" ሌላ ጥያቄ:: እናቱም የኢትዮጵያ መንግሥት ያን የማድረግ አቅም እንደሌለው ባለመሰልቸት ትመልስለታለች:: ታዳጊውም የኢትዮጵያን መንግሥት እርሱ ከመጣበት የአሜሪካ መንግሥት ጋር በማነጻጸር "የኢትዮጵያ መንግሥት ለምን እንደ አሜሪካ መንግሥት አቅም ያለው አልሆነም?" ብሎ ይጠይቃል:: የእናት ምላሽ አሁንም ይቀጥላል::

እናትና ልጅ የጀመሩትን ጨዋታ ሳይጨርሱ እቤታቸው ደረሱ:: እቤታቸው ደርሰው መክሰስ እየተመገቡ እያሉ በተከፈተው ዜና በኢትዮጵያ ውስጥ ለርሃብ ስለተጋለጡ ዜጎች ዜና ይሰማል:: ሰዎች የሚበሉት አጥተው የሚሞቱበት ሁኔታ ይበልጥ የታዳጊውን ልብ ነካው::ታዳጊው በሚያውቀው ኮልታፋ አማርኛና እንግሊዝኛ እየደባለቀ የሚያገኛቸውን ሰዎች በሙሉ "እንዴት ሰዎች የሚበሉት ያጣሉ?፤ እንዴት ሰው በዝናብ እየተደበደበ መኪና ይጠብቃል?፤ እንዴት ሰዎች መኖሪያ ቤት አጥተው በአንድ ቤት ውስጥ ታጭቀው ይኖራሉ?" ወዘተ እያለ ይጠይቃል::

ታዳጊው ሁሉም ሰው ስለሚያነሳው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ደግሞ ሌላው ግርምትን ፈጥሮበታል:: ሁሉም ችግሩን ወደ ሌሎች ሰዎች መጠቆም ላይ ያተኮረ መሆኑን ይረዳል:: በአብዛኛው ችግሩ ወደ መሪዎች፤ ወደ ፖለቲካ ሰዎች ያነጣጠረ ሆኖ ይቀርብለታል:: ችግሩን ወደ ሌላ በመጠቆም ያስረዱት ሰዎችን ዘላቂ መፍትሔው ምንድን ነው ብሎ ለሚያቀርብላቸው ጥያቄ የሚሰጡት ምላሽ ሊያሳምነው አልቻለም:: የችግር አተያያቸውም ሆነ የመፍትሔ ጥቆማቸው ሊያሳምነው አልቻለም::

ለእርሱ ትልቁ ችግር ሆኖ የሚሰማው ይህን ነባራዊ ሁኔታ ተቀብሎ መደበኛ ኑሮን መኖር መቻሉ ነው:: እንዴት ሰው እንዲህ ባለ ሕይወት ውስጥ በመደበኛነት ይኖራል፤ እንዴትስ ችግሩን ሁሉም ውጫዊ ያደርጋል፤ እንዴት እያንዳንዱ ሰው የራሱን የችግር አስተዋጽኦን ለመረዳት አይሞክርም እያለ ከራሱ ጋር ይሞገታል:: ታዳጊው እንግዳ:: በኖረበት አጭር እድሜው ውስጥ ችግርን እና አፈታቱን በሚያይበት አተያይ ውስጥ ሆኖ::

እናት በታዳጊው ልጇ የሚቀርብላትን የጥያቄ ጋጋታ ባለመሰልቸት ትመልሳለች:: አሜሪካን ሀገር በስራ ተጠምዳ ለብዙ ጊዜ እናቱን ማግኘት የሚቸገረው ልጅ በአሜሪካን ሀገር ያለው የስራ ባህል ምንያህል ለአሜሪካኖች እድገት ወሳኝ እንደሆነ ተረዳ:: እናቱን እንደሚፈልግ ማግኘት ባለመቻሉ ቅር ይሰኝ የነበረው ታዳጊ ከእናቱ የትውልድ ሀገር ሁኔታ በደንብ ተረዳ:: ትክክለኛው አካሄድ የትኛው ነው ሲል ራሱንም ጠየቀ፤ የአሜሪካ ወይንስ የኢትዮጵያ::

ሰዎች ተገቢ የሆነ እረፍት ሊኖራቸው እንደሚገባ ቢያምንም በድህነት ተቆራምዶ በዚህ ደረጃ ከመገኘት ግን በማይመች ሁኔታም ውስጥ ጠንካራ ስራ ሰርቶ ነጻ መውጣት ይገባል ሲልም አሰበ:: መነሻው ግን ራሱ ሰው ላይ መስራት እንደሆነ ተረዳ:: የችግር አተያይም ሆነ የመፍትሔ አሰጣጥ ችግር ያለበት ሰው በሞላበት ሁኔታ እንዴት ዘላቂ ለውጥ ሊመጣ ይችላል ሲል ራሱን ጠየቀ:: ከማልማት በፊት መልማት ያለበት ሰው ይቀድማል አለ:: ይህን ሁሉ ሰው ማልማት እስኪቻል ድረስ ብዙ ዓመት የሚፈጅ መሆኑን ተረዳና የማይመለከተው ነገር ውስጥ ገብቶ የሚጨነቅ መሆኑን ለራሱ ነገረ::

### ለምቶ ማልማት፤

የልማት ጽንሰሃሳባዊ አረዳድ ሰፊ ትንተናን የሚፈልግ ነው:: ስለ ልማት ብዙ ተጽፎም ይገኛል:: በየአካባቢያችን የልማትን ቃል ተጠቅመው ገንዘብ የሚጠይቁ፤ ስብሰባ የሚጠሩ፤ ደንብን ጠቅሰው የሚጠይቁ ወዘተ አሉ:: ልማት ሲመረቅ መሪዎች ሪባንም ሲቆርጡ ተመልክተናል:: በተለይ በምርጫ ሰሞን የሚመረቁ የልማት አይነቶችና የሚቀመጡ የመሰረት ድንጋዮች አማላይ ሆነው እናያለን::

መሪው ሪባን በመቁረጥ የሚያስመርቀው ልማት በልማትነት ትርጉም ውስጥ ይዘልቅ ዘንድ ልማት በሰፊው የተዋሃደን ሊሆን እንደሚገባ ይነገራል:: ማሕበረሰብ በአካባቢው ያለውን ልማት የእኔ ነው ብሎ ተቀብሎ ተገቢን እንክብካቤ ማድረግ የሚችለው እንዴት ነው የሚለው ጥያቄ በልማት ዙሪያ የሚሰሩ አካላት ጥያቄ ከሆነ ሰነበተ:: ልማትን ዘላቂ ማድረግ ተደጋግሞ የሚነሳ ጥያቄ ነው:: ንድፈሃሳባዊ ትንታኔዎችን ማቅረብ ስለማንችል ጎልቶ የሚወጣውን ወሳኝ ነጥብ ግን እናንሳ፤ ለምቶ የማልማትን ሃሳብ::

የሰብዓዊ ምላሽ፣ ዘላቂነት ያለው ልማት እና ዘላቂነት ያለው ሰላም የማይነጣጠሉ መሆናቸውን አንቶኒዮ ጉተሬዝ ይናገራሉ /Humanitarian response, sustainable development, and sustaining peace are three sides of the same triangle:: ሦስቱን በአንድ ቃል ለመግለጽ ብናስብ ዘላቂነት ያለው ልማት ልንለውም እንችላለን:: ዘላቂ ልማት ደግሞ ዘላቂ አልሚ እንደሚፈልግ እናስብ::

ልማት በገንዘብ ብዛት የሚመጣ አይደለም:: ብዙ ገንዘብ ያለው ሰው እንዴት ገንዘቡን መጠቀም እንዳለበት ካለማወቁ የተነሳ የሚገባበት ውድቀት በብዙ ማስረጃዎች ሊቀርብ የሚችል በገንዘብ ብዛት ብቻ የሚመጣ ልማት እንደሌለ የሚያሳይ ነው:: ልማት ድንጋይ መደርደር ብቻም አይደለም:: ቄንጠኛ ድንጋዮችን ደርድረው ዞር ሲሉ ቄንጠኛውን ግንባታ መጠበቅም ሆነ ማስጠበቅ በማይችል የሰው ሃይል የተከበበ ከሆነ ልማቱ ዘላቂነት ጥያቄ ውስጥ ይገባል:: ልማት ሲታሰብ አስቀድሞ መነሳት ያለበት ጉዳይ የሰው ሃይል ልማት ነው:: የሰው ሃይል ልማት መሰረታዊውን ልማት ለማከናወንም ሆነ ለማስቀጠል ወሳኙ መሳሪያ ሆኖ በተቀየሩ ሀገራት የታየ እውነት ነው:: በሰው ሃይል ልማት ላይ ለመስራት እንዲሁ የሚጠበቀው ጥልቀቱና ስፋቱ የታሰበበት መሆኑ የግድ የሚለው ለእዚህ ነው::

ለመንደርደሪያ የሚሆኑ ጥያቄዎችን በወጣቶቻችን ዙሪያ እናንሳ:: ወጣቶቻችንን ስናስብ ፈጥኖ ወደ አእምሮችን የሚመጣው ምን እንደሆነ እንጠይቅ:: አንባቢው ለራሱ ታማኝ ሆኖ እኒህን ጥያቄዎች ራሱን ይጠይቅ ምላሽም ይስጥባቸው:: ዛሬ ወጣቶቻችንን ስናስብ የምናስበው የለውጥ ሃይሎች ሆነው ወይንስ በቀንበር ውስጥ ሆነው የሚገኙ? ወጣቶቻችንን ስናስብ የምናስበው ስራ ለመፍጠር አቅም ያላቸው ወይንስ ተቀምጠው የሚጠብቁ? ወጣቶቻችንን ስናስብ የሚታየን ቤተሰብ መስርተው ፍሬያማ ሕይወትን ለመኖር ዝግጁ የሆኑ ወይንስ ውድ የሆነውን እድሜያቸውን ውሉ በጠፋበት መንገድ ውስጥ የሚያባክኑ? ወጣቶቻችንን ስናስብ የምናስበው ተጽእኖን ተቋቁመው ያለሙትን ለማሳካት የሚሰሩ ወይንስ እንዲሁ የሚባክኑ? እኒህ ጥያቄዎችን ይዘን የግላችንን ምላሽ ሰጥተን እንቀጥል:: የሰጠነው ምላሽ ከሚታየው ልማት በፊት ሊቀድም የሚገባውን የሰውን ልማት ማሰብ የግድ እንደሚል እንደሚያስረዳ ይታመናል::

እንደ ሀገር በስንዴ ራስን አለመቻል በብዙ መንገድ የጎዳን እንደሆነ ሲነገር እንሰማለን:: ከዚህ ጉዳትም ለመውጣት እንደ ሀገር እየተሰራ ያለው ስራ ፍሬያማ ሊሆን እንደሆነ በዜና ሲነገር ሁሉም ሰው ሀሴት ሲያደርግም እንዲሁ:: እዚህ ጋር ግን አንድ ጥያቄ ማንሳት አስፈላጊ ነው:: እርሱም እንዴት እስከዛሬ በስንዴ ራስን መቻል ከባድ እንደሆነ የሚጠይቅ ጥያቄ:: በውሃ ሀብታም በሆነች ሀገር ውስጥ፤ ስንዴ ማብቀል የሚችል ሰፊ መሬት ባለባት ሀገር ውስጥ፤ በግብርና ዓመታትን ያስቆጠረ ልምድ ባላት ሀገር ውስጥ፤ እንዴት እንደ ሀገር የስንዴ ፍላጎትን ማሟላት ሳይቻል ቀረ? ታዳጊው ልጅ ያለንበት ሁኔታ የማይገባው ቢሆን እንዴት ይገርማል:: ቆም ብለን ራሳችንን ስንጠይቅ ያለንበት ነባራዊ ሁኔታ ከብዙ አንጻር ለመረዳት አስቸጋሪ ስለሆነ::

### ሀገር እና ግለሰብ

ከኔልሰን ማንዴላ ንግግሮች መካከል አንዱን እናስቀድም:: በተጨባጭ ይህ ነው የሚባል የሃላፊነት ቦታ ያልተሰጣቸው ነገርግን ማሕበረሰብን ለመገንባት ትልቅ አስተዋጽኦ ስላደረጉ ወንዶችና ሴቶች መኖራቸው የተናገሩት ነው:: There are so many men and women who hold no distinctive positions but whose contribution towards the development of society has been enormous. ሀገርና ግለሰብን ስናገናኝ የምናስበው ግንኙነት የእውቅና ማማ ላይ የመውጣት አለመውጣትን አይደለም:: በእውቅና ማማ ላይ ሳይወጡ ባሉበት ሁኔታ ትርጉም ያለው ስራ የሚሰሩ ዜጎችን ማለታችን ነው::

የሰው ሃይላቸውን በግለሰብ ደረጃ ጠንካራ ማድረግ የቻሉ ሀገራት በተጨባጭ ጠንካራ ሀገር መገንባት ችለዋል:: ለምቶ ማልማት ሲታሰብ እያንዳንዱን ግለሰብ ጠንካራ አድርጎ መስራት ላይ አተኩረው ሰርተዋል:: እያንዳንዱ ግለሰብ እንደ ግለሰብ ትልቅን ማሰብ፤ ሃላፊነትን መወጣት፤ ፈተናዎችን ተቋቁሞ መዝለቅ፤ ወዘተ ቢችል ለምቶ ማልማት ቀላል ይሆናል:: ከመጽሐፍት የምንረዳው ጠንካራ ሀገርን የፈጠሩ መርሆች እጅግ ውስብስብ አለመሆናቸውን ነው:: ቀላል የሆኑ፤ ነገር ግን በተጨባጭ መተግበር በቻሉ መርሆች ውስጥ አስቸጋሪ መንገድን ተጉዘው የሄዱ ወደ ውጤት ደርሰዋል:: እያንዳንዱ ግለሰብ ራሱን ጠንካራ አድርጎ ማቅረብን የሚጠይቅ ሥርዓት ባነበርን ቁጥር በድምር ውጤቱ ሀገር ጠንክራ ትገኛለች::

ለምቶ ማልማት ሲታሰብ ለአንድ ዜጋ የሚኖረን አተያይ ይወስነዋል:: አንዱ ዜጋ ምናልባትም እንደ አልበርት አንስታይን ዓለምን የሚያስደምም ፈጠራ ይዞ የሚወጣ ሊሆን ይችላል:: አንዱ ዜጋ ምናልባትም እንደ ሙሴ ሕዝብን ከባርነት ነጻ የሚያወጣ ሊሆን ይችላል:: አንዱ ዜጋ ምናልባት እንደ ማራዶና ታሪክ የማይረሳው የእግር ኳሱ ሜዳ ልዩ ፍጡር ተደርጎም ሊቆጠር ይችላል:: ጥያቄው ለአንዱ ዜጋ የሚሰጠው ትኩረት ነው፤ ራሱን ብቁ አድርጎ የመገኘትን አስፈላጊነት የሚያሳይ:: ከአንዱ ዜጋ ተነስቶ የሀገር ምስልን መቀየር::

በመደበኛ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ተማሪዎች ከአንድ ክፍል ወደ ሌላ ክፍል የሚያደርጉት ጉዞ እንደሚታወቀው የተለመደ አሰራር ነው:: ተማሪዎች ከአንድ ክፍል ወደ ሌላ ክፍል እያለፉ የሚያደርጉት ጉዞ ግን በትልቅ የሀገር የዓላማ ምስል ውስጥ የተቃኘ መሆን አለመሆኑን ስንመለከት ክፍተትን እናስተውላለን:: ከክፍል አንደኛ እየወጣ የሄደ ልጅ ዲግሪውን በአስደናቂ ውጤት ይዞ ነገር ግን በሀገሩ ውስጥ ያለውን የማልማት ፈተና መቋቋም የማይችል፤ ከራስ ያለፈ እይታ የሌለው፤ ስለ ሀገር ያለው መረዳዳት የተጣመመ ከሆነ ትናንት የሄደበት የመገንቢያ ጊዜው ዛሬ ከእርሱ በሚጠበቀው ልክ እንዳይገኝ ያደርገዋል::

ሀገርን ከእያንዳንዱ ግለሰብ ተነስተን መገንባትን ስናስብ ብቻ ቀላሉ ነገር ቀላል ሆኖ ሊታየን ይችላል::



ራስን በምግበ መቻል እንደ ሀገር ትልቅ ችግር የሆነበትን ምክንያትም ተረድቶ ለመፍትሔም መድረስ ይቻላል:: ዓለም በስንት ጉዳይ በብዙ እርቀት ከእኛ በራቀበት ሁኔታ የተገነባን ለማፍረስ፤ ወይንም ሸጦ ለግለሰብ ጥቅም ለማዋል የሚደረግ አተያይ ዝም ብሎ የመጣ ዝም ብሎም የሚጠፉም አይደለምና መፍትሔው የግድ ይላል:: አንድን ግለሰብ እንደ ግለሰብነቱ የሚሰራበት መስመር መዳረሻውን እያየ የሚሄድበት የመፍትሔ መንገድ::

ለምቶ ማልማት ሲታሰብ በእውቀትም ሆነ በእሴት የተገነባ አንድ ግለሰብ ያስፈልጋል ማለት ነው:: ለአንዱ ግለሰብ የሚሰጠው ትኩረት በቀነሰ ቁጥር ነገሮች አቅጣጫ ስተው ይገኛሉ:: በቀጣይ የሚኖሩ ማናቸውም ሀገራዊ ግቦች እንደታሰበላቸው ላይሆኑም ይችላሉ:: ከአንድ ምእራፍ ወደ ሌላ ምእራፍ የሚደረግ ሀገራዊ ጉዞም ውጤት ያለው ይሆናል:: ከዛሬው ወደተሻለው ምእራፍ እንጂ ከዛሬው ወደ ከፋ የመሄድ ጉዞም አይኖርም:: የመነሻ ታሪካችን ውስጥ የተመለከትነው ታዳጊ ጥያቄዎችም በቀላሉ መልስ ማግኘት ይችላሉ:: እኒህ ጥያቄዎች የሁላችንም ጥያቄዎች ሆነው ለከፍተኛ ስራ እንድንነሳሳ የሚያደርግ ግለሰባዊ ግንባታ ከሁሉ የቀደመው ነው:: ያስቀደሙቱ ተጠቅመዋል፤ ስፍራን ያልሰጡት በሌሎች ላይ ጥገኛ ሆነው ይኖራሉ:: ቤታችን ልንረዳው ያስጠጋነውን ሰው እድሜ ልኩን የሚበላውን እየሰጠን ከመርዳት እንዴት ሰርቶ የራሱን ገቢ ማመንጨት እንደሚችል ብንረዳው ብናሳየው የትኛው ይሻላል ብሎ መጠየቅ ተገቢ ጥያቄ ነው:: የመፍትሔው ጉዞ ግለሰቡ ባለው እውቀት፤ ክህሎት፤ እሴት ወዘተ ውስጥ መሆኑን ተስማምተን ሰፊ ቦታ ሊኖረው ስለሚገባ ግለሰባዊ እሴት እናንሳ::

በተጨባጭ አንዳችን ከሌላችን እንለያያለን:: እያንዳንዳችን ሕይወትን በምናይበት መንገድ፣ በባህሪያችን፣ ለጊዜ በምንሰጠው ቦታ፣ ወዘተ በብዙ መንገድ እንለያያለን:: ሁላችንም አንድ አይነት ሃሳብ በአንድ ጉዳይ ላይ ላይኖረን ይችላል:: አንድን ምስል ተመልክተን የየራሳችንን ትርጉም ልንሰጥ እንችላለን:: የሃሳብ፣ የሃይማኖት፣ የቅደምተከተል፣ የውሳኔ አሰጣጥ፣ የአለባበስ፣ የአመጋገብ፣ የአነጋገር ወዘተ ልዩነቶች አሉን:: ለእኛ የሚመቸን አይነት አለባበስ ለሌላው ሰው አይመቸውም ይሆናል:: ለአንዱ የተመቸው የምግብ አይነት ለሌላው አለርጂ ሊሆን ይችላል:: በብዙ ጉዳዮች ላይ መሰል ነገሮች ይኖራሉ:: በእሴት ዙሪያ የሚኖረን ልዩነትም እንዲሁ ነው::

መልካም የምንላቸው እሴቶች ዙሪያ ሁሉም ሰው በሚባል ደረጃ መስማማት ያለው ነው:: መከባበር እሴት ቢሆን ማን ይጠላል:: መደማመጥ በተግባር ሆኖ ቢታይ ማን ይጠላል:: መረዳዳት ቢሆን ማን ይከፋዋል:: በግለሰብ ደረጃ እንዲተገበሩ የሚታሰቡ እሴቶች የሃይማኖትን አጥር አልፈው የሚያቀራርቡ ናቸው::

እሴትን ከእውቀት ጋር እና ከተዋሃደ ልምድ ጋር አቀናጅተን እንደ ሀገር በጋራ በምናየው ግብ ውስጥ አብሮ መፍሰስ መቻል ለምቶ ማልማት፤ ተገንብቶ መገንባት ላይ ያደርሰናል::


የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
Commercial Bank of Ethiopia
እንኳን ለአሸንዳ ፣ አሸንድዬ፣
ሻደይ እና ሶለል በዓል በሰላም
አደረሳችሁ።
መልካም በዓል!
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
ሁሌም የሚተማመኑበት ባንክ!

# መሠረተ ልማት

## አጂማ ጫጫ የመስኖ ግድብ ፕሮጀክት፤ በውሃ ሃብት የመጠቀም መብት ሌላኛው ማሳያ

መሳኩ ኤሮሴ



ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ሥራ ሲጀምር 14 ሺ እማወራዎችንና አባወራዎችን በመስኖ ልማት ተጠቃሚ ያደርጋል

ጀማ ወንዝ ከዓባይ ገባር ወንዞች አንዱ ነው።ከሰሜን ሸዋ አካባቢ የሚፈልቀው ጀማ ወንዝ በሚፈለገው ልክ ጥቅም ላይ ሳይውል ልክ እንደ ዓባይ ወንዝ ለዘመናት ሲፈስ ቆይቷል።ካለፉት ቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን የጀማ ወንዝን ለመስኖ ጥቅም ላይ ለማዋል ጥረት እየተደረገ ይገኛል።ይህን ወንዝ ጥቅም ላይ ለማዋል እየተደረገ ካለው ጥረት አንዱ ማሳያ በዚህ ወንዝ ላይ እየተገነባ ያለው የአጂማ ጫጫ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ነው።ይህ ፕሮጀክት በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በአንጎለላ ጠራ ወረዳ እየተገነባ ይገኛል።

ይህ የመስኖ ፕሮጀክት በአማራ ክልል ውስጥ በመገንባት ላይ ካሉ ትልልቅ የልማት ፕሮጀክቶች አንዱ ነው።ግድቡ ከአንድ ዓመት ከመንፈቅ በፊት ጥር 2013 ዓ.ም ግንባታው የተጀመረ ሲሆን፤ የፕሮጀክቱን ግንባታ በሶስት ዓመት ለማጠናቀቅ ታቅዶ ስራው እንደተጀመረ ከመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያሳያል።በዚሁ እቅድ ሰኔ 2016 ዓ.ም ለማጠናቀቅ ታቅዷል።

ከሚኒስቴሩ ያገኘነው መረጃ እንደሚያመላክተው፤ ፕሮጀክቱ በ5 ነጥብ 3 ቢሊየን ብር ወጪ የሚከናወን ነው።የግድብና ተያያዥ ስራዎች እና የመስኖና ድሬይኔጅ ግንባታው በመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ባለቤትነት እየተከናወነ ይገኛል፤ ግድቡ 372 ሜትር ርዝመት፣ 45 ነጥብ 5 ሜትር ከፍታ እና 55 ነጥብ 1 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ የመያዝ አቅም አለው።

ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ከአማራ ክልል አጎለላ ጠራና የባሶን ወረዳዎች 10 ቀበሌዎቸ ውስጥ 7 ሺህ ሄክታር መሬት በመስኖ እንዲለማ ማድረግ ያስችላል፤ 14 ሺህ እማወራዎችና እና አባወራዎችን ተጠቃሚ የማድረግ አቅም እንዳለው የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መረጃዎች ያመላክታል።

በግድቡ የሚያዘው ውሃ ወደ ኋላ አምስት ኪሎ ሜትር ድረስ በመተኛት 680 ሄክታር መሬት በመሸፈን ሰው ሰራሽ ሀይቅ ይፈጥራል።ይህ ሰው ሰራሽ ሀይቅ ከመስኖ ልማት በተጨማሪ ለአሳ ልማት እና ለመዝናኛ ሊውል የሚችልም ነው።በዚህም ለአካባቢው ተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያስገኛል።

የአጂማ- ጫጫ መስኖ ልማት ፕሮጀክት በሶስት ሎቶች ተከፋፍሎ ግንባታው እየተካሄደ ያለው። የፕሮጀክቱ ዋና ዋና ስራዎች የግድብ ግንባታና ተያያዥ ስራዎች (ሎት- ሶስት)፣ ከወንዙ ቀኝ በኩል 3000 ሄክታር የሚያለማው ዋና ቦይና የመስኖ መሰረተ ልማት ግንባታ (ሎት- አንድ) እንዲሁም ከወንዙ ግራ በኩል 4000 ሄክታር የሚያለማው ዋና ቦይና የመስኖ መሰረተ ልማት ግንባታ ( ሎት- ሁለት ) ናቸው።ሎት-ሶስት በታኅሳስ 2013 ዓ.ም እንዲሁም ሎት አንድ እና ሁለት በ2014 በጀት ዓመት ነው ግንባታቸው የተጀመረው።

በ2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ የፕሮጀክቱ ሎት-አንድ 20 በመቶ ፣ ሎት-ሁለት 20 በመቶ እና ሎት-ሶስት 34 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ፤ ሎት አንድ 14 ነጥብ 24 በመቶ ወይም የዕቅዱን 71 ነጥብ 20በመቶ ፣ ሎት ሁለት 2 ነጥብ 14 በመቶ ወይም የዕቅዱን 10 ነጥብ 70 በመቶ እና ሎት ሶስት 18 ነጥብ 81 በመቶ ወይም የዕቅዱን 55 ነጥብ 32 በመቶ በቅደም ተከተል ተግባራዊ ማድረግ መቻሉን ሚኒስቴሩ በቅርቡ ይፋ አድርጓል።

በዚህም መሰረት አጠቃላይ የፕሮጀክቶቹን የግንባታ አፈጻጸም በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት ሎት-አንድ 0 ነጥብ 50 በመቶ ወደ 14 ነጥብ 74በመቶ ፣ ሎት- ሁለት 2 ነጥብ 14በመቶ (በዚህ ዓመት የተጀመረ) እና ፣ (ሎት- ሶስት) ከ22 ነጥብ 82በመቶ ወደ 41 ነጥብ 63በመቶ በ2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ማድረስ መቻሉን የሚኒስቴሩ የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ብዙነህ ቶልቻ አብራርተዋል።

ለሎት አንድ የሚያስፈልግ ተጨማሪ የካምፕ ግንባታ ሥራዎች፣ የቀኝ ዋና መስኖ ቦይ ቁፋሮ ሥራ 10 ኪሎ ሜትር ፣ የቀኝ ዋና መስኖ ቦይ የግንብ ሥራ 10 ኪሎ ሜትር ፣የቀኝ ዋና የመስኖ ቦይን ተከትሎ የመዳረሻ መንገድ 10 ኪሎ ሜትር፣ የውሃ ማስተላለፊያ እና ማፋሰሻ ውቅሮች ግንባታ ሥራ መጠናቀቁን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በቅርቡ ይፋ ባደረገው መረጃ አመላክቷል።

ለሎት- ሁለት የሚያስፈልጉ ተጨማሪ የካምፕ ግንባታ ሥራዎች፣ የግራ ዋና መስኖ ቦይ ቁፋሮ ሥራ አራት ነጥብ ሁለት ኪሎ ሜትር፣ የግራ ዋና መስኖ ቦይ የግንብ ሥራ አራት ነጥብ ሁለት ኪሎ ሜትር (በከፊል)፣ የግራ ዋና የመስኖ ቦይን ተከትሎ የመዳረሻ መንገድ 4.2 ኪሎ ሜትር በላይ ተገንብቶ ተጠናቅቋል፡፡

በተጨማሪም (ሎት- ሶስት) በክረምት ወቅት ወንዝ ለመቀልበሻ የሚያገለግለው የግርጌ ግድብ ግንባታ አብዛኛው ሥራ፣ የትርፍ ውሃ ማስወጫ ውቅር ግንባታ አብዛኛው ሥራ፣ የግድብ የታችኛው ውሃ ማስወጪያ ውቅር አብዛኛው ሥራ፣ የመስኖ ውሃ ማስወጪያ ቱቦ ቀበራ ሥራ እና የእግረኛ መተላለፊያ ድልድይ ሥራዎች፣ አብዛኛው የመሰረት ማጠናከሪያ የሲሚንቶ ማጠጣት ሥራ፣ የዋናው ግድብ የታችኛው ክፍል የተወሰነ የድንጋይ ሙሌት ሥራ እና ጊዚያዊ የመዳረሻ መንገድ ግንባታ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

ፕሮጀክቱን የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር በባለቤትነት እያስገነባ ሲሆን፤ የሶስቱም ሎቶች ፕሮጀክት ስራ ተቋራጭ የአማራ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ነው፤ አማካሪው አማራ ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ድርጅት ነው።

ፕሮጀክቱ ገና በግንባታ ላይ እያለ ከአሁኑ ለአካባቢው ማህበረሰብ ትልቅ ጥቅም እያስገኘ ነው። ለበርካቶች ቋሚ እና ጊዚያዊ የስራ እድል ፈጥሯል።በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በተፈጠረ ቋሚና ጊዚያዊ የሥራ ዕድል 2 ሺህ 885 ወንዶችና 1 ሺህ 754 ሴቶች በድምሩ 4 ሺህ 639 እንዲሁም አንድ ተቋራጭ ድርጅት እና አንድ አማካሪ ድርጅት የስራ እድል ተጠቃሚ መሆናቸውን የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የፕሮጀክቱ የፋይናንስ አጠቃቀምም መልካም የሚባል ሲሆን የበጀት ዓመቱ የፋይናንስ አጠቃቀም ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ብር 883,542,563.00 ታቅዶ ብር 808,795,601.16 ወይም የዕቅዱን 91 ነጥብ 54 በመቶ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ መዋሉንም መረጃዎቹ ያመለክታሉ።

ፕሮጀክቱ የተወሰኑ ተግዳሮቶችም አጋጥመውት እንደነበር የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መረጃ ያሳያል።በተቋራጩ የገልባጭ መኪና እጥረት የፕሮጀክቱ አንዱ ተግዳሮት ሆኖ ነበር።በተለይም ሎት ሁለት ላይ ይህ ችግር ታይቷል። የተቋራጭ ድርጅት መረጣ ሂደት ረጅም ጊዜ የወሰደ እና ተቋራጭ ድርጅቱ በወቅቱ ሥራ ያልጀመረ መሆኑ፣ የመሰረት ማጠናከሪያ ሥራ ቢጀመርም በሚፈለገው ፍጥነት ሥራው እየሄደ አለመሆኑ፣ ወረዳው የካሳ ግምቶችን በወቅቱ አስልቶ ቶሎ ወደ ሚኒስቴር መሰሪያ ቤቱ አለመላኩ ከተግዳሮቶቹ መካከል ይጠቀሳሉ።

እንደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መረጃ፤ ችግሩን ለመቅረፍ የተለያዩ የማስተካከያ እርምጃዎችም ተወስደዋል።ተቋራጭ ድርጅቱ ያለበትን የገልባጭ መኪናዎች ችግር በፍጥነት እንዲፈታ በደብዳቤ እና በቃል እንዲያውቀው በማድረግ ችግሩን እንዲፈታ እንዲሁም የባከኑ ጊዚያትን ለማካካስ ተቋራጭ ድርጅቱ ተጨማሪ የሰው ሃይል እና ማሽነሪዎችን ወደ ፕሮጀክቱ በማስገባት የማካካሻ ስራዎችን እንዲያከናውን ጥረት ተደርጓል።ከተቋራጭ ድርጅቱ ጋር በመነጋገር እና ችግሮች እንዲፈቱ በማድረግ የግራውቲንግ ስራ ከዚህ በተሻለ ሁኔታ እንዲፈጥን ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል።

የመስኖ ፕሮጀክቱ ለኢትዮጵያዊያን ትርጉሙ ብዙ ነው።ከግድብነት ባሻገር ተጨማሪ መልዕክትም አለው።የግድቡ ግንባታ በፈረንጆቹ ጃንዋሪ 10 በ2021 በተጀመረበት ወቅት የወቅቱ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ኢንጂነር ስለሺ በቀለ እንዳሉት፤ አጂማ ጫጫ የዓባይ ገባር ወንዝ በሆነው ጀማ ወንዝ ላይ የሚገነባ ፕሮጀክት እንደመሆኑ ኢትዮጵያ በውሃ ሃብቷ የመጠቀም መብቷን የትኛውም ምድራዊ ሀይል ሊያስቆመው እንደማይችል አንዱ ማሳያ ነው።አገሪቷ በዓባይ ወንዝ ገባር ወንዞች ላይ የመስኖ ግድቦችን እየገነባች ስለመሆኗ ሌላ ማሳያ ነው።ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች በዓባይ ገባሮች እና ሌሎች ወንዞች ላይ በብዛት መገንባታቸው በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ያለውን የህዝብ ብዛት ለመመገብ አማራጭ የሌለው ስራ ነው።

በጀማ ወንዝ አቅራቢያ የሚኖሩ አርሶ አደሮች ወንዙ ሲፈስ እያዩ ከወንዙ ሳይጠቀሙ ለዘመናት ኖረዋል። ጀማ ወንዝም ለብዙ ዘመናት ከዓባይ ወንዝ ጋር በማበር የኢትዮጵያን ለም አፈር ወደ ጎረቤት አገሮች ሲያግዝ የኖረ ነው።ወንዙን የአካባቢው አርሶ አደሮች ለዘመናት በትካዜ ሲያዩት ኖረዋል።የግድቡ ግንባታ ተጠናቆ ስራ ሲጀመር የአጂማ ወንዝ ሲፈስ የማየት ዘመን ይቀየራል።

ፕሮጀክቱ የአካባቢውን አርሶ አደሮች በዓመት ዝናብ እየጠበቁ ከማልማት ኋላቀር ግብርና አሰራር በማላቀቅ በዓመት ከአንድ ጊዜ በላይ እንዲያለሙ ያስችላቸዋል።የአካባቢውን ማህበረሰብ የኑሮ ደረጃም ከፍ ያደርገዋል።በዓመት አንድ ጊዜ የሚያመርቱ አርሶ አደሮች ከሁለት ጊዜ በላይ ማምረት ሲችሉ በሕይወታቸው ላይ ተጨባጭ ለውጥ ያስመዘግባሉ።ለአገሪቱ ኢኮኖሚም ከፍ ያለ ሚና ይጫወታሉ፡፡

በተለይም አካባቢው የኢትዮጵያ እና የአፍሪካ መዲና ለሆነችው አዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝ እንደመሆኑ የአካባቢው አርሶ አደሮች በግድቡ ውሃ የተለያዩ አትክልቶች እና ፍራፍሬዎችን በማምረት ለገበያ ማቅረብ ስለሚችሉ የገበያ ችግር ያጋጥማቸዋል ተብሎ አይሰጋም።

በቀጣይም በሌሎች የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ላይ ሲያጋጥሙ የነበሩ ችግሮች እንዳያጋጥሙ አስፈላጊው ርብርብ ሊደረግ ይገባል።የፕሮጀክቱ ግንባታ በአስቸኳይ እንዲጠናቀቅ ከሚደረግ ጥረት ባሻገር ፕሮጀክቱ እንደተጠናቀቀ በአስቸኳይ ወደ ስራ ለማስገባት ከአሁኑ ዝግጅቶች መደረግ አለባቸው።በተለይም የአካባበቢው ህብረተሰብ ስለመስኖ ልማት ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ በትኩረት መስራት ይኖርበታል።የአካባቢው አስተዳደር እና ማህበረሰብም የበኩላቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ "ሁለቱ ወገኖች" ከሚለው ስያሜ ወጥቶ ግጭት ቀስቃሹን ሕወሓት ወደ ሰላም ያምጣ

የፌዴራሉ መንግስት በሰሜን ኢትዮጵያ ለተፈጠረው ችግር ዘላቂው መፍትሄ ሰላማዊ አማራጭ መሆኑን ሁሌም ያስገነዝባል፤ ይሄው እንዲሆንም ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ ይገኛል። ለሰላም የተዘረጋው እጁ ተገፍቶ በሕወሓት ጥቃት አድራሽነት ጦርነት ተከፍቶበት እያለ ቢሆንም ጦርነት ብዙ ዋጋ እንደሚያስከፍል ያውቃልና ለጦርነት ሲቸኩል አልታየም። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በቅርቡ ሶስት አመት ከመዋጋት አስር አመት መወያየት ይሻላል ሲሉ ማስገንዘባቸውም ይህንኑ ያመለክታል።

መንግስት ከጦርነት በፊትም፣ ጦርነት እየተካሄደም፣ ጦርነቱን በድል አጠናቆም ሰላማዊ አማራጭን ይዞ ሲሰራ ቆይቷል። ጦርነት አይቀሬ ሲሆንም ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳትን በቀነሰ መልኩ ለመፈጸም ሃላፊነት በተሞለባት መንገድ ወደ እርምጃ ይገባል። በጦርነት የሚጠፋው ሕይወት፣ የሚደርሰው መፈናቀልና እንግልት፣ የሚወድመው ሀብት በእጅጉ ያሳስበዋል፤ በሚወድሙ መሰረተ ልማቶችና በመሳሰሉት ጥፋቶች ህዝብና አገር ምን ያህል እንደሚጎዱ ይገነዘባል። ከሕግ ማስከበር እርምጃ ማግስት ትግራይን መልሶ ለመገንባት መንግስት ካወጣው መቶ ቢሊየን ብር መረዳት የሚቻለውም ይህንኑ ነው።

እናም መንግስት የኢትዮጵያ ጠላቶች ጥቃት ሲሰነዝሩ ወዲያውኑ ፈጣን ምላሽ ከመስጠት ይልቅ የጥፋት እጃቸውን እንዲሰበስቡ፣ ሰላማዊ አማራጭን እንዲከተሉ በማድረግ ላይ አተኩሮ የሚሰራውም ይሄንኑ ሰብዓዊና ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ለማስቀረት ነው። ሆኖም ወደ ጦርነት ቢገባ መንግስት በአሸናፊነት እንደሚወጣም በሚገባ ያውቃል። ለዚህ ደግሞ አሁን ሁሉን አቀፍ አቅም ተገንብቶ ቀርቶ፣ ሕወሓት የቱንም ያህል ተባባሪ ይዞ በጦርነት ቢሰለፍ እንደማያሸንፍ በህልውና ዘመቻ ወቅት የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች በሁሉም መስክ ከጎኑ ተሰልፈው ኢትዮጵያ ያሸነፈችበትን እውነት ማየቱ በቂ ነው።

ይሄን ያልተገነዘቡት እና "ጦርነት ባህላዊ ጨዋታችን ነው" በሚል ዲስኩር በጦርነት መናርን የመረጡት ሕወሓቶች ድል ቀንቷቸው አያውቅም፤ በተሸነፋባቸው ጦርነቶች ለሚጠፋው ሕይወትና ንብረት ሃላፊነት ተሰምቷቸውም አያውቅም። ባለፉት ሁለት ጦርነቶች የትግራይን ህዝብ ልጆች ማስፈጀቱ አልበቃ ብሎት፣ ለሶስተኛ ጊዜ ጦርነት መጀመሩ ሃላፊነት የማይሰማው አጥፊ ቡድን መሆኑን ያረጋግጣል። ወደ ጦርነቱ የገባውም ትናንት በሰሜን እዝ ላይ የፈጸመውን ክህደት በሚያስታውስ መልኩ የተኩስ አቁሙን ጥሶ፣ ሰላማዊ ንግግርንም ረግጦ ነው።

ለዚህ ደግሞ የትግራይ ሕዝብ ዋጋ እንዲከፍል እያደረገው፤ ልጁን ከጉያው፣ ምግቡን ከጉሮሮው እየነጠቀው ይገኛል። የትግራይ ህዝብ ካለበት ችግር እንዲያርፍ በርካታ ሰብዓዊ ድጋፍ ወደክልሉ ቢገባም፣ በህዝቡ ስም የተገኘውን እርዳታ እየቀማም፣ እየዘረፈም፣ አንዳንዴም ሕዝቡ ልጁን በምግብ እንዲለውጥ እያደረገ ለወታደራዊ ተግባር እያዋለ ነው። ይሄን እኩይ ተግባሩን በአማራና አፋር ክልሎች የወረራ ጊዜ ቆይታው ፈጽሟል። ሶስተኛውን ጦርነት በከፈተበት በአሁኑ ወቅት የዓለም ምግብ ድርጅት 570ሺ ሊትር ነዳጅን በታጣቂዎቹ እንዲዘረፍ ማድረጉን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ይፋ አድርጓል። በዚህም የትግራይን ህዝብና ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ክዷል፤ አጭበርብሯል።



የፌዴራሉ መንግስት ከዚህ አይነቱ ቡድን ጋር ነው ሁለት ጦርነቶችን ያካሄደው፤ በእዚህ አይነቱ ቡድን ነው ሶስተኛውም ዙር ጦርነት ተከፍቶበት ውጊያ ውስጥ እንዲገባ እየተገፋ ያለው። በዚህ ሁኔት ውስጥ ሆኖ ነው መንግስት ለችግሩ ዘላቂው መፍትሄ ሰላማዊ አማራጭ ነው ብሎ ጥቃቱን ከመከላከል ጎን ለጎን ለንግግር እጁን ዘርግቶ አሁንም እየተጠባበቀ ያለው።

የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በሰጠው መግለጫም ያረጋገጠው ይሄንኑ ነው፤ ምክንያቱም አሸባሪው ሕወሓት በአሁኑ ወቅት የከፈተው ጥቃት በጀግናው የመከላከያ ሰራዊትና በመላው የጸጥታ ሃይሎች በተቀናጀ መልኩ በድል እየመከተ ይገኛል። የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ከአሸባሪው ቡድን ለመጠበቅም በወትሮ ዝግጁነት ሁሉም የጸጥታ ሃይላችን በተጠንቀቅ ቆመዋል። ሆኖም የትኛውም ችግር መፍትሄ ማግኘት የሚችለው በሰላማዊ መንገድ ብቻ መሆኑን በመገንዘብ ዛሬም ነገም የሰላም አማራጭ የመጀመሪያ መፍትሔ እንደሆነ መንግሥት በፅኑ ያምናል፤ መሆን የሚገባውም ይሄው ነው።

ለዚህም ነው ተገድዶ የገባባቸውን ያለፉትን ሁለት ጦርነቶች በድል የተወጣው የፌዴራሉ መንግስት ዛሬም ለሰላማዊ ንግግር እጁን እንደዘረጋ ያለው። ትናንት በወጣው የመንግስት ኮሙኒኬሽን መግለጫም ድጋሚ እንደተመላከተው፤ መንግሥት እስከ አሁን ድረስ ለሰላም በሩን ክፍት አድርጎ ቢጠባበቅም ጁንታው ጥቃቱን ቀጥሎበታል፤ በመሆኑም የፌዴራል መንግሥት ያለ ቅድመ ሁኔታ ለመነጋገር የገለጸው ዝግጁነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለጁንታው ፀረ ሰላም ዕብሪት ምንጭ የሆኑ ወታደራዊ አቅሞችን ዒላማ ያደረገ እርምጃ ለመውሰድ የተገደደ መሆኑን አረጋግጧል። ይህ የሚያሳየው ደግሞ ይሄን የሰላም አማራጭ ከመግፋት ይልቅ በአዎንታ ተቀብሎ መጠቀሙ ለሁሉም ይበጃል። ምክንያቱም ዛሬም፣ ነገም የሰላም አማራጭ ጠቃሚው እና ብቸኛው መፍትሄ ነው። ለዚህ ደግሞ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ "ሁለቱ ወገኖች" ከሚለው ስያሜ ወጥቶ ግጭት ቀስቃሹን ሕወሓት ወደ ሰላም እንዲመጣ ማድረግ ይኖርበታል።


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ከሁለቱ መሸሸጊያዎች ጀርባ

**ተገኝ ብሩ**

በብሔርና በሃይማኖት ስር የተጠለሉ ነገር ግን ሃይማኖት መርህም ሆነ የየትኛውም ብሔር ባህል ከሚያዘው በጎ ተግባር ውጭ አገራቸው ላይ የሚያሴሩ ተበራክተዋል። በሃይማኖትና ብሔር ተጠልለው ስውር አጀንዳቸውን የሚያስፈፅሙ፤ ከእምነቱ አልያም ብሔሩ ጋር ፈፅሞ የሚቃረን ተግባር ላይ የሚገኙ ናቸው። ከላይ ሲታዩ የመጠሊያዎቹ ዋንኛ ጠባቂ ይመስላሉ። ከእነሱ በላይ ለሃይማኖታቸው ተቆርቋሪ ከእነሱ በላይ ለብሔራቸው ተሟጋች ፈፅሞ ያለ አይመስልም።

ነገር ግን እነርሱ በዚያ ተሸሽገው እኩይ ተግባር የሆነ አላማቸውን ያስፈፅማሉ። አገር ላይ ያሴራሉ፣ ህዝብን ይከፋፍላሉ፣ በማስመሰል የተካኑ ናቸውና በለበጣቸው ከህዝብ ያገኙት ድጋፍ ተመርኩዘው ህገወጥነትን ያንሰራፋሉ። እነዚህ በሁለቱ ጥላዎች ስር ተጠልለው አገርን የሚያምሱ አስመሳይ የመጋረጃ ጀርባ ተዋናዮች ተው ልንላቸው ይገባል።

በብሔር አልያም በሃይማኖት ለእነሱ መጠቀሚያ ብቻ ናቸው። በእርግጥ አንድም ሊሆኑ አይችሉም። አማኝ መስሎ በእምነት ጥላ ስር ያደባው ተው ተግባርህ ትክክል አይደለም ሲባል "እምነቴ ምናምን ስለሆነ ነው" የሚል መሸፈኛ ያቀርባል። የብሔረሰብ ተቆርቋሪ መስሎ ተንኮል የሚሸርበው ስራህ ህገ ወጥ ነው። ሲባል "ብሔሬ እንዲያ ስለሆነ ነው፤ የተወነጀልኩት" የሚል ውሃ የማያነሳ ምክንያት ይደረድራል። እነዚህ ጉዶች ሃይማኖት አልያም ብሔር ለማስመሰል የሚጠለሉባቸው እንጂ ከእነሱ ተግባር ጋር አይታረቁም።

ዛሬ ኢትዮጵያችን ከውስጥና ከውጭ ኢትዮጵያ ሆና እንዳትቆም በሚፈልጉ አካላት ሴራ ተወጥራለች። አገራችን ከምንጊዜውም በላቀ የዜጎችዋ አብሮነት የልጆችዋ ተገንነት የምትፈልግበት ወቅት ላይ ነች። ታዲያ በዚህ ሁሉ ትግልና ወሳኝ ወቅት ነው፤ እነዚህ አስመሳዮች አገር ላይ ደባ የሚፈጽሙት። በራሱ ውስጣዊ መሻት ላይ የተመረኮዘ እኩይ ምግባሩን ለመወጣት በመጋረጃ ተሰውሮ ደባ ይሰራል። ይህ በኢትዮጵያ ህልውና ላይ አደጋ ሊጋርጡ ከሚያስቡ የውጭ ጠላት ጋር የሚደረግ ስውር ተልዕኮ ማሳያ ነው።

በነገራችን ላይ እነዚህ የመጋረጃው ጀርባ ሴረኞች የቆሙት ለህዝብ አልያም ለእምነት ነፃነት አይደለም። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ውስጥ ውስጡን የሚያሴሩት ከባዕድ የተቀበሉትን ተልዕኮ ለማስፈፀም ነው። ስለምን ጓዳ ጎድጓዳችን ሊበረብር ለመጣ ጠላት ማንነታችንን አንተቦ ያለንን ቀምቶ ለሚሄድ ባዕድ ዓላማ መሳካት የአገር ልጅ በአገሩ ላይ ሊያሴር ይቻለዋል። ዛሬ ላይ ይህቺን ታላቅ አገር አገር ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ውስጥ እልህ አስጨራሽ ትግል የሚያደረጉት ታላላቅ ኢትዮጵያዊያንን ተግባር የሚያንኳስሱ ትናንሽ ኢትዮጵያዊያን በርክተዋል።

በዚህች ታላቅ አገር የሚኖሩ ትንንሽ ሀሳብ አራማጆች የኔ በሚሉዋቸው ብሔሮቻቸው ስር ተጠግተው አገር የማያሻግር ሀሳብ ይወረውራሉ። ህዝብን የሚያጋጭ፤ አብሮነትን የሚንድ አሳሳች መረጃ ያቀብላሉ። ተሰሚነታቸውን ተጠቅመው የሚፈልጉትን እኩይ ተግባር ይከውናሉ።

የሌላኛው አስመሳይ መመሸጊያ ደግሞ ወዲህ ነው። ህዝብ የሚሳሳላቸው እምነት ተቋማት። ጅማሮው ላይ አማኞችን እናንተ ብሩህ ናችሁ፤ እምነታችሁም ከሁሉ የላቀ ብሎ ይቀርብና ለስውር አላማው ያመቻቻል። ቀስ በቀስ ለራሱ ዓላማና ግብ ማሳኪያ ይሆነው ዘንድ በማስመሰል የተንጠላጠለበትን መሰላል ይጠቀማል። ከእምነትና አምልኮ ውጭ የራሱን ዓላማ በስውር ያራምዳል።

የዚህ አይነቱ አስመሳይ የእምነት ጥላ ተንተርሶ የሌላውን እምነት በግልፅ ያነውራል። ሌሎች አማኞችን ያጥላላል። አንዱ አማኝ በሌላው ላይ እንዲነሳ ያደርጋል። በጎነት የሚሰብከው እምነቱ በጥላቻ ይሞላዋል። ይህ ለሴራው ይሆነው ዘንድ ሌላውን የሚሰድብ የሚያንቋሽሽና አስተምሮትን በተሳሳተ መልኩ የሚያራምድ የጥላው ስር ሴረኛ ነው።

ኢትዮጵያ ከሁልጊዜ በተለየ መልኩ መፀንታ መቆም በሚገባት በዚህ ጊዜ፤ ከብሔርና ሃይማኖት ጥላ ስር ያሉ እነዚህ ሴረኞች ትልቅ ፈተና ናቸው። በዚህ ወሳኝ ጊዜ እንኳን የሚፈልጉትን ከማድረግ አይቆጠቡም። ህዝብን ባልረባ ነገር ከመከፋፈል ምዕመናን በትክክል ወደ አምላካቸው ተጠግተው ስለ አገራቸው ሰላም እንዲፀልዩ(ዱዓ) እንዲያደርጉ እድል ከመስጠት ይልቅ በሸረቡት ሴራ አማኝና እምነትን ፈተና ውስጥ ይጥላሉ።

እነዚህ የአገር ጠላቶች በግርግሩ ይበልጥ ላደናግር ያሉ ይመስላል። አገራቸው ከሌለች፣ ነፃነትዋ ከተደፈረ፣ ማንነትዋ ከተናደ የተጠለሉበት ብሔርም ይሁን ሃይማኖት ነፃነት የሌላቸው መሆኑ እንኳን አልተረዱም። እምነቱ ተጠግቶ የእኛ እምነት በሌሎች እየተበደለ ነው ብለው አማኙን ያሳምኑታል፤ ብሔሩን የተጠጋው ደግሞ እኛ የምንበደለው እገሌ በመሆናችን ነው ብለው ያሳምፁታል።

እነዚህ ተጠላዮች ወይም አስመሳዮች በአማኞቹ ቶሎ አይለዩም። ስለዚህም ሳይታወቁ ከፍ ያለ ጉዳት በህዝብ ብሎም በአገር ላይ ያደርሳሉ። አስጠላዮቹም ወይም የተጠለሉበት ሃይማኖትም ሆነ የኔ ብለው ለዓላማቸው መሳኪያ የተለጠፉባቸው ብሔራቸው በእነዚሁ እጅጉን ይጎዳሉ፤ በሴራው ይጠቃሉ። አንዴ አይናችን ገልጠን ብናያቸው ጥላውን ገፈን ማንነታቸው ብንመረምረው እነዚህ የጥላው ስር ሴረኞች ባዶነታቸውን በተረዳን ነበር።

ፈፅሞ ለብሔራቸው መብት የማይሰሩ መሆናቸው፤ ለእምነታቸው ያላደሩ አስመሳይ እንደሆኑ ፍንትው ብሎ በታየንም ነበር። ይሄ ግን ጊዜ ይጠይቃል። በተለይ በዚህ አገር በጠላት ተከባ ፈተናዎችዋ በዝተው ሁሉም በስሜት በሚፈርድበት ጊዜ ሜዳው ይመቻቸዋልና እውነት የያዙት አስመሳዮቹ ብቻ ይመስላሉ። የተደበቁበት ታላቅ እምነት ወይም ብሔር ለእነሱ መከታ ለስውር ሀሳባቸው መደበቂያ ይሆናልና። ነገር ግን ኢትዮጵያ ከሁሉ ከፍ የምትል፤ ዘመንን የምትሻገር መሆንዋን አልተረዱም።

ህዝብ ቆም ብሎ እነዚህ ማጋለጥና ተው ሊላቸው ይገባል። የሚነግሩትን ሰምቶ ለምን? ብሎ ማስላት እንዴት ብሎ መመርመር ይገባዋል። አማኝ ለእምነቱ ያደረ መልካም ነገርን አብዝቶ የሚተገብር ከወገኖቹ ጋር በፍቅር ያለውን የሚጋራ ሆኖ ሳለ፤ ስለምን? የሌሎችን እምነት ያንቋሽሻል? ለምንስ መልካም ነገር ከመስበክ ይልቅ የሌላው እምነት ተከታይ እየሰደበና በሌላው ላይ እየተሳለቀ ከአምላኩ ትዕዛዝ ተቃርኖ ይቆማል? አዎን እንዲህ ብሎ መጠየቅ ይገባል።

እምነት በበጎ የሚያዝ ከመጥፎ ነገር የሚከለክል ሆኖ ሳለ ለሌሎች መጥፎ ሁኑ ሊል አይችልም። ይሄኔ አማኙ መመርመር ይገባዋል። አስመሳዩ ግን አማኝ ነኝ ብሎ፤ በእምነት ጥላ የተሸሸገ እንጂ በአምላካዊ በጎ ተግባር የታነፀ የእምነቱን ቀኖና የሚያከብር ለሰው ልጆች በጎ የሆነ አስተሳሰብ የለውም። በሃይማኖት ጥላ ስር የራሱን ድብቅ አላማ ማስፈፀም ነው ግቡ። በብሔሩ ተሸሽጎ ለድብቅ አላማው የሚያላዝነውም እንዲሁ።

የሁሉም እምነቶች መሰረት በጎነት የአማኞች ተግባርም መልካምነት ለሰው ልጆች ምቹ መሆንን ማስተማር ነው። ለአገር አብሮ መቆም ለወገን ችግር መድረስ ተደጋግፎም ክፉን ጊዜ መሻገር እንደሚገባ መስበክ ነው ዋንኛ ግቡ። ስለዚህም ነው በዚህ በጎ ጥላ ስር ያለውን መሰሪ መለየት የሚገባው።

ልክ እንደ እምነቱ ሁሉ በብሔሩ ጥላ ስር ያደሩ ለብሔሬ ተቆርቋሪ ነኝ፤ ለህብረተሰቤ ተሟጋች ብለው እራሳቸውን እላይ የሰቀሉ አስመሳዮች አሉ። ተቆርቋሪ መሳይ ነገር ግን የተጠለሉበትን ብሔረሰብ የማይመስሉ ለእርሱም እውነተኛ አርነት የማይሰሩ መሆናቸው ነው ከባዱ ነገር። ስለማህበረሰቡ የሚጨነቅ ስለወገኑ የሚቆረቆር ቂምና ጥላቻን በሌላው ላይ አይሰብክም።

ማህበረሰቡ ባህልና ወጉ በሌላው እንዲከበር የሌላን ማህበረሰብ ባህልና ወግ ማክበር ወሳኝ መሆኑን ይረዳል። እነዚህ ተጠላዮች ግን ወክልንህ አልያም እኔ ለአንተ ቆምኩልህ ይበሉት እንጂ ተግባርና አካሄዳቸው ሁሉ ማህበረሰቡን ለእንግልት የሚዳርጉ የአብሮነት እሴቱን የሚሸረሽሩ የአገር ህልውናም የሚያናጉ ናቸው።

እነዚህ የሁለቱ ጥላ ስር ሴረኞች ዓላማ ግልፅ ነው። የራሳቸውን እኩይ ዓላማ በተጠለሉበት ማንነት ውስጥ በመሰወር ማስፈፀም ነው። ለእነዚህ መድኃኒት ደግሞ እኛ አንድ ሆነን ቆመን አንድነታችን ሊንድ እኛን መስሎ የሚቀርበንን ተው ማለት ነው። በአገራችን ህልውና ላይ አደጋ ሊጥል የሚያሴርን መዋጋት እንደ ዜጋ የሁላችን ኃላፊነት መሆን ይገባዋል።

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ካልሻረው ጦርነት ጠባሳ ስር ...

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

የልጅነት ሕይወታቸው ብዙም ፈተና የለበትም።ይህ አጋጣሚ ታዲያ ያን ጊዜ በመልካምነቱ ብቻ እንዲያስቡት አድርጓል።የቤተሰቦቻቸው ሕይወት ግብርና ላይ ያረፈ በመሆኑ ያሻቸውን ከእፍታው እያገኙ አድገዋል።በተለይ የእረኝነት ውሏቸው ለእሳቸው ሥራ ብቻ አልነበረም።ይህ ዘመን ከሚያግዷቸው ላሞች ጡት ጉንጭ ሙሉ ወተት አስጎንጭቷቸዋል።

በየቀኑ በጉሮሯቸው የሚንቆረቆረው ትኩስ ወተት ዛሬ ከጥንካሬ አልፎ ልዩ ትዝታቸው ነው። ይህ የልጅነት ዕድሜ ለአብዱልከሪም ሰይድ አንድም ከቤታቸው፣ ሌላም ደግሞ ከእድሜ እኩዮቻቸው የሚቦርቁበት ጊዜ ነበር።ይህን ባሰቡ ጊዜ ልጅነታቸው ይናፍቃቸዋል።ዳግመኛ ወዳለፉት መንገድ መመለስን ይመኛሉ።

የእሳቸው ልጅነት በልቶ ማደር ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ማሰብን አስተምሯቸዋል።ነፍስ ካወቁበት ጊዜ አንስቶ ለቤተሰቡ ጉሮሮ የአቅማቸውን ማድረግ ልምዳቸው ነበር።አብዱልከሪም ልጅነትን አልፈው አዋቂ መሆን ሲጀምሩ ግን ማንነታቸው በውጣውረድ የሚፈተንበት ጊዜ ደረሰ።ወቅቱ ሁሉም እንደአቅሙ ተፍጨርጭሮ ለመኖር ዋጋ መክፈል ግድ የሆነበት ነበር። ይህን ሲረዱ ችግርንና ሰርቶ የማደርን ዋጋ ቀምሰው አጣጣሙት።

### የሚቻለው ያልተቻለ

አብዱልከሪም ተወልደው ያደጉት ራያ ውስጥ ‹‹ቅልሽ›› ከምትባል ቦታ ነው።በደስታ የተሻገሩት ልጅነት ለወጣትነት ቦታውን ሲለቅ አስቸጋሪውን ሕይወት የማየት አጋጣሚ ተፈጠረ።ጊዜው የዘመነ ደርግ ጦርነት ነበር። በወቅቱ ለዚህ ዝግጁ አይደሉምና እሳቸውን ጨምሮ ሌሎች በእሳት የሚማገዱበትን ፈታኝ ጊዜ ለማለፍ ቀያቸውን ሊለቁ ግድ ሆነ። ከመሳሪያ ድምጽ ርቀውም ያገኙትን ሠርተው ለማደር ተመኙ።ይህ ውሳኔያቸውም ዝቅተኛ በሚባለው ሥራ እንዲሰማሩ አስገደዳቸው።

አብዱል ከሪም ጦርነቱን ሸሽት ከቀን ስራ ጀምሮ፣ ያልተሳተፉበት የስራ መስክ አልነበረም።ከሰው እስኪለምዱ ፈተና ቢገጥማቸውም በልቶ ለማደር ጠንክሮ መስራት ግድ ነበር።በተለይ ዓመታትን በገፉበት የኮንስትራክሽን ሙያ የጉልበት ስራ መተዳደሪያቸው ሆኖ ዘልቋል።የዛኔ የለመዱት የጭቃ ቤቶች ግንባታ እስዛሬ የገቢ ምንጫቸው እንደሆነ ነው።

አንዳንዴ ጥጥ ከሚመረትበት አካባቢ ሲገኙ ከሪም የሥራ ዘርፋቸውን ቀይረው ይተጋሉ። ኩትኳቶና ጥጥ ለቀማም እንጀራቸው ነበር።በተለይ በዚህ ሥራ ውጤታማ እንደሆኑ አይረሱትም ።ከሆዳቸው አልፈው የሚቆጥቡት ገንዘብ ጭምር ቋጥረውበታል። ቆይቶም ወደ ንግዱ ዓለም ለመግባት ምክንያታቸው ነበር።

በዚህ ስራ መነሻ በኮንትሮባንድ ንግድ ከጅቡቲ አዲስ አበባ ተመላልሰው ጥሩ ጥሪት አስቀመጡ።ይህ አይነቱ ሥራ ስጋት የሞላውና የሚተማመኑበት አይደለም።በወቅቱ ግን ለእሳቸውና ለብዙዎች ቋሚ መተዳደሪያ ነበር።እንዲህ መሆኑ ከጉልበት ስራ እንዲላቀቁና ቤተሰብን እንዲያግዙ ረድቷቸዋል።

የማታ ማታ ግን የጀመሩት የኮንትሮባንድ ንግድ መጨረሻው አላማረም።በድንገት ከትልቅ ኪሳራ ጣላቸው።ይህ ክፉ አጋጣሚም ዳግመኛ ወደ ቀን ሰራው መልሶ ከቀድሞው ድካም አገናኛቸው።

አሁን አብዱል ከሪም ያላቸው ምርጫ በጉልበት ለፍቶ ማደር ብቻ እንደሆነ አውቀዋል። በልቶ ለማደር፣ ቤተሰብን በተሻለ ለማገዝ ደግሞ ከቀን ሥራ አለፍ ያሉ ገቢዎች ሊኖሩ ያሻል።በኑሮ ከፍ ብሎ ለመለወጥም ሳይታክቱ ሥራ ማፈላለግ የግድ ነው። ይህን ለማሳካት ያልሄዱበት መንገድ፣ ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም።

የነበሩበት ሁኔታ ግን ላሰቡት ሁሉ ዕድል አልሰጣቸውም።ለስራ ማልደው ቢተጉም የጉልበታቸውን በረከት ሊጠቀሙ አልቻሉም።የእሳቸው ኑሮ አፋር ‹‹ዳሳጊርታ›› ነውና በጦርነቱ ተጎድቷል።ሁሉም ጭንቀትና በፍርሃት እየኖረ ነው ።በዚህ ውስጥ ሆኖ ስራን ማሰብ ደግሞ ፍጹም አይታሰብም።

እሳቸው በጦርነቱ ቤት ንብረትን ከማጣት ባለፈ



የዛሬን የዕለት ጉርስ መሙላት ተቸግረዋል።የባለቤታቸውን ጨምሮ የልጆቻቸውን ጉሮሮ የሚሞሉት በቀን ሥራ ከሚያገኙት ገቢ ነበር።ዛሬ ደግሞ ይህ መቀጠል አልቻለም።ጦርነቱ በአካባቢው የከፋ ጉዳትን አሳርፏል።አሁን ስራና ሰራተኛ ይሉት እውነት የሚሞከር አይደለም።የሚሰራም፣ የሚያሰራም የለም።በርካቶች ጉልበታቸውን ገብረው የላባቸውን ለማግኘት እየተፈተኑ ነው።

በዚህ ጊዜ አብዱልከሪምና ቤተሰቦቻቸው ጦም ማደር ልምዳቸው እየሆነ ነው።ሁሌም ግን ‹‹ነገ ሌላ ቀን ነው›› ሲሉ ተስፋ ያደርጋሉ። እስከ ስምንተኛ ክፍል ፊደል የቆጠሩት አባወራ ይህ ዕውቀታቸው ብዙ እንደማያራምዳቸው ያውቃሉ።የእሳቸው ልምድ በጉልበታቸው ድካም፣ በላባቸው ወዝ ሰርቶ ማደር ነው።

ከአፋር ባህላዊ ቤቶች ጋር አጥርን አስውቦ ማሳመር የእጅ ጥበብን ይጠይቃል።አብዱል ከሪም በዚህ ሙያ የተካኑ ናቸው።ዛሬ ግን ፈላጊ አላገኙም።ስራ ባለማግኘታቸው በትምህርት ላይ ያሉ አምስት ልጆቻቸውን የሚያበሏቸው እያጡ ነው።ባለቤታቸው በየቤቱ እንጀራ እየጋገሩ ልብስ ያጥባሉ።በዚህ ገቢ ቤቱ ጥቂት ቢደጉምም ስራው እንደልብ የሚገኝ አልሆነም።እናም በእርዳታና አልፎ አልፎ በሚያገኝ ገንዘብ ብቻ ሕይወታቸው እየተንገዳገደ ቀጥሏል።

### ችግር ያልፈታው ትዳር

አብዱል ከሪም ዛሬ ላይ የግራ ጎናቸው ሆና የልጆች በረከት ስለቸረቻቸው ሴት ብዙ ያስታውሳሉ።በአፋር ብዙ ዓመታትን ሲያሳልፉ ኑሯቸው በብቸኝነት ነበር። እንዲህ መሆኑ ችግራቸውን የሚጋራቸው ሰው እንዳይኖራቸው አድርጓል።ወልዶ መሳምን ቢፈልጉም ሳይሳካላቸው ቆይቷል።ሁሌም ሃሳባቸውን ለመሙላት በየአቅጣጫው ዓይናቸውን ማማተር ልምዳቸው ሆነ።እንዳሰቡትም አንዲት ጉብል ላይ ቀልባቸው አረፈ።ለመግባባት ጊዜ አልፈጁም።ጎጆ ቀልሰው ትዳር መሰረቱ ።

ጥንዶቹ በእኩል ለፍቶ አዳሪዎች ናቸውና ደስተኞች ሆኑ።አንዳቸው የሌላቸውን ሀብትና ገንዘብ ሽተው አልተገናኙም።ልፋታቸው የጋራ፣ ጥቅማቸው የትዳራቸው ሆኗል።

ንጹህ አየር በሚመላለስበት የአፋር ቤት የሚኖሩት ቤተሰቦች ዛሬም ከነችግራቸው ደስታ አልተለያቸውም።የአባወራው ወይዘሮ በቤቷ እንግዳ እንግዳ መጥቶ አይደለም እረፍት ይሉትን አታውቅም።እኛ በደረስን ጊዜ ግን ሕመም አሸንፏት ተኝታ ነበር።እንዲያም ሆኖ ቤት ያፈራው ለእንግዶች ይቀርብ ዘንድ ስትወተውት አስተውለናል።

ጥንዶቹ ከደጅ ውለው በቋጠሩት ገንዘብ ያቆሙት ትዳር ፍቅር የሞላበት እንደነበር ከሁኔታቸው ተረዳን።ሁሌም ችግር ባይጠፋም ውለው ሲገቡ እፎይ ይላሉ። አድረው ሲወጡ የሚመለሱበትን እያሰቡ ይጽናናሉ። በጎጇቸው ውስጥ ችግር ብቻ እንዳይነግስ ፍቅርና መተሳሰብ ፣ ሳቅና ጨዋታቸውን ያበረታሉ።

አብዱልከሪምና ትዳር ከተገናኙ ዓመታት ተቆጥረዋል። ዛሬ እንደ ትናንቱ መስራት አልቻሉምና ችግራቸው ቀጥሏል።አሁን በጎጆ በረከት እየተዋዛ ተስፋ የሚሆናቸው አንዳች ነገር የለም።ጊዜያት እየተቆጠሩ ነጉደዋል።ለእነርሱ ግን አንዳች ጠብ ያለላቸው የለም። በተለይ ባተሌዋ ወይዘሮ እንደቀድሞው ደፋ ቀና አለማለቷ እጅግ አሳስቧቸዋል።ቢያንስ የእርሷ ሥራ ቤቱን ለመደጎም ያስችል ነበር።የእርሳቸውም የሥራ ፍለጋ ጥረት የእለት ጉርሳቸውን መሙላት የሚችል አልሆነም።

አብዱልከሪም በአፋር በተከሰተው ጦርነት ብዙ ነገራቸው ተወስዷል።ተስፋቸው የጨለመ መስሎም ይታያቸው ይዟል።በተለይ አሁን ‹‹ተስፋ በሌለበት፣ ተስፋን ማለምለም እንዴት ይቻላል?›› የሚል ጥያቄ ላይ ናቸው።ነገር ግን በትዳራቸው ፣ በፍቅራቸው ብርሃን ጨለማውን እንደሚገፉት ያምናሉና የቻሉትን ለማድረግ እየጣሩ ነው።

### የአጋጣሚ ክፉ

ውሎ ለማደር፣ አድሮ ለመነሳት ያህል በቀጠለው ሕይወት ጦርነት ሲከሰት ይይዙት፣ ይጨብጡት ይጠፋል።ማንን ጥሎ ማንን ማዳን ፣ የቱን ይዞ የቱን መጣል እንደሚኖር ግራ ይገባል።ሆድን የሚሞላ ነገር በሌለበት ዓለም ድንገተኛ አጋጣሚዎች ሲከሰቱ ደግሞ መከራ ብቻ ሳይሆን ሞትም ጭምር ይሆናሉ።የረሀብና ጥምን እውነታ ፣ የመለያየትን ጥግ ይህ ጦርነት በሚገባ አሳይቶ ፈትኗቸዋል። 42 ኪሎ ሜትርን በእግራቸው ተጉዘው ጫካን ቤቴ ብለው ወራትን እንዲቆጥሩ ተገደዋል።

ከጫካ ኑሮ መልስ ወደቀያቸው ባቀኑ ጊዜ ጁንታው አንዳች ንብረት እንዳልተወላቸው አወቁ።ሕይወት ይቀጥል ዘንድ በባዶ ሜዳ ላይ የአፋር ጎጇቸውን ቀልሰው ሊኖሩ ተገደዱ።ያም ቢሆን ‹‹ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል›› አይነት ነው።በዚህም ትከሻቸው ከሸክም ባልወጣበት ወቅት ክፉውን አጋጣሚ መቋቋም ተሳናቸው።

ቤተሰቡን የሚያኖር ሥራ የለም ፣ የሚበላ የሚቀመስም እንዲሁ።በዚያ ላይ በርከት የሚለው ቤተሰብ በጠባቧ ቤት መኖር ጀምሯል። ሕይወት በዚህ መልክ እየተጓዘ ነው። ትንሽዋ ቤት ሰፊውን ቤተሰብ አስተቃቅፋ እንደነገሩ ታሳድራለች።

ለአብዱርከሪም ጉልበታቸው ማለት የቤታቸው ዋልታ ነበር። የእንጀራቸው ምንጭ፣ የመኖራቸው ትርጉም።ዓመታትን የተሻገሩበት ድልድይም ነው። ዛሬ ግን ይህን ማድረግ ከማይችሉበት ደርሰዋል።ቀድሞ የእሳቸውን እጅ የሚፈልጉ ዛሬ የሰው እጅ ናፋቂ ሆነዋልና አይፈልጓቸውም።ስለዚህም ቤተሰቦቻቸው በችግር ሊፈተኑ፣ ግድ ሆኗል።

ተስፋ መቁረጥ ደግሞ እርሳቸውን ፉከከሩ ውስጥ አያስገባቸውም።ሩጫና ትግል በሞላባት ዓለም ከችግር የተዳመረውን ድንገተኛ ሁነት ማጥፋት ካልተቻለ አደጋው የከፋ ነው።‹‹በቃኝ›› ብሎ መቀመጥም የባሰ ይጥላል።እናም ሥራ አገኙም፣ አላገኙም ማልደው መነሳትን የትግሉ አንዱ ማሳያ አድርገውታል። አንዳንዴ የጉልበት ሥራ ሲገኝ ጥቂት ይሞክራሉ።ያም ሆኖ ከእጃቸው የሚደርሰው ገንዘብ ጥቂት ገንዘብ ጉዳይ አይሞላም።

ከቀን ስራው የሚመጣው ገቢ ቁራሽ ዳቦን ለሚሹት ልጆቻቸው ጉሮሮ የሚበቃ አይደለም። ይህ እውነት ለአባወራውና ለእማወራዋ ከአቅም በላይ እየሆነ ነው። ችግር እግሩን ተክሎ ገቢና ፍላጎታቸውን ሳይጣጣም ቀናትን እያስቆጠረ ይገኛል።ደግነቱ ልጆቻቸው ብርቱ ናቸው።አስቸግረው አያውቁም።ራበን፣ ጠማን ሳይሉ ያገኙትን ቀምሰው ያድራሉ።

አንዳንዴ የእርዳታ እህል ሲመጣና ከበጎ አድራጊዎች ስጦታዎች ሲገኙ ደስተኞች ናቸው ።ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ጎዶሏቸውን ይሞላሉ።ማገሩን አሮጌ ጨርቅ በወተፈው፣ ጣሪያው ሙሉ ዝናብ በሚያፈሰው ጎጇቸው ሆነውም ተስፋ አድርገው ይኖራሉ።

### አብዱርከሪም ዛሬ

አሁንም ከእነ አቶ አብዱርከሪም መኖሪያ ውስጥ ነን ። ጊቢው እንደማንኛውም የገጠር ቤት አጥር ዞሮታል።በሩን ለመለየት አስቸጋሪ ይመስላል።እንግዶቹን የምትመራው ሴት በምታውቀው መልኩ ከፈተችልንና ወደውስጥ ዘለቅን።እንዲህ ባይሆን በቀላሉ ለመግባት እንደማንችል ግልጽ ነው።

ወደቤት በዘለቅን ጊዜ ባለቤታቸው በውስጥ፣ እርሳቸው ደግሞ መናፈሻ በሚመስለው የአፋር አጥር ቤት ውስጥ ጋደም ማለታቸውን ተመለከትን። በቤቱ የሚላስ የሚቀመስ እንደሌለ ያስታውቃል።ወይዘሮዋ በህመም እርሳቸው ደግሞ ስራ በማጣት ከቤት ውለዋል። ይህ ደግሞ ዛሬም የቤተሰቡ ጓዳ በችግር እንዲፈተን አድርጓል ።በነገ ላይ ተስፋ ከመጣል ውጪ አማራጭም አልሰጣቸውም።ደከመኝ ካሉ ብዙ ነገሮች አብረው እንደሚጥሏቸው ያውቃሉና ለልጆቻቸው የተሻለ ነገር ለመስጠት ሥራ በአገኙበት አጋጣሚ ሁሉ ደፋ ቀና ይላሉ።ነገ ትናንት ሊሆን አይችልምና በነገ ፈረስ ዛሬን አይጋልቡም።ሁሌም ለእሳቸውና ለልጆቻቸው አዲስ ዓለምን ለመስጠት ይተጋሉ።

ጦርነቱም ቢሆን ሁሌም ችግር ብቻ እንደማይኖረው ያምናሉ።ከችግሩ ማዶ ብርቱነት አለ።በየቀኑ ጥንካሬ ይወለዳል።አዲስ የሆነ ነገን ለመፍጠር ጥረታቸው ይቀጥላል። ችግር ተስፋቸውን ቢያጨልምም ቆይቶ እንደሚያነጋ ያውቃሉ።እንዴት ካሉ ደግሞ ባልተበገረ ተስፋ ውስጥ ሆነው በመሥራት ነው።በጦርነቱ የተፈጠሩ ችግሮችም ለእርሳቸው ተስፋ ፈንጣቂ የሚሆኑበት ጊዜን ያመጣል ብለው ያስባሉ።ምክንያቱም ጦርነቱ ያወደማቸው ዳግም ሲገነቡ ለቀን ሰራተኛው ከሪም ዕድልን ያመጣሉ።ቦታውን ከእርሳቸው ቀድሞ የሚፈናጠጥበት የለም።

‹‹እውነተኛ ሰላም የሚረጋገጠው የጦር መሳሪያዎችን ድምጽ ባለመስማት ብቻ አይደለም።ችግር ቢከሰትም ለፍቶ ማደርና የእለት ምግብን ማግኘት ሲቻል ነው። ሰላም ማለት የጦርነት አለመኖር ብቻ ማለት ሳይሆን የፍትህ፣ የልማት፣ የአንድነትና የምድርን በረከት በእኩልነት መቋደስ ጭምር ነው።›› የሚሉት አብዱርከሪም፤ አሁን ያሉበት ሁኔታ በእጅጉ ያሳስባቸዋል።

ከሪም ተፈጥሮን እንኳን መጠቀም እንዳይችሉ ሆነዋል። ለማረስ ቢሹም መሬቱ በፈንጅ ተሞልቷልና ሊረግጡት ያሰጋል።በየሰው ቤት ለመሥራትም የቀድሞው አይነት ዕድል የለም።ፍራቻ፣ ነግሷል።አሰሪ አካላትም በተለያዩ ምክንያቶች ከመግባት ተቆጥበዋል።እናም ከሪም ተስፋቸው አንድና አንድ ብቻ ሆኖ ያቺን የሰላም ቀን እየናፈቁ ነው። መንግሥት በጦርነቱ የወደሙትን ዳግም እገነባለሁ ያለውን ቃል በተስፋ ይጠብቁታል።

እርሳቸው የቀን ሰራተኛና ግንበኛ በመሆናቸው ደግሞ ትልቅ እድል እንዳላቸው ተስፋ አድርገዋል።አካባቢያቸው ትልቅ ጉዳትን ካስተናገዱት መካከል የመጀመሪያው በመሆኑ በቅርቡ የሚጀመረው የትምህርት ቤት ግንባታ አንዱ የሥራ አማራጭ እንደሚሆን ያስባሉ። የትምህርትቤት ግንባታው ደግሞ ገና ከአሁኑ ጅማሬው መልካም ሆኗል።እንዲህ መሆኑ ተስፋቸውን አለምልሟል።ከዚያ በኋላ በጉልበታቸው ድካም፣ በላባቸው ወዝ የቤተሰቦቻቸውን አንገት ቀና እንደሚያደርጉ ተስፋ አላቸው።

ጦርነት ለፍጥረታት ሁሉ መቅሰፍት ነው።የእጅን ፍሬ ያስጥላል፣ ሕይወትን ነጥቆ ሙሉ አካል ያሳጣል።እንዲህ በሆነ ጊዜ የንጹሃን ነፍሶች ከዛፍ እንዳሉ ወፎች ይመሰላል።ጎጇቸው ይፈርሳል።ሀብታቸው ይበተናል።አገር ቀያቸው ይወድማል።ይህ መልከ ብዙ መቅሰፍት ስደትና መፈናቅልን አስከትሎ መልካም ታሪክን ይሽራል።የአቶ አብዱልከሪምና ቤተሰቦቻቸው ሕይወትም በዚህ አይነቱ እውነታ የተቃኘ ነው።ነገ ያሰቡት ሞልቶ ሰላማቸው እስኪመለስ ያረፈባቸው ደማቅ ጠባሳ ምልክታቸው ሆኖ ይቀጥላል።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የሲዳማ ባህላዊ ምግብን ከቤት ወደ አደባባይ ያወጡት የባህል ምግብ ቤት ባለቤት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ኢትዮጵያ የቱባ ባህሎችና የአኩሪ ታሪኮች አገር ስለመሆኗ ዓለም መስክሯል:: ከቱባ ባህሎቿ መካከልም ባህላዊ ምግቦቿ ይጠቀሳሉ:: የባህላዊ ምግብ አይነቶቹ፣ አዘገጃጀታቸውና የአመጋገብ ሥርዓታቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው:: የየዘመኑ ትውልድም ይህንኑ አኩሪ ባህል እየተቀባበለ እዚህ አድርሶታል::

በዛሬው የስኬት ገጻችንም የሲዳማ ባህላዊ ምግብን በሆቴላቸው በማዘጋጀት ለሕብረተሰቡ በማቅረብ ታዋቂነትን ያተረፉ እንግዳ ይዘን ቀርበናል:: እንግዳችን ብዙም ከቤት ውስጥ ፍጆታ ውጭ ማለፍ ሳይችል ዘመናትን ያስቆጠረውን ይህን ባህላዊ ምግብ ወደ አደባባይ ሲያወጡ ነገሮች አልጋ ባልጋ አልሆኑላቸውም::

ከቤተሰብ ጀምሮ በአካባቢው ማሕበረሰብ ጭምር ተቃውሞ ገጥሟቸውም እንደነበር ያስታውሳሉ:: ለመጀመሪያ ጊዜ የምግቦቹን ስም ዝርዝር በሜኑ ላይ በማውጣት ለደንበኞች ሲያቀርቡ ችግር ገጥሟቸውም ነበር:: ያልተለመደ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ባህላዊ ምግብ በቤት ውስጥ ከእናቶቻችን ውጭ እንዴት ይቀርባል፤ በሚል ለጊዜው ተፈትነዋል::

እርሳቸው ግን ፈተናዎቹን በማለፍ ባህላዊ ምግቡን በሆቴላቸው እያቀረቡ ይገኛሉ፤ በዚህ ብቻም ሳይወሰኑ በውጭው ዓለም የማስተዋወቅ ራዕይ ሰንቀው እየሠሩም ይገኛሉ:: በአሁኑ ወቅት ግን ባህላዊ ምግቦቹ ተወዳጅና ተፈላጊነታቸው እየጨመረ እንደመጣም ይገልጻሉ::

እንግዳችን ወይዘሮ አዝርዕት አየለ ይባላሉ፤ በሃዋሳ ከተማ የአዚ ባህላዊ ምግብ ቤት ባለቤት ናቸው:: በሲዳማ ክልል ቦና አካባቢ ተወልደው ያደጉት ወይዘሮ አዝርእት፤ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በዚሁ አካባቢ ተከታትለዋል:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በሀዋሳ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠናቅቀዋል:: የኮሌጅ ትምህርታቸውን ቢጀምሩም ብዙ አልገፉበትም፤ ከዛ ይልቅ ውስጣዊ ፍላጎታቸው ለምግብ ዝግጅት ያደላ ነበርና የምግብ ዝግጅት ትምህርት ተከታትለው በዲፕሎማ ተመርቀዋል::

የምግብ ዝግጅት ትምህርታቸው በዘመናዊ የምግብ አሰራር ላይ ትኩረት ያደረገ ቢሆንም፣ እሳቸው ግን ባህላዊ ምግብ በተለይም የሲዳማ ባህል ምግብ ማዘጋጀት ይማርካቸዋል:: ‹‹ስለሲዳማ ባህላዊ ምግብ ለመግለጽ ቃላት ያጥረኛል›› የሚሉት ወይዘሮ አዝርእት፤ ‹‹እጅግ ጣፋጭና ለጤና ተስማሚ፤ ቀምሶ የማያውቀው ማንም ሰው ቢመገበው አዲስ የማይሆንበትና ምቹ ምግብ ነው›› ሲሉ ያስረዳሉ::

እሳቸው እንደሚሉት፤ የሲዳማ ባህላዊ ምግብ ከእንሰትና ከእንስሳት ተዋጽኦ፤ ከቦቆሎና ከአጃ ነው የሚዘጋጀው:: በዋናነት የእንሰት ተዋጽኦን ቆጮና ቡላን በመጠቀም በተለያየ አዘገጃጀት ተሰናድቶ ለተመጋቢዎች እንዲቀርብ የሚደረግ ነው::

እንሰት ተፍቆ ቆጮ ይዘጋጃል:: ቆጮው ይጨመቅና ተነፍቶና ተበጥሮ ከጸዳ በኋላ እንዲበስል ይደረጋል:: የበሰለው ቆጮም በተለያየ መልኩ ለምግብነት ይዘጋጃል:: ቂቤ ተጨምሮ ቡሪሳሜ፣ ጩካሜና አሞልቾ የሚባሉ ባህላዊ የምግብ አይነቶች ተዘጋጅተው ባማረ መልኩ ለተመጋቢዎች ይቀርባሉ::

ከቡላ ደግሞ ኮፉሜ፣ የቡላ ገንፎ፣ የቡላ ቂጣና ዱአሜ የሚባሉ ባህላዊ የምግብ አይነቶች ይዘጋጃሉ:: ከቦቆሎ የሚዘጋጁት ባህላዊ የምግብ አይነቶችም እንዲሁ የበቆሎ ቂጣ፣ ገፉማ፣ ገፉማ ጨንጨናሜና ሌሎችም ይጠቀሳሉ::

አብዛኛው የሲዳማ ባህላዊ ምግብ ከእንስሳት ተዋጽኦና ከእንሰት ጋር ተያያዥነት ያላቸው እንደሆኑ የሚናገሩት ወይዘሮ አዝርእት፤ ከእንሰት የሚዘጋጁ ምግቦች ከፍተኛ መጠን ያለው ቂቤ የሚፈልጉና በእርጎና በአሬራ የሚበሉ ስለመሆናቸው ያስረዳሉ፤ በሲዳማ ባህላዊ ምግብ ውስጥ እንሰትና የእንሰሳት ተዋጽኦ የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች እንደሆኑ ይናገራሉ:: ስጋም በስፋት በቆጮ እንደሚበላ አስረድተዋል::



በመንግሥት ሥራ ከሚተዳዳሩ ወላጆች የተገኙት ወይዘሮ አዝርእት፤ ተማሪ እያሉ ተምረው የመንግሥት ሠራተኛ መሆን ምኞታቸው ነበር:: ነገር ግን በንግድ ሥራ ያውም በምግብ ቤት ንግድ ከሚተዳደር ጋር ትዳር መመሥረታቸው የተማሩትን የምግብ ዝግጅት ይበልጥ እንዲያሳድጉት ምቹ ሁኔታ ፈጥረላቸው:: የባለቤታቸውን የምግብ ሥራ ንግድ እርሳቸው ትልቅ አቅም ሆነው ብዙ ርቀት እንዲጓዝም አድርገዋል::

ከዛሬ አስራ አምስት ዓመት በፊት የጀመሩት የምግብ ሥራ ዛሬ ላይ ታዋቂ የባህል ምግብ ቤት ሆኖ መቀጠል የቻለው ጠንክረው በመስራታቸውና የተለያዩ ፈተናዎችን ማለፍ በመቻላቸው እንደሆነም ይናገራሉ:: ሥራውን ሲጀምሩ የግለሰብ ቤት ተከራይተው ነበር፤ የቤት ክራዩ ከአቅማቸው በላይ እየሆነ ይመጣና ለማቆም ይገደዳሉ::

ከአንድ ዓመት ቆይታ በኋላ ወደ ሥራው እንደገና የተመለሱት ወይዘሮ አዝርእት፣ ሥራውን ይበልጥ አስፋፍተውና አጠንክረው በመሥራት ውጤታማ መሆን ችለዋል:: ለሥራ ትልቅ አክብሮት አላቸው:: ባለቤታቸውም ጠንካራ ሠራተኛና ሥራ አክባሪ እንደሆኑ ይመሰክራሉ::

በሆቴል ሥራው ቤተሰባቸውን ከማስተዳደር ባለፈም 50 ለሚደርሱ ቋሚ ሰዎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል:: ከሠራተኞቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነትም የአሰሪና ሠራተኛ ሳይሆን፣ ቤተሰባዊ መሆኑንም ነው ያጫወቱን::

ወይዘሮ አዝርእት ይህንን ባህላዊ ምግብ ከሆቴላቸው በተጨማሪ በየአካባቢው ተደራሽ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አምነው እየሰሩም ናቸው:: በሁሉም አካባቢዎች ተደራሽ ለማድረግ በተለይም በሃዋሳ አካባቢና አዲስ አበባ ከተማም ጭምር ቅርንጫፍ ለመክፈት እየተዘጋጁ ናቸው፤ ለዚህም በየጊዜው ከደንበኞቻቸው የሚያገኙት በጎ ምላሽ ትልቅ አቅም እየፈጠረላቸው እንደሆነ ነው ያስረዱት:: ከተለያዩ አካባቢዎች ወደ ባህላዊ ምግብ ቤታቸው ለሚመጡ ደንበኞቻቸው ምግቡን በየአካባቢያቸው ለማቅረብ ዕቅድ አላቸው:: በሀዋሳ ከተማ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ፕሮግራሞች ሲከናወኑም በጨረታ ተወዳድረው ባህላዊ ምግቡን ያቀርባሉ::

‹‹ተረፍረፍ ያለ ነገር እወዳለሁ፤ ውስን ያለ ነገር አልወድም›› የሚሉት ወይዘሮ አዝርእት፤ ከመቀበል ይልቅ መስጠት ያስደስታቸዋል:: ለመስጠት ደግሞ ውስን ያልሆነ ነገር እንዲኖራቸው ጠንክረው ሰርተዋል:: በሥራ የሚያምኑና ሥራ የሚያስደስታቸው ጠንካራ በመሆናቸውም እንደምንም ብለው ተፍጨርጭረው ኢኮኖሚያቸውን ማሳደግ ችለዋል::

ማንኛውም ሰው ሥራ ሳይንቅ ተፍጨርጭሮ መሥራትና መለወጥ እንዳለበት ይመክራሉ:: በተለይም ሴቶች ከኢኮኖሚ ጥገኝነት ለመላቀቅ የትኛውንም ሥራ መሥራት እንዳለባቸው ያስገነዝባሉ:: እሳቸው አሁን የደረሱበት ደረጃ ለመድረስ ብዙ ውጣ ውረዶችን እንዳሳለፉ በማስታወስም፣ በንግድ ዓለም ውስጥ ኪሳራ፣ ማጣት ማግኘት ያጋጥማል፤ ነገር ግን ሁሉን ተቋቁሞ ማለፍ ያስፈልጋል ይላሉ:: ትናንት ምንም ያልነበረን እንደሆንን ሁሉ፣ ዛሬ ብናጣ ነገን ተስፋ በማድረግ በጥንካሬና በጥረት መሥራት አለብን ሲሉ ይገልጻሉ::

በተለይም ሴቶች የቱንም ያህል እንቅፋት ቢገጥማቸው ጠባቂ ከመሆን ተላቀው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ተፍጨርጭረው መሥራት እንዳለባቸው ይመክራሉ:: ሴት የራሷ ገቢ ካላት በነጻነት መንቀሳቀስና በራስ መተማመኗ እንደሚጎለብት ያምናሉ::

ለዚህም ቁጠባ ወሳኝ መሆኑን ነው የሚመክሩት:: ከራስ ተደብቆ መቆጠብ እንደሚቻል የሚናገሩት ወይዘሮ አዝርእት ከባለቤታቸው ጋር የጀመሩት የምግብ ቤት ሥራ ኪሳራ ሲያጋጥመው ለአንድ ዓመት ያህል ከሥራ ውጭ እንደነበሩ ያስታውሳሉ:: ወደ ሥራው ለመመለስ ግን እርሾ የሚሆን ብር ነበራቸው:: ይህም ቆጥበው ያስቀመጡት ባለቤታቸው የማያውቁት ዘጠኝ ሺ ብር ነበራቸው:: ከባለቤታቸው ደብቀው እንዲሁም ከራሳቸው ቀንሰው የቆጠቡት ይህ ገንዘብ እንደገና ለከፈቱት ሆቴል መነሻ ሆኗቸው ዛሬ የሚወዱትን የሲዳማ ባህላዊ ምግብ በስፋት መሥራት እንዲችሉ ምክንያት ሆኗቸዋል::

ባለቤታቸው የጀመሩትን የምግብ ሥራ አጠናክረው ያስቀጠሉት የአዚ ባህላዊ ምግብ ቤት ባለቤት ወይዘሮ አዝዕርት፤ ተወዳጅ የሲዳማ ባህላዊ ምግቦችን በማሰናዳት ዕውቅና አትርፈዋል:: በአዚህ ባህላዊ ምግብ ቤት የሚዘጋጀውን የሲዳማ ባህላዊ ምግብ የቀመሰ ማንኛውም ሰው ምግቡን አድንቆ እያመሰገነ ያለበት ሁኔታ ይበልጥ እንዲሠሩ አድርጓቸዋል:: የሆቴል ቤቱ ተገልጋዮች ብቻም ሳይሆኑ እንግዶች ባህላዊ ምግቦቹ በብዙዎች ዘንድ ተወዳጅና ተመራጭ ስለመሆናቸው ግብረ መልስ እንደሚሰጧቸውም ወይዘሮ አዝርእት ይናገራሉ::

በቅርቡም የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከባለቤታቸው ከቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው ጋር በመሆን ምግብ ቤቱን መጎብኘታቸውንና መመገባቸውንና በምግቡም ደስተኛ መሆናቸውን መግለጻቸውን ወይዘሮ አዝርእት አጫውተውናል::

ወይዘሮ አዝርእት፤ ባህላዊ ምግቡን በአገር ደረጃ ተደራሽ ለማድረግ ደረጃውን የጠበቀና ባህሉን የሚገልጽ ባለ ኮከብ ሆቴል ለመክፈት ዕቅድ አላቸው:: ሆቴሉም በአፍሪካ ትልቁና የቱሪስት መስህብ መሆን እንዲችል ታስቦ የሚሠራ እንደሆነና በቱሪዝም ዘርፉ ብዙ ሥራ መሥራት የሚጠበቅ እንደሆነም ጠቁመዋል:: ባህላዊ ምግቦቹ ሳይበላሹ ለረዥም ጊዜ መቆየት የሚችሉ በመሆናቸው ከአገር ውስጥ ባለፈ ወደ ውጭ አገር ለመላክ ምቹ ሁኔታ እንዳለ የገለጹት ወይዘሮ አዝርእት፣ እሳቸው ምግቦቹን እየላኩ እንደሆነም ይናገራሉ::

ለሚያሰናዷቸው ምግቦች ዋናው ግብአት የሆኑትን የእንሰት ውጤቶች የሚገዙት በሲዳማ ክልል ከሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች ለአብነትም ከበንሳ፣ ከቦና፣ ከአርቤ ጎና፣ ከኤራ እና ከሌሎችም አካባቢዎች እንደሆነ ተናግረዋል::

ባህላዊ ምግቡን ለውጭ አገር በስፋት በመላክ ተደራሽ ማድረግ እንዲቻል እንሰት ላይ ብዙ መስራት አስፈላጊ ነው የሚሉት ወይዘሮ አዝዕርት፤ በአሁኑ ወቅት የእንሰት እጥረት እየተስተዋለ ስለመሆኑም ይናገራሉ::

ከዛሬ አስር ዓመት በፊት ወደ ሥራው ሲገቡ የነበረው የእንሰት መጠንና ዋጋ ዛሬ ላይ ካለው ጋር ፍጹም የሚገናኝ እንዳልሆነ አመልክተው፣ የአንድ ጭነት ቆጮ ዋጋ በሶስትና አራት እጥፍ ከማደጉ በላይ እጥረት እየተከሰተ ይላሉ:: ከዚህ ቀደም እንሰትን ብዙ የሚጠቀም ሰው አልነበረም:: በየአካባቢው ከምግብ ፍጆታ አልፎ ለገበያ አይቀርብም ነበር የሚሉት ወይዘሮ አዝርእት፣ አሁን ተፈላጊ እየሆነ መምጣቱን ይገልጻሉ:: ሰዎች በቦታው ላይ ጫትና የተለያዩ አትክልቶችን መትከል መጀመራቸውም ሌላው የእጥረቱ ምክንያት እንደሆነም ያብራራሉ::

ከዚህ ቀደም ለምግብነት የሚውለው እንሰት ተፍቆ ለረጅም ጊዜ ይቀመጥ እንደነበር ጠቅሰው፣ ከብዙ ቆይታ በኋላ ለምግብነት ይውል እንደነበርም ያስታውሳሉ:: በአሁኑ ወቅት ግን በብዙዎች ዘንድ ተፈላጊ እየሆነ በመምጣቱ በቤት ውስጥ የዕለት ምግብ ከመሆን አልፎ በገበያው በእጅጉ እየተፈለገ ነው ይላሉ:: በዚህም ምክንያት እንሰቱ ገና ሳይደርስ ለገበያ እየወጣ ነው:: ይህ ደግሞ ጥራቱ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ አለ:: ስለዚህ እንደቀድሞው ሁሉ እንሰት በየጓሮው በስፋት እንዲለማ በማድረግ ቀጣይነቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ሲሉ ያስገነዝባሉ::

የእንሰት ፍላጎት እየጨመረ ምርቱ ደግሞ እየተመናመነ የመጣ መሆኑን ተከትሎም ወይዘሮ አዝርእት በእንሰት ልማት ለመሳተፍ ፍላጎት እንዳደረባቸው ተናግረዋል፤ መሬት በኢንቨስትመንት ወስደው እንሰት በስፋት ለማልማት እየተዘጋጁ ናቸው:: ሌሎችም እንሰትን በማልማትና በመንከባከብ ሥራውን አስፍተው ቢሰሩ፤ በተለይም በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ባላቸው መሬት እንሰት ቢያለሙ በእጅጉ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ መክረዋል::

‹‹እንሰት በጓሮው ውስጥ ያለው ሰው ምንም ቢሆን ለረሃብ አይጋለጥም›› የሚሉት ወይዘሮ አዝርእት፣ ከእንሰት የተለያዩ የምግብ አይነቶች የሚገኝ በመሆኑ በጓሮው እንሰት የተከለ አርሶ አደር ሌላው ቢቀር አሚቾ የተባለውን የምግብ አይነት በቀላሉ ለልጆቹ መመገብ እንደሚችል ያስረዳሉ:: በመጨረሻም እንሰት እንደ ሌሎች የምግብ አይነቶች ሁሉ እጅግ ተወዳጅና ጠቃሚ የምግብ አይነት መሆኑን ጠቅሰው፣ እንሰትን አብዝተን በማልማት ተጠቃሚ እንሁን ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል::

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ቅዳሜ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ዋልያዎቹ በቻን ማጣሪያ ከሩዋንዳ ጋር አቻ ተለያዩ

ቦጋለ አበበ

በቀጣይ ዓመት አልጄሪያ በምታዘጋጀው የአፍሪካ ሀገራት ቻምፒዮን ሺፕ(ቻን) ዋንጫ ለመሳተፍ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በመጨረሻው የማጣሪያ ምእራፍ ላይ ይገኛል፡፡ የመጨረሻው ዙር ማጣሪያ የመጀመሪያ ጨዋታውን ትናንት በገለልተኛ ሜዳ በታንዛኒያ ቤንጃሚን ምካፓ ስታዲየም ሩዋንዳን ገጥሞም አቻ በሆነ ውጤት አጠናቋል፡፡ ጥሩ እንቅስቃሴን በጨዋታው ማሳየት የቻሉት ዋልያዎቹ የሩዋንዳን ግብ መድፈር ባይችሉም የትናንቱን ጨዋታ 0ለ0 ማጠናቀቃቸው ለሶስተኛ ጊዜ በቻን ለመሳተፍ ያላቸውን ተስፋ አያጨልመውም፡፡ ይሁን እንጂ የመጨረሻው የዘጠና ደቂቃ ፍልሚያ ሩዋንዳ በሜዳዋና በደጋፊዋ ፊት የምታደርገው እንደመሆኑ ዋልያዎቹ ቀላል ፈተና አይጠብቃቸውም፡፡

ከዋናው የዋልያዎቹ ስብስብ በግብጽ ሊግ የሚጫወተው አማካይ ሽመልስ በቀለ እንዲሁም በደቡብ አፍሪካ የሚገኘው የአጥቂ ስፍራ ተጫዋች አቡበከር ናስር በውድድሩ ላይ የማይሰለፉ መሆናቸው የአሰልጣኝ ውበቱን ቡድን በትናንቱ ጨዋታ ግብ ሳያስቆጥር እንዲወጣ አድርጎታል፡፡

በአገር ውስጥ ሊጎች የሚጫወቱ ተጫዋቾች ብቻ በሚሳተፉበትና በካፍ አዘጋጅነት በየሁለት አመቱ የሚደረገው የቻን የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር የማጣሪያ ጨዋታዎች ከነሀሴ ወር መጀመሪያ አንስቶ እየተከናወኑ ይገኛሉ። በቅድመ ማጣሪያ ጨዋታው ከደቡብ ሱዳን ጋር የተደለደለችው የኢትዮጵያ ስቴድየሞች የካፍን መመዘኛ መስፈርት አለማሟላታቸውን ተከትሎ በተጣለው ዕገዳ ልክ እንደ አፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎቿ ሁሉ ይህንንም ጨዋታ ከሜዳዋ ውጪ ታንዛኒያ ላይ ለማድረግ ተገዳለች።



ወሳኙ የመልስ ጨዋታ ከሳምንት በኋላ በሩዋንዳ ሲካሄድ ዋልያዎቹ ከባድ ፈተና ሲገጥማቸው ይችላል፤

የመጨረሻውን የማጣሪያ ጨዋታም ኢትዮጵያ እና ተጋጣሚዋ ሩዋንዳ የካፍን መስፈርት የሚያሟላ ስታዲየም የሌላቸው መሆኑን ተከትሎ እገዳ ላይ ቢገኙም ሩዋንዳ አንድ ስቴድየሟ ጨዋታ እንዲያስተናግድ ፍቃድ ማግኘቱ ይታወቃል፡፡ ይህንን ተከትሎ ሩዋንዳ ነሐሴ 29 የሚደረገውን የመልስ ጨዋታ በሁዬ ዓለም አቀፍ ስታዲየም እንደምታስተናግድ ይፋ ተደርጓል። ኢትዮጵያ ግን አሁንም ስቴድየሞቿ ፍቃድ ስላላገኙ ከሩዋንዳ ጋር ትናንት ያደረገችውን የመጀመሪያ ጨዋታ በታንዛኒያ ዳሬሰላም ቤንጃሚን ምካፓ ስታዲየም እንደምታደርግ ተገዳለች፡፡

በአፍሪካ ከዋናው አፍሪካ ዋንጫ ቀጥሎ ትልቁ የእግር ኳስ መድረክ የሆነው የቻን ዋንጫ በአገር ውስጥ ሊጎች የሚጫወቱ ተጫዋቾችን ብቻ ለማበረታታት በካፍ አማካኝነት እኤአ በ2007 የተዋወቀ ሲሆን 2009 ላይ በኮትዲቯር አዘጋጅነት ለመጀመሪያ ጊዜ ተካሂዷል። ከጊዜ ወደ ጊዜ በውድድሩ የሚሳተፉ አገራት ቁጥርም እያደገ ሄዶ ትኩረት ከሚሰጣቸው የስፖርት መድረኮች አንዱ ሆኗል። የአለምን እግር ኳስ በበላይነት የሚመራው ፊፋም እኤአ 2010 ላይ ለዚህ ውድድር እውቅና ሰጥቶታል።

ኢትዮጵያ ከሰላሳ አንድ አመታት በኋላ እኤአ 2013 ላይ በደቡብ አፍሪካ አዘጋጅነት በተካሄደው የአፍሪካ ዋንጫ መሳተፏን ተከትሎ በእግር ኳሱ የተፈጠረው ከፍተኛ መነቃቃት ይታወሳል። የዚያ ትውልድ ታሪካዊ ተጫዋቾችና የዋልያዎቹ አሰልጣኝ የነበሩት ሰውነት ቢሻው ከአፍሪካ ዋንጫው ማግስት በተመሳሳይ ደቡብ አፍሪካ ላይ በተካሄደው የቻን ዋንጫ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ መሳተፍ ችለዋል። ለዚህ ተሳትፎም የመጨረሻውን የማጣሪያ ጨዋታ ከሩዋንዳ ጋር ከሜዳቸው ውጪ ተፋልመው ማለፋቸው አይዘነጋም። በተለይም በዚያ የመጨረሻ የማጣሪያ ፍልሚያ የዋልያዎቹ ቋሚ ግብ ጠባቂ የነበረው ጀማል ጣሰው ጨዋታው በመለያ ምት እንደሚጠናቀቅ ከአሰልጣኙ ጋር ቀደም ብለው በመግባባት የመለያ ምት የማዳን የተሻለ ብቃት ያለው ግብ ጠባቂ ሲሳይ ባንጫ ተቀይሮ እንዲገባ ማድረጋቸው አይዘነጋም። ሲሳይ ባንጫም ተቀይሮ ገብቶ ሁለት የመለያ ምቶችን በማዳን ዋልያዎቹን ለቻን ዋንጫ ያበቃበት ክስተት የሚታወስ ነው።

ዋልያዎቹ በቀጣዩ የቻን ውድድርም በአሰልጣኝ ዮሐንስ ሳህሌ እየተመሩ በጋቦን በተካሄደው ዋንጫ ላይ መሳተፍ ችለዋል። በሁለቱም ብቸኛ ተሳትፏቸው ግን ከምድባቸው ሳያልፉ ቀርተዋል። ዘንድሮም በመጨረሻው የማጣሪያ ጨዋታ በአሰልጣኝ ውበቱ እየተመሩ ለሶስተኛ ጊዜ ለመሳተፍ ሩዋንዳን በሜዳዋ ከሳምንት በኋላ ማሸነፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ማን ያውቃል የሲሳይ ባንጫ ታሪክ በፋሲል ገብረሚካኤል ይደገም ይሆናል፡፡

## ከኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ
### ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# ለውጤታማ ስፖርተኛ ብቃት ያለው ምልመላ

የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ለአዲስ አበባ እና ለአሰላ (በአትሌት ጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል) ካምፓሶች የሚያካሄደውን የ2015 ዓ.ም የእጩ ሰልጣኞች የመጀመሪያ ዙር ምልመላ ስኬታማ በሆነ መልኩ እያከናወነ ይገኛል፡፡

የእጩ ሰልጣኞች ምልመላው ከነሐሴ 08 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ በመካሄድ ላይ የሚገኝ ሲሆን የአካዳሚው መልማይ ቡድኖችም የፀጥታ ችግር ካለባቸው አካባቢዎች በስተቀር ሁሉንም የአገሪቱ ክፍሎች በመንቀሳቀስ ዕጩ ሰልጣኞችን እየመለመሉ ይገኛሉ፡፡ የእጩ ሰልጣኞች ምልመላ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወንም ግልፅ፣ ፍትሃዊ እና አሳታፊ የሆነ ወጥነት ያለው የመመልመያ መስፈርት ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

በ2015 ዓ.ም አካዳሚውን ለሚቀላቀሉ እጩ ሰልጣኞችን ለሚመለምሉ መልማይ ኮሚቴ አባላት በአካዳሚ ከፍተኛ አመራሮች ቀደም ብሎ ሐምሌ 28 ቀን 2014 ዓ.ም በአካዳሚው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ኦረንቴሽን ሰጥቷል፡፡ በመድረኩ የአካዳሚው የአስተዳደርና ልማት ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ፍቃዱ መኩሪያ፤ አገራዊ የስፖርት ፖሊሲውን መነሻ በማድረግ ስፖርት አካታች ሁሉን አቀፍ ፆታ፣ ሃይማኖት እና ጎሳ የማይለይ መሆኑን በማመላከት ሳይንሳዊ የምልመላ፣ መረጣና ስልጠና አሰጣጥ አጋዥ ፅሁፎችን በማስደገፍ የስፖርተኞች ተሰጥኦ እና ልዩ ተሰጥኦ በተመለከተ፣ የተሰጥኦ የዕድገት ደረጃዎች፣ የስፖርት እድገት እና ስፖርት ከኢኮኖሚ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ አንፃር ያለው ፋይዳ ከአካዳሚው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማነፃፀር ገለፃ አድርገዋል፡፡





የአካዳሚው የጥናትና ምርምርና የማማከር አገልግሎት ምክትር ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አመንሲሳ ከበደ፤ ወጥነት ያለው አጠቃላይ የምልመላ እይታ መርሆዎች ማስፈፀሚያ ሰፊ ሰነድ ያቀረቡ ሲሆን በሰነዱ ላይም ገንቢ ውይይት ተደርጎበታል፡፡

ምልመላውን በተመለከተ የስራ መመሪያና አቅጣጫዎችን ያስቀመጡት የአካዳሚው ዋና ዳይሬክተር አቶ አምበሳው እንየው፤ ሁሉም የምልመላ አባላት አካዳሚው የተሰጠውን አገራዊ ተልዕኮ እና ራዕይ እውን ለማድረግ የሚያስችል ተከታታይ እና ወጥነት ያለው ምልመላ ማካሄድ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል፡፡«በቅርቡ በኮሎምቢያ በተደረገው የዓለም ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ውጤት ያመጡ የአካዳሚው አትሌቶችን የሚተኩ ሰልጣኞችን መመልመል ይገባልም»ብለዋል፡፡

ለ2015 በጀት አመት ስልጠና አካዳሚውን ለአራት አመት ስልጠና የሚቀላቀሉ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ለአትሌት ጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል 54 ወንድ እና 97 ሴት በድምሩ 151 ሰልጣኞች ናቸው። ለአዲስ አበባው ካምፓስ 41 ወንድ እና 68 ሴት በድምሩ 109 ሰልጣኞች ሲሆኑ በአጠቃላይ ለሁለቱም ካምፓሶች 95 ወንድ እና 165 ሴት በድምሩ 260 ሰልጣኞችን ብቃት እና ጥራትን መሰረት ባደረገው ምልመላ ተለይተው አካዳሚውን ይቀላቀላሉ፡፡

የእጩ ሰልጣኞች ምልመላውን ለማከናወን አካዳሚው ዘጠኝ መልማይ ቡድኖችን በማዋቀር በመላው አገሪቱ አሰራጭቷል፡፡ የመልማዮቹ የጉዞ ፍኖተ ካርታ(የጉዞ መስመር) ተዘርግቶላቸዋል፡፡ ቡድን አንድ፡ አዲስ አበባ ከተማ፤ ሰበታ፤ ገላን፤ ቢሾፍቱ፤ ሞጆ፤ ወንጂ፤ አዳማ ከተማ ሲሆን ቡድን ሁለት፡ ፍቼ፣ ደብረማርቆስ፣ እንጅባራ፤ ባህር ዳር፣ ደብረ ታቦር፤ ጎንደር ከተማ፤ ደባርቅ ናቸው፡፡

ቡድን ሶስት፡ መልማዮች የጉዞ ፍኖተ ካርታ ደግሞ፣ አሰላ ከተማ እና አካባቢው፣ በቆጂ፣ ኮፈሌ፣ ባሌ ሮቤ፤ ደሎመና፤ ጊኒር ሲሆን ቡድን አራት፡ ጅማ፣ አጋሮ፣ ቦንጋ ፤ በደሌ ፤ መቱ፣ ጋምቤላ ከተማ ፤ (ላሬ ፤አበቦ) ናቸው፡፡

የቡድን አምስት፡ መልማዮች ደግሞ ወደ ዝዋይ፣ ሻሸመኔ፤ ሀላባ ቁሊቶ፤ ሀዋሳ፤ አርቤጎና፣ ዲላ ፣ አገረ ማርያም፤ ጉጂ ሲሆኑ የቡድን ስድስት፡ መተሀራ፤ አዋሽ ሰባት/አርባ (አካባቢው)፣ ድሬዳዋ፣ ሃረር፣ ጅግጅጋ አቅንተዋል፡፡ ቡድን ሰባት፡ ደብረብርሃን ፤ ኮምቦልቻ ፤ደሴ፤ ተንታ፤ ወልዲያ ፤ቆቦ፣ ሲያመሩ፣ ቡድን ስምንት፡ ሶዶ ጉራጌ ፤አረቅጥ ፤ ሆሳህና ከተማ ፤ ወላይታ፣ አርባ ምንጭ እና ጂንካ እንዲሁም ቡድን ዘጠኝ፡ ሱሉልታ ፤ ለገጣፎ ፤ወሊሶ፣ ወልቂጤ ፤ቡራዩ፤ ሆለታ፤ አዲስ አለም፤ ጊንጪ አምቦ ከተማ መዳረሻቸውን በማድረግ ዕጩዎችን በመመልመል ላይ ይገኛሉ፡፡

አካዳሚው ምልመላውን በአትሌቲክስ፣ በቮሊቦል፣ በእግርኳስ፣ በቅርጫትኳስ፣ በብስክሌት፣ በፓራሊምፒክ (በአይን ጉዳት ጭላንጭል እና በእጅ ጉዳት ከክርን በላይ ጉዳቶች) በቦክስ፣ ወርልድ ቴኳንዶ እና በጠረጴዛ ቴኒስ ስፖርት አይነቶች በሁለቱም ፆታ እንደየስፖርት አይነቱ ወጥ የሆነ የመመልመያ መስፈርት በማዘጋጀት ምልመላ እያደረጉ ሲሆን ለተመረጡ እጩ ስፖርተኞችም የጤና ምርመራ፣ የአካል ብቃት እና የክህሎት ልኬቶችን ያከናውናሉ፡፡ አካዳሚው ከዚህ የመጀመሪያ ዙር የእጩ ሰልጣኞች ምልመላ በኋላ በመላው አገሪቱ የተመረጡ የእጩ ሰልጣኞችን መረጃ ወደ አንድ ቋት በማስገባት የተሻለ ውጤት ያላቸውን እጩ ሰልጣኞች ከሚፈልገው ቁጥር ሲሶ በመጨመር መስከረም 2015 ዓ.ም ላይ ብዙ ሙያተኞች የሚሳተፉበትን የመጨረሻ ዙር እጩ ሰልጣኞች ምልመላ ያካሂዳል።